እንቅፋት የሚፈጥሩ ባህላዊ አስተሳሰቦችን ለመዋጋት ምን ዓይነት አሳቦችን ታቀርባለህ?

4. ሀ) እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመሪነት ሲያዘጋጀው ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) አንድ ግለሰብ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚሆኑ ሁኔታዎች የሚሰጣቸው ምላሾች እግዚአብሔርን በሚገባ የሚያገለግልባቸውን መንገዶ እንዴት እንደሚወስኑበት ግለጽ። ሐ) ስጦታ ያላቸው ወጣቶች እግዚአብሔርን የሚፈሩ ውጤታማ መሪ ዎች እና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንዲሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በበለጠ አብረዋቸው በሚሠሩባቸው መንገዶች ላይ ተ ወያዩ።

5. ሀ) በዚህ ትምህርት ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስፈልጋል በሚል መረዳት የቀረበውን መደበኛ ትምህርት ብዙ መሪዎች ስለ መደበኛ የሥነ መለኮት ትምህርት ካላቸው የተለመደ አስተሳሰብ ጋር በማነጻጸር ተወያዩበት። የምትስማማበትን እና የማትስማማበትን ነገር አብራራ። ለምን እንደምትስማማ እና እንደማትስማማ አብራራ። ለ) መደበኛ የሥነ መለኮት ትምህርት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ ማገልገል የሚችሉበትን ጥሩ መሣሪያ ሲሰጣቸው ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ። ሐ) መደበኛ የሥነ መለኮት ትምህርት ትልቅ ፈተና ሆኖበት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይን ባሕርይ እና የአገልጋይነት መንፈስ ሲለውጥ እንዴት እንዳየህ ግለጽ። መ) በሥነ መለኮት ት/ቤቶች የሚማሩ ሰዎች ወደ ትዕቢት እና የግል ፍላጎቶችን ለማሟላት ወደ መፈለግ የሚመራውን ፈተና መቋቋም እንዲችሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?



# ትምህርት አሥራ ዘጠኝ

## ክፍል ሦስት

### አንደኛ ቀን

በቤተ ክርስቲያን አመራር ጥናታችን፣ የውጤታማና መንፈሳዊ አገልጋይን ሁለት ዐበይት ክፍሎችን መርምረናል። በክፍል አንድ፣ የመንፈሳዊ መሪን ባሕርያትና ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውን በማጥመድ ስሙን የሚያጎድፉትን ኃጢአቶች አጥንተናል። ይህ የመንፈሳዊ አመራር ወሳኝ ክፍል መሆኑን ገልጸናል። እግዚአብሔርን ከሁሉም በላይ የሚያሳስበው ባሕርያችን ነው። እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው እጅግ ውጤታማ መሪዎች መንፈሳዊ ባሕርይ ያላቸው ናቸው። በክፍል ሁለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሥራቸው ውጤታማ ለመሆን ሊማሯቸው የሚገባቸውን አሥራ ሁለት ክህሎቶች ተመልክተናል። እነዚህን ክህሎቶች በመማር፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት የሚጠቀምብን ስለታም መሣሪያ እንሆናለን።

በዚህ የመጨረሻ ክፍል ከቤተ ክርስቲያን አመራር ጋር የተ ያያዙትን የተለያዩ እውነታዎች እንመለከታለን። ቤተ ክርስቲያን ከዓለማዊ ድርጅቶች የተለየች መሆኗንና ይህም በአመራር ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እናጠናለን። ከቤተ ክርስቲያን ታሪ ክም ስለ አመራርና አስተዳደር መዋቅሮች አንዳንድ ትምህርቶችን ለመውሰድ እንሞክራለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናትና ወንጌላውያን ምን ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ማካሄድ እንዳለባቸው እንመለከታለን። እንዲሁም መደበኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት ሥልጠና ለቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ስለሚያበረክተው አስተዋጽኦ እና ስለ ሴቶች አገልግሎት አንዳንድ መርሖዎችን እናያለን።

(ማስታወሻ፡- በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከተው መሪዎች በአሳብ የሚለያዩባቸውን ትምህርቶች ነው። በክፍሉ ውስጥ የተጸንባረቀው የደራሲው አመለካከት ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን

ጉዳዮች በትኩረት በመመልከት እግዚአብሔር የሚፈልገውንና ለቤተ ክርስቲያን ከሁሉም የሚሻለውን አቅጣጫ መከተላቸውን ቢያረጋግጡ መልካም ነው እላለሁ።)

አንድ ጠዋት ሦስት ከሥነ መለኮት ኮሌጅ የተማረቁ ሰዎች ሻይ ቤት ቁጭ ብለው በኢትዮጵያ ስላለው የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ መነጋገር ጀመሩ። ሁሉንም ያሳሰባቸው ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቃቸው ነበር። ይህን ሁኔታ ለመለወጥ ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ነጥቦች መዘርዘር ጀመሩ። አንደኛው፣ «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በደንብ የሠለጠነ መጋቢ ሊኖረን ይገባል፣» ሲል ተናገረ። «ይህ መጋቢ እግዚአብሔርን የመስማትና ከዚያም ሽማግሌዎችና ሌሎችም ምን ማድረግ እንዳለባቸው የመናገር ሥልጣን ሊኖረው ይገባል። በየሳምንቱ ከምስባኩ ሆኖ ሊያስተምራቸው ይገባል። ጠንካራ አብያተ ክርስቲያናት ሊኖሩን የሚችሉት የመምራት ሥልጣን ያለው መጋቢ ሲቀባ ብቻ ነው፣» ሲል አሳቡን አብራራ። «የለም፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ አምባገነን የሚሆኑ መጋቢዎች ሊኖሩን አይገባም። ነገር ግን ሽማግሌዎች የበለጠ ቢሳተፉ መልካም ነው። ሽማግሌዎችን በማሠልጠን በተሻለ መንገድ እንዲያስተምሩ፣ እንዲሰብኩና እንዲመሩ ብናደርግ ነው የሚሻለው፣» ሲል ሁለተኛው ምሩቅ አስተያየቱን ሰነዘረ። «ለምን የቀድሞይቱን ቤተ ክርስቲያን የአመራር ሁኔታ አናጠናም? ምናልባት ይህ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን እንዴት መመራት እንዳለባት ለመረዳት ያግዘን ይሆናል። የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ቃሉን ያውቁና እምነታቸውን በትጋት ለሌሎች ያካፍሉ ነበር። በአንድ ትውልድ ዘመን ሮምን ከዳር እስከ ዳር ለማዳረስና ማኅበረሰቦቻቸውን ለመለወጥ ችለው ነበር። ምናልባት እንዲህ ዓይነቱ ኃይልና ከሁኔታዎች ጋር የመዛመድ ብቃት እንደገና እንዲኖረን ለማስቻል ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር አንዳንድ ትምህርቶችን ይሰጠን ይሆናል፣» አለ ሦስተኛው ሰው። ሦስቱም በዚህ አሳብ በመስማማታቸው ሳምንቱን አዲስ ኪዳን በተለይም የሐዋርያት ሥራንና የኤፌሶንን መልእክት በማጥናት ስለ አመራር ጠቃሚ ትምህርቶችን ለማግኘት ወሰኑ።



ሦስቱ ምሩቃን የቤተ ክርስቲያን አመራርን ለመረዳት አዲስ ኪዳንን በሚያጠኑበት ጊዜ፣ «ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?» የሚለው ጥያቄ መጀመሪያ ሊመልሱት የሚገባቸው መሆኑን ተገነዘቡ። ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ለመነጋገር ከፈለግን፣ መሪዎች የሚመሩት ድርጅትን ምንነት ማወቅ ይኖርብናል። እንደ እስራኤል ያለችውን አገር ይሆን እየመራን ያለነው? እንደዚያ ከሆነ፣ ልክ እንደ ንጉሥ ዳዊትና እንደ ካህናት ነው መምራት የሚጠበቅብን። አመራር የፖለቲካና የሃይማኖት ውህደት ይሆናል። ወይስ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ካሉት ድርጅቶች ሁሉ የተለየች ነች? ከ«ድርጅት» ይልቅ «አካል» ነች?

1ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ከላይ የተነሣውን ጥያቄ እንዴት ትመልሰዋለህ? ቤተ ክርስቲያን እንደ እስራኤል አገር ያለች ነች? የቤተ ክርስቲያን አመራርስ ከአገር አመራር ጋር አንድ ዓይነት ነውን? ወይስ ቤተ ክርስቲያን የተለየ አመራር የምትከተልና ከእስራኤል የተለየች ነች? ለ) እስራኤልና ቤተ ክርስቲያን የሚለያዩ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን የምትለየው በምን በምን መንገዶች ነው? ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አመራር ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ያሳያል?

2ኛ ጥያቄ፦ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ፦ ሮሜ 12:4-8፤ 1ኛ ቆሮ. 3:16-17፤ 12:12-28፤ ኤፌ. 2:19-22፤ 4:15-16። ሀ) እያንዳንዱ ጥቅስ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ነው የሚገልጻት? ለ) የቤተ ክርስቲያን አባላትንስ? ሐ) የቤተ ክርስቲያንን መሪ የሚገልጹት እንዴት ነው?

### የቤተ ክርስቲያንን አመራር የተለየ የሚያደርገው የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ምንድን ነው?

ዛሬ «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል በምንለማበት ጊዜ፣ በአብዛኛው የምናስበው ስለ ሕንጻ ወይም ስለ ቤተ እምነት ነው። ለብዙ ሰዎች «ቤተ ክርስቲያን» ማለት ክርስቲያኖች በየእሑዱ ለአምልኮ የሚሰባሰቡበት ቦታ ነው። እነዚህ ሕንጻዎች የቆርቆሮ ቤቶች ወይም እንደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ታላላቅ ሕንጻዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ሕንጻው ትልቅና የሚያምር ከሆነ፣ የተሻለ ይሆናል ብለን እናስባለን። ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ ክርስቲያን ጋር በምንተዋወቅበት ጊዜ «የየትኛው ቤተ ክርስቲያን

አባል ነህ?» ብለን እንጠይቀዋለን:: እርሱም «የቃለ ሕይወት»፣ «የመካነ ኢየሱስ»፣ «የሙሉ ወንጌል» ወይም «የመሠረተ ክርስቶስ» አባል መሆኑን ይነግረናል:: እነዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ በርካታ ቤተ እምነቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው:: ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው አባል የሚሆንባት ድርጅት ናት::

ነገር ግን በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ለነበረ አንድ ሰው «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል ትርጉም ብንጠይቀው፣ የተለየ መልስ ነው የሚሰጠን:: በምንም ዓይነት ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሊያስብ አይችልም:: ምክንያቱም የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ዎች አልነበራትም:: አማኞች የሚሰባሰቡት በግለሰቦች ቤቶች ውስጥ ነበር:: ይህም እንደ ዛሬው ዘመን የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ሳይሆን፣ እንደ ሠፈር ፕሮግራም ይመስል ነበር:: እንዲሁም የቀድሞዎቹ አማኞች ስለ ቤተ እምነት ሊያስቡ አይችሉም ነበር:: ምክንያቱም በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩትን አማኞች የሚያካትት መዋቅር አልነበረም:: ቤተ ክርስቲያን ከተለያዩ ድርጅቶች የተገነባች ነች የሚለው አስተሳሰብ እንግዳ ብቻ ሳይሆን፣ የማያስደስት ስሜት ይፈጥርባቸው ነበር::

በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለምንኖር ሰዎች፣ ቤተ ክርስቲያን የተደራጀች አካል መሆኗ ለመጀመሪያዎቹ አማኞች ምን ትርጉም ይሰጥ እንደ ነበረ ለማወቅ እንቸገራለን:: እነዚህ የቀድሞ አማኞች የክርስቶስ ሞት የእምነታቸው መሠረትና መዳንን ያስገኘላቸው የእግዚአብሔር ተግባር እንደ ሆነ ቢገነዘቡም፣ ዕለተ በዓለ ኀምሳን የሚመለከቱት እንደ ትልቅ የታሪክ አቅጣጫ ለውጥ ነበር:: በዕለተ በዓለ ኀምሳ እግዚአብሔር ልዩ ሕዝብን እንደ ጀመረ ይገነዘባሉ:: ዕ ለተ በዓለ ኀምሳ መንፈስ ቅዱስ የመጣበት ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህ አዲስ ሕዝብ የተጀመሩበትም ነው::

3ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ጴጥ. 2:4-5፤ 9፣ 11-12 አንብብ:: ሀ) ጴጥሮስ አማኞች ናቸው የሚላቸውን የተለያዩ ነገሮች ዘርዝር:: ለ) እነዚህ እንዴት ተ መሳሳይና ከብሉይ ኪዳን የተለዩ መሆናቸውን ግለጽ::

1. የብሉይና የአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ልዩነት መ ረዳት::



ዛሬ አማኞች የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚለያዩባቸው ብዙ ነገሮች መኖራቸውን መረዳታቸው አስፈላጊ ነው:: ብዙ ክርስቲያኖች እነዚህን ልዩነቶች ባለመ ረዳታቸው፣ ለብሉይ ኪዳን አይሁዶች ብቻ የተገነሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ከክርስቲያኖች ሕይወት ጋር ለማዛመድ ሲሞክሩ እንመለከታለን:: የሚከተሉትን ልዩነቶች ተመልከት:-

ሀ. የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤል ተብላ የምትጠራ አገር ሕዝብ ነበሩ:: ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተለየ ዳርቻ እንደ ነበረው ያሳያል:: እግዚአብሔር አብርሃም በምድሪቱ መካከል እንዲመላለስ ሲጠይቀው፣ ለወደፊት ትውልዶች ዳርቻን እንዲወስን መናገሩ ነበር (ዘፍጥ. 13:14-17):: ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከየትም ነገድና ጎሳ ሰዎች የተ ሰባሰቡባት ናት:: እኛ መንፈሳዊ ሕዝብ እንጂ፣ አካላዊ ሕዝብ ወይም አገር አይደለንም:: ቤተ ክርስቲያን በአንድ የዓለም ክፍል ወይም በአንድ አገር ውስጥ የምትገኝ አይደለችም:: ስለዚህ ክርስቲያን «አገር» የሚባል ዓይነት ነገር የለም:: ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ዳርቻችንን እንደሚያሰፋ ወይም ከታዘዝነው ከሌሎች አገሮች እንደሚጠብቀን የሚናገሩትን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች በቀጥታ ለቤተ ክርስቲያን ማዛመድ የለብንም::

ጳውሎስ ቀዳሚው ዜግነታችን ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ መሆኑን ተናግሯል (ፊልጵ. 3:20-21):: ክርስቲያኖች በሰማይ ወዳለው እውነተኛው ቤታቸው የሚጓዙ «እንግዶች» ወይም «መናኞች» ናቸው (1ኛ ጴጥ. 2:11):: ቤተ ክርስቲያን ይህንን እውነት በመርሳቷ አንዳንድ ሰዎች ሌሎችን ለማሳመን ጉልበት ለመጠቀም ሞክረዋል:: እጅግ የከፋው የቤተ ክርስቲያን ዘመን የታየው ሌሎች ክርስቲያኖች እና «የክርስቲያን» አገር አካል እንዲሆኑ ለማሳመን የመስቀል ጦርነት በታዘዘበት ወቅት ነበር::

ለ. የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ በ12 ነገዶች የተ ከፋፈሉ ነበሩ:: አንዳንዶቹ ነገዶች ልዩ ነበሩ:: ለምሳሌ፣ የሃይማኖት መሪዎች ሁልጊዜም የሚመጡት ከሌዊ ነገድና ከአሮን ጎሳ ነበር:: በልዩ አለባበሳቸው ሃይማኖታዊ መሪዎች መሆናቸውን ያሳዩ ነበር::

የፖለቲካ መሪዎች የሚመጡት ከይሁዳ ነገድና ከዳዊት ጎሳ ነበር:: አዲስ ኪዳን ግን ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ከሁሉም ጎሳዎች የሚካተቱባት እንደ ሆነች ይናገራል (ገላ. 3:28):: ሁላችንም የንጉሥ ልጆችና ካህናት ነን (1ኛ ጴጥ. 2:9):: የትኛውም ነገድ ከሌላው የበለጠ አስፈላጊ አይደለም:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከየትኛውም ቡድን ሊመረጡ ይችላሉ:: በአዲስ ኪዳን መሪን መሪ ካልሆነው ሰው ለመለየት የሚያስችል አለባበስ አልነበረም:: ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰዎች ከተለያዩ ነገዶች ለመሪነት እንደሚመረጡና የተለዩ ልብሶችን እንደሚለብሱ የሚናገሩ ጥቅሶች ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ አይሆኑም::

ሐ. አይሁዶች የሚዋጋላቸው ሠራዊት ነበራቸው:: ይህ ሠራዊት አይሁዶችን ከሌሎች አገሮች ጥቃት ለመጠበቅና ድንበራቸውን ለማስፋት ያገለግል ነበር:: ሰዎችን ለመቆጣጠር ኃይልን ይጠቀም ነበር:: እኛ ግን አካላዊ ሠራዊት የለንም:: ጳውሎስ የጦር መሣሪያዎችን በመጠቀም ከሰዎች ጋር እንደማንዋጋና ዳሩ ግን መንፈሳዊ ጦርነትን እንደምንዋጋ ተናግሯል (ኤፌ. 6:12):: ቤተ ክርስቲያን ይህንን በመዘንጋት በኃይል አስገድዳ ሰዎችን ለማሳመን በምትሞክርበት ጊዜ፣ ወይም የማያምኑ ሰዎች ሕጎቿን እንዲከተሉ ለማድረግ ኃይልን ስትጠቀም፣ የብሉይ ኪዳን አማኞች እንጂ የአዲስ ኪዳን አማኞችን መርሖዎች እየተከተለች አይደለም ማለት ነው::

መ. በብሉይ ኪዳን የአምልኮ ማዕከል ሕንጻ ነበር:: መጀመሪያ የመገናኛው ድንኳን ነበረ፣ በኋላ ደግሞ ቤተ መቅደስ:: እነዚህ የአምልኮ ቦታዎች በጌጣጌጥ ያሸበረቁ ነበሩ:: ሰዎች እነዚህን ቤተ መቅደሶች እንዲያከብሩ የሚጠይቁ ብዙ ደንቦችም ነበሩ:: የቤተ መቅደሱ መጠን የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚያመለክት ነበር:: በአዲስ ኪዳን ግን የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው የሚባል ቤተ መቅደስ የለም:: አሁን እግዚአብሔር የሚኖረው በሰዎች ልብ ውስጥ ነው:: አማኞች የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ቤተ መቅደስ ሕያው ዓለቶችና መንፈሳዊ ቤተ መቅደስ እንዲሆኑ ተጠርተዋል (1ኛ ጴጥ. 2:5፤ 1ኛ ቆሮ. 3:16):: ሁለት ወይም ሦስት



የእግዚአብሔር ሕዝብ በሚሰባሰቡበት ጊዜ፣ በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ በነበረበት መልኩ በመካከላችን ይገኛል:: ስለዚህ ጫማን ስለ ማውለቅ ወይም ወደ ቤተ መቅደሱ ስለ መጸለይ የሚናገሩ ትእዛዛት ለአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚዛመዱ አይደሉም::

ሠ. ብሉይ ኪዳን የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ቢከተሉ ሥጋዊ በረከቶችን እንደሚያገኙ ይናገራል (ዘዳግ. 28):: የሙሴን ሕግ ቢከተሉ፣ አገራቸው ከጠላት እንደምትድን፣ ብዙ እህል እንደሚኖራቸው፣ ብዙ ቤተሰቦች እንደሚኖሯቸው፣ ወዘተ. . . ቃል ተገብቶላቸዋል:: በአዲስ ኪዳን ግን በዚህች ምድር ላይ ሥጋዊ በረከቶችን እንደማናገኝ ተነግሮናል (1ኛ ጴጥ. 1:4፤ ኤፌ. 1:3-14):: ስለዚህ ስለ ሥጋዊ በረከት ወይም ልጆችን ስለ ማግኘት የሚናገሩትን ጥቅሶች በቀጥታ ከራሳችን ጋር ማዛመድ የለብንም:: እነዚህ የብሉይ ኪዳን እንጂ የአዲስ ኪዳን የተስፋ ቃሎች አይደሉም::

ረ. የብሉይ ኪዳን አምልኮ በውጫዊ ሥርዓቶች ላይ ያተኩር ነበር:: የእንስሳት መሥዋዕቶች፣ ዕጣን ማጠንና ሌሎችም የአይሁድን አምልኮ የሚያንጸባርቁ ሥርዓቶች ነበሩ:: በአዲስ ኪዳን ግን አምልኮ በቀዳሚነት የልብ ጉዳይ ነው:: መሥዋዕታችን ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት አሳልፎ መስጠት ነው (ሮሜ 12:1-2):: ይህም የአምልኮ መዝሙሮችን መዘመር (ዕብ. 13:15)፣ የተቸገሩትን ወይም ወንጌል የሚሰብኩትን መርዳት (ዕብ. 13:16)፣ ወዘተ. . . ነው:: አምልኮአችን በካህናት አማካኝነት የሚካሄድ ሳይሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በቀጥታ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ነው:: ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያን ያጌጡ የአምልኮ ሥርዓቶች ወይም ውጫዊ የአምልኮ ዕቃዎች ላይ ትኩረት ማድረግ የለባትም:: ነገር ግን ልባችንንና ሕይወታችንን በማዘጋጀት የምናደርገው ሁሉ ለእርሱ ክብርንና ደስታን እንዲያመጣ ዘላለማዊውን አምላክ እናመልካለን::

ሰ. በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ለተወሰኑ ሰዎች ለተወሰኑ ጊዜያት ብቻ ይሰጥ ነበር:: ካህናት፣ ነገሥታትና ነቢያት

አንዳንድ ጊዜ በመሪነት አገልግሎታቸው አገዛውን ያገኛሉ:: ተራ ሰዎች ግን ይህ በረከት አልነበራቸውም:: ነቢያት መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ሁሉ የሚሰጥበትን ዘመን በናፍቆት ይጠባበቁ ነበር (ኢዩ. 2:28-29):: መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ተለውጠው እንዲታዘዙ ይረዳቸዋል::

በበዓለ ኀምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በ120ዎቹ ደቀ መዛሙርት ላይ ወረደ:: እነዚህ ወንዶችና ሴቶች፣ መሪዎችና ምእመናን ነበሩ:: ሐዋርያት አንድ አዲስ ነገር ወደ ምድር እንደ መጣ ተገነዘቡ:: ከእንግዲህ የሕዝቡ ታዛዥነትና ስኬት በቀዳሚነት በመሪዎች ላይ አይደገፍም ነበር:: እያንዳንዱ ሰው በልቡ መንፈስ ቅዱስ ይኖረው ነበር:: ይኸው መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ አማኝ ትክክለኛውን መንገድ በማስተማር በትክክለኛው መሥመር እንዲጓዝ ይረዳው ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ምን ማድረግ እንዳለብን ይነግረን ነበር::

ጴጥሮስ ድሆችና ስደት ለተጋረጠባቸው አይሁዶችና አሕዛብ ሲጽፍ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ምን ዓይነት ሰዎች እንደ ሆኑ አብራርቶላቸዋል:: አማኞቹ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕዝብ መሆናቸውን ተናግሯል - ዳርቻ የሌላቸው ሕዝብ ወይም አገር:: በተጨማሪም የንጉሥ ልጆች (የነገሥታት ንጉሥ የሆነው የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናቸው)፣ እንዲሁም እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚያገለግሉ ቅዱስ ካህናት መሆናቸውን አመልክቷል:: አማኞቹ በመንፈሳዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ ሕያው ድንጋዮች ነበሩ:: ቅዱስና የታዛዥነት ሕይወት በመኖር መንፈሳዊ ቤተ መቅደስ ይገነቡ ነበር:: የዚህም ቤተ መቅደስ ክብር ከሰሎሞን ቤተ መቅደስ ክብር ይልቃል:: ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሰዎች «እንግዶች» እና «መጻተኞችም» ነበሩ:: በምድር ላይ እስካሉ ድረስ፣ ከቤታቸው ገና አልደረሱም:: ርስታቸው በሰማይ ይጠብቃቸዋል:: ለጊዜው ግን መከራን መታገሥ አለባቸው::

የአዲስ ኪዳን አማኞች ራሳቸውን ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እኩል አድርገው ይመለከቱ ነበር:: ነገር ግን፣ እኛ እንደ አይሁዶቹ ሥጋዊ ሕዝብ ሳንሆን፣ «መንፈሳዊ» ሕዝብ በመሆናችን ከእነርሱ እንለያለን::



4ኛ ጥያቄ:- ኤፌ. 1:20-23፤ 2:19-22ን አንብብ:: እግዚአብሔር በታሪክና በቤተ ክርስቲያን ለሚያከናውናቸው ተግባራት እነዚህ ጥቅሶች ምን ያስተምራሉ?

2. ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ናት::

መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረገ አዲስ ኪዳን መሆኑን ያሳያል (1ኛ ቆሮ. 11:25፤ ዕብ. 8:7-13):: በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ከዓለም የተለዩትና የአማኞች ማኅበረሰብ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አካል ናቸው:: ይህ ማኅበረሰብ በምድር ላይ ኢየሱስ ክርስቶስን ይወክላል:: በኤፌሶን 1:20-23 ጳውሎስ እንዳብራራው፣ በእግዚአብሔር ታላቅ ዕቅድ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ በታላቅ ኃይል ከሞት ተነሥቷል:: ከዚያም ክርስቶስ በታላቅ ክብር በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡን አመልክቷል:: እግዚአብሔር አገዛዝን ለክርስቶስ ሰጥቶታል:: ክርስቶስ የአጽናፈ ዓለም ገዥ እንደ መሆኑ፣ በሰማይና በምድር ያሉትን ሁሉ ይቆጣጠራል:: ይህ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ሲባል የተደረገ መሆኑን ጳውሎስ ያብራራል::

ከእኛ እይታ አንጻር፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን፣ ወይም ቤተ እምነታችን፣ ወይም በዓለም ሁሉ ያሉ አማኞች የሚካተቱባት ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን አነስተኛና ደካማ፣ በዓለም የተሰደደችና በውስጧም ችግሮች ያሉባት ናት:: ችግሮችን በምንመለከትበት ጊዜ በቀላሉ ተስፋ ልንቆርጥ እንችላለን:: የእግዚአብሔር ዓላማ ግን ቤተ ክርስቲያንን መገንባት ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የሚገኙባት ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ልትጠፋ አትችልም (ማቴ. 16:18):: ቤተ ክርስቲያን እንከን እንደሌለው ነገር፣ እንደ ንጽሕት ሙሽራ ቅዱስና ንጹሕ ናት (2ኛ ቆሮ. 11:2፤ ኤፌ. 5:25-27፤ ራእይ 21:2):: ራእይ 21:9-26 ይህች ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ለዘላለም የሚኖርባት ውብ ከተማ እንደ ሆነች ያሳያል:: እግዚአብሔር በዘመናችን እያከናወነ

ያለው ታላቅ ሥራ ሰዎች ከየጎሳውና ብሔሩ ተጠርተው ምርጥ ሕዝቡ እንዲሆኑ መጥራት ነው::

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ:- ኤፌ. 1:9-10፤ 4:15-16፤ 5:23፤ ቈላ. 1:18ን አንብብ:: በእነዚህ ክፍሎች ክርስቶስ ምን ተብሎ ተጠራ? ይህ ምን ማለት ነው? ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ መሪዎች ባለን ግንዛቤ ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ምንድን ነው? |

3. የቤተ ክርስቲያን መሪ ክርስቶስ እንጂ፣ ሰዎች አይደሉም::

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጡት የተለመዱ ምሳሌዎች አንዱ አካል ነው:: የክርስቶስ አካል በአማኞች የተገነባ ነው:: አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉት፣ ብዙ አማኞች አሉ:: እነዚህ አማኞች ደግሞ የተለያዩ ስጦታዎችና አገልግሎቶች አሏቸው:: እነዚህ ስጦታዎች የተሰጧቸው በክርስቶስ ትእዛዝ ከመንፈስ ቅዱስ ነው:: አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም፣ አንድ ራስ ብቻ አለው:: የቤተ ክርስቲያን ራስ ወይም መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ሁሉንም አማኞችና ተግባሮቻቸውን ይቆጣጠራል፣ ይወስናል::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን እውነት ማወቃቸው በጣም አስፈላጊ ነው:: አዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን «ራስ» መሆናቸውን አያሳይም:: የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ለአማኞች ሁሉንም ዓይነት ውሳኔዎች መስጠታቸውን የሚያሳይ ነገር በአዲስ ኪዳን ውስጥ አናገኝም:: ይልቁንም፣ አዲስ ኪዳን አማኞች ራስ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን መከተላቸውንና እርሱም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንደሚመራቸው ያሳያል:: በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለውን የቀድሞይቱን ቤተ ክርስቲያን አሠራር በምንመለከትበት ጊዜ፣ ብዙውን ጊዜ አማኞቹ የሚያከናውኗቸውን ነገሮች የሚወስኑት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አለመሆናቸውን እንረዳለን:: ለምሳሌ፣ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ እንዲሄድ ወይም ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጋር እንዲነጋገር ያዘዙት በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሐዋርያት አልነበሩም:: መንፈስ ቅዱስ ነበር የት መሄድና ምን ማድረግ እንዳለበት የመራው:: ዓለምን በወንጌል የመድረስ ዕቅድ አውጥተው ጳውሎስና በርናባስ መጀመሪያ ወደ ቆጵሮስ፣ ከዚያም ወደ ገላትያ፣ በአሁኗ ዘመን



ቱርክ፣ ግሪክና ኢጣልያ እንዲሰብኩ ያደረጉት በኢየሩሳሌም የነበሩ መሪዎች አልነበሩም:: ነገር ግን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የት መሄድና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነግሯቸዋል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ስልት ሲነድፉ አንመለከትም:: ወንጌላውያንና መጋቢዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያስረዱ ዝርዝር ትእዛዛትንም ሲሰጡ አንመለከትም::

ይህ መሪዎች ሰዎችን ከሚቆጣጠሩበት የብሉይ ኪዳን አሠራር እጅግ የተለየ የሆነው ለምንድን ነው? የአዲስ ኪዳን አማኞች አንድ ነገር መለወጡን ተረድተዋል:: በአዲስ ኪዳን መሪዎች ከመንፈስ ቅዱስ እንዳች መልእክት ሰምተው ለተራው ሕዝብ የሚያዳርሱበት ሁኔታ አብቅቷል:: የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እያንዳንዱ አማኝ ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ተረድተው ነበር:: ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዱ አማኝ ምን ማድረግ እንዳለበት ይነግረዋል:: ራስን ሰምቶ ትእዛዛቱን መፈጸም የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ነበር::

ይህ እውነት ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥራ ምንድን ነው? መሪዎች አማኞች ራሳቸው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት እንደሚሰሙ ማስተማር፣ ነገሮች ከእግዚአብሔር መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል:: በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት በዚያ የሚከናወነው ከእግዚአብሔር የሆነ ነገር መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ወደ ሰማርያና በኋላ ወደ አንጾኪያ ወኪሎችን ሲልኩ እንመለከታለን (የሐዋ. 8:14-17):: እንደ ደኅንነት ባሉት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ክርክር በሚነሣበት ጊዜ፣ በጋራ ተ ቀምጠው የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመፈለግ ይሰባሰቡ ነበር (የሐዋ. 15):: የሐዋርያት ሥራ በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሐዋርያት ሕዝቡን ለመቆጣጠር አለመሞከራቸውን ያሳያል:: ራሳቸውን በሥልጣን ላይ የሚያስቀምጥና ሌሎችን ሁሉ ታዛዥ የሚያደርግ አስተዳደራዊ መዋቅር አላዘጋጁም:: ከዚህ ይልቅ፣ ትኩረት ያደ ረጉት አማኞች በቀጥታ እግዚአብሔርን ማዳመጥ ይችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃልና ጸሎት በማስተማሩ ላይ ነበር:: ሕዝቡ

የእግዚአብሔርን ቃል ካወቁና በጸሎት አማካኝነት በውስጣቸው ያለውን መንፈስ ቅዱስ ካዳመጡ፣ ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በግልም ሆነ በጋራ ሊመራቸውና ምን ሊያደርጉ እንደሚገባቸው ሊያሳያቸው እንደሚችል እርግጠኞች ነበሩ።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ:- ኢየሱስ የእያንዳንዱ አማኝ መሪ እንደ ሆነና እያንዳንዳችን የሚመራን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እንዳለን አጥብቀን ብናምን፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር እንዴት የሚለወጥ ይመስልሃል? |

አዲስ ኪዳን የሚያስተምረው ዛሬ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ከሚያስቡት በጣም የተለየ ነው። መሪዎች እንደ መሆናቸው፣ እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን በእኛ በኩል ይናገራል የሚል አሳብ አላቸው። እነዚህም መሪዎች ትልቁ ራስ በሆነው ክርስቶስ ሥር የሚገኙ «ትናንሽ ራሶች» ሆነዋል። ከዚህም የተነሣ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለመጀመር፣ ወጣ ብለው የምስክርነት አገልግሎት ለመስጠት፣ ወይም ድሆችን ለመርዳት የእነርሱን ፈቃድ እንዲጠይቁ ይፈልጋሉ። ሰዎች ለመሪነት ወደ እነርሱ እንዲመለከቱ ይሻሉ። ይህ ግን የቤተ ክርስቲያኑ ራስ ክርስቶስ ሳይሆን፣ ሰዎች መሆናቸውን ያሳያል። መሪዎች በምእመናን ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ይመራቸዋል የሚል እምነት የላቸውም። ነገር ግን፣ በመሪዎች ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ሁሉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያዝዛል ብለው ያስባሉ።

ከዚህ የተሳሳተ መረዳት የተነሣ፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃልና እንዴት መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰሙ፣ ወይም እንዴት እንደሚጸልዩና ኢየሱስ የሚላቸውን እንደሚሰሙ በማስተማር ላይ ማተኩሩን እየቀነሰ መጥቷል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጊዜያችንን ሁሉ የምናጠፋው ቤተ ክርስቲያንን በማስተዳደር፣ ሰዎችን ስለ ማደራጀት ውሳኔዎችን በመስጠት፣ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶች ዕቅዶች በማውጣት፣ ሰዎች አገልግሎት ሊጀምሩ እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ በመወሰን፣ ሰዎች ትዳር ሊመሠርቱ እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ በመወሰን፣ ወዘተ . . . ነው። ይህንን ለሁሉም



ምእመናን በጥሩ ሁኔታ ልናከናውን ስለማንችል፣ አብዛኞቹ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትጋት ሳይሳተፉ ይቀራሉ። እያንዳንዱ አማኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ሊያደርግ እንደሚገባ እንዲነግረው ከመጠየቅ ይልቅ፣ የመሪዎችን ትእዛዝ ይጠብቃል።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ቆሮ. 12:7-11፣ 27-31ን አንብብ። ሀ) መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም አማኞች ምን ይሰጣል? ለ) ስጦታዎችን ዘርዝር። ሐ) እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች ለምን ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ እንደ ሆኑ አብራራ። |

### 4. አማኞች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮች ናቸው።

በብሉይና አዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉት ዐበይት ልዩነቶች አንዱ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ሰዎች የተወሰኑ ጥቂት ቡድኖች ነበሩ። እንደ ንጉሥ በሚሊዮኖች ላይ ይነግሣል። ጥቂት ካህናት በብዙ አይሁዶች ፈንታ አምልኮውን ይመራሉ። አልፎ አልፎ እግዚአብሔር ነቢይ አስነሥቶ ለሕዝቡ መልእክቱን ያስተ ላልፋል። ይህ የሚሆነው በአብዛኛው ሕዝቡ ከእውነቱ በሚያፈነግጥበት ጊዜ ነው፡

ይህ ሁሉ ግን በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተ ለውጧል። አንድ ሰው በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ሁለት ወሳኝ ነገሮችን ያደርጋል። አንደኛ፣ መንፈስ ቅዱስ አዲሱን አማኝ «የክርስቶስ አካል» በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያኖራል። ሁለተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ አማኝ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ልዩ ስጦታ ይሰጣል። ጳውሎስ ይህንን የአገልግሎት ስጦታ ከአካል ክፍሎች ጋር ያነጻጽራል። እንደ አፍ (የማስተማርና የመስበክ ስጦታዎች) የሚያገለግሉ ሰዎች አሉ። እንደ እጅ (የመስጠት፣ የመርዳትና የማገዝ ስጦታዎች)፣ እንዲሁም እንደ እግር (የወንጌላዊነትና የሐዋርያነት ስጦታዎች) የሚያገለግሉ ወገኖች አሉ። ነገር ግን ማናቸውም ስጦታዎች «ራስን» አይመስሉም። ማናቸውም ስጦታዎች ሌሎች ክፍሎችን ሙሉ በሙሉ አይቆጣጠሩም። ይህ የክርስቶስ ኃላፊነት ነው።

በኤፌሶን 4:11-16፣ ጳውሎስ የተለያዩ ዓይነት የአመራር ስጦታ ዎችን ለሰዎች የሚሰጠው በቀዳሚነት ምእመናንን ለማስተማርና

የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ያካሂዱ ዘንድ ለማስታጠቅ መሆኑን ይናገራል:: ከብሉይ ኪዳን በተቃራኒ፣ መሪዎች በምእመናን ፈንታ አገልግሎትን ማካሄድ አያስፈልጋቸውም:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ብስለት ሊኖር የሚችለው የቤተ ክርስቲያን አባላት በክርስቶስ ፈንታ በዓለም ውስጥ እንዲያገለግሉ ካስተማርናቸው ነው::

> 8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች እያንዳንዱ አባል ማገልገል እንዳለበትና መሪዎች ደግሞ ምእመናንን ማሠልጠን እንዳለባቸው የሚያስረዳውን ይህንን እውነት ቢገነዘቡ አመራራቸው እንዴት እንደሚለወጥ ግለጽ:: ለ) ጳውሎስ ስለ መንፈሳዊ ስጦታ ያስተማረውን እውነት ተግባራዊ ለማድረግ የምእመናን አስተሳሰብ መለወጥ ያለበት እንዴት ነው?

የሚያሳዝነው ይህንን ጠቃሚ የአዲስ ኪዳን ትምህርት የሚረዱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን ብዙዎች አይደሉም:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥራውን የማከናወን ኃላፊነት የእኛው ነው ብለው ያስባሉ:: ስዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚያገለግሉ ወንጌላውያንን የምትቀጥረው:: ብዙ ምእመናን ለጎረቤቶቻቸው የመመስከርና ወደ ክርስቶስ የመምራት መብትና ኃላፊነት እንዳላቸው አያስቡም:: ምእመናንን ደቀ መዝሙር ለማድረግ ደግሞ መጋቢዎችን እንቀጥራለን:: ነገር ግን ራሳቸው ምእመናንን በማሠልጠን ይህንን ጠቃሚ ተግባር እንዲያከናውኑ ማድረግ ይቻል ነበር:: አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የሚያስቡት ክርስቲያን ማለት እሑድ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የሚያመልክ ሰው ነው ብለው ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ስጦታ እንደ ሰጣቸው ይዘነጋሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ምእመናንን በማሠልጠንና በማስታጠቅ የሚያሳልፉት ጊዜ ትንሽ ነው:: ትኩረት የሚያደርጉት በማደራጀትና አስተዳደራዊ ችግሮችን በመፍታቱ ጉዳይ ላይ ነው:: ከዚህ አንጻር አብያተ ክርስቲያኖቻችን ደካማ መሆናቸው አስገራሚ አይሆንም::

> 9ኛ ጥያቄ፡- ገላ. 3:26-28፣ ቈላ. 3:11ን አንብብ:: እነዚህ ጥቅሶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች እኩል ስለ መሆናቸው ምን ያስተምራሉ? ለ) እነዚህ ጥቅሶች ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድን ነው?



5. ሰዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኩል ናቸው::

ብሉይ ኪዳን በግልጽ የተደነገገ ተዋረድ እንደ ነበረው ቀደም ሲል ተመልክተናል:: ካህናት ከተራ ሌዋውያን በላይ አስፈላጊዎች ነበሩ፣ ሌዋውያን ደግሞ ከምእመናን በላይ አስፈላጊዎች ነበሩ:: አንዳንድ ጎሳዎችም ከሌሎች በላይ አስፈላጊዎች ነበሩ:: የይሁዳ ነገድ ከሮቤል ነገድ በላይ አስፈላጊ ነበር:: ሁስም አይሁዶች ደግሞ አይሁዳዊ ካልሆነው ሰው በላይ አስፈላጊዎች ነበሩ (በአዲስ ኪዳን ውስጥ አይሁዶች ያልሆኑ ሰዎች አሕዛብ ይባሉ ነበር::)

ጳውሎስ እንዳስተማረው፣ ከብሉይና አዲስ ኪዳን ልዩነቶች አንዱ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው ማኅበራዊ ተዋረድና ክፍፍል አሁን መወገዱ ነው:: ሰዎች ሁልጊዜም እኩል መሆናቸውን ማሰብ አለባቸው:: ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን:: ነገር ግን ሁላችንም በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባመንን ጊዜ ይቅርታ ተደርጎልናል:: ሁላችንም በእኩል ደረጃ የእግዚአብሔር ልጆች ነን:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁላችንም በእኩል ደረጃ አስፈላጊዎችና ዋጋ ያለን ነን:: ከእንግዲህ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት ሊኖር አይገባም:: በአይሁዶችና አሕዛብ መካከልም የጎሳ ልዩነት አይኖርም:: በተማሩ (ግሪኮች) እና ባልተማሩ ሰዎች መካከልም ልዩነት ሊኖር አይገባም:: በባሪያ አሳዳሪዎችና በባሮች መካከልም ልዩነት ሊኖር አይገባም:: ሁሉም አማኞች በእኩል ደረጃ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው:: ሁሉም በእግዚአብሔር ፈንታ የሚያገለግሉ ካህናት ናቸው:: ለሁሉም በእኩል ደረጃ መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶአቸዋል:: ይህ መንፈስ ቅዱስ ሁላችንንም ይመራል፣ ያስችላልም:: ስለዚህ ሁሉም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ ሊመረጡ ይችላሉ:: ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ ስለ ትምህርት፣ ኢኮኖሚ ወይም የጎሳ ጉዳይ የተገለጸ ነገር የለም:: እግዚአብሔርን የሚያሳስበው የአመራር መስፈርት ልባችን፣ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነትና መንፈሳዊ ብስለታችን ብቻ ነው::

በዘመናችን፣ ይህንን ጠቃሚ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ስመጣስ እየሞከርን እንገኛለን:: ሰዎች መሪ እንዲመርጡ በሚጠየቁበት ጊዜ፣ የተማረ ወይም ሀብታም ሰው እንዲመርጡ እንፈልጋለን:: (ከራስ ወዳድነታችን የተነሣ ሀብታም ሰው ከተመረጠ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ገንዘብ ይሰጣል ብለን ስለምናስብ::) ወይም ደግሞ የተከበረ ጎሳ አባላትን እንመርጣለን:: እንደ ሸክላ ሠሪ የተናቁትን ሰዎች ግን ለመምረጥ አንደፍርም:: ይህ ለቤተ ክርስቲያን መጥፎ ስም ያመጣል ብለን እንሰጋለን::

> 10ኛ ጥያቄ:- ሀ) በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እውነተኛ እኩልነት የሌለ በሚመስል ሁኔታ የምንመላለሰው እንዴት እንደ ሆነ አብራራ:: ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ የመሪነት መስፈርቶች ሳይሆን፣ ሰዎች በዓለማዊ መስፈርቶች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መመረጣቸውን የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ጥቀስ:: ሐ) እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሰጠን መስፈርት ይልቅ፣ በዓለማዊ መስፈርት ተጠቅመን ሰዎችን በምንመርጥበት ጊዜ የሚመጣው ውጤት ምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው እውነት ምን ያህል አፈንግጠናል! ዓለም የመሪን ግንዛቤያችንን እንዲለውጥ አድርገናል:: ከዚህም የተነሣ መንፈሳዊ ያልሆኑትን ምርጫዎቻችንን ውጤቶች እያጨድን ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎቻችንን እግዚአብሔር ባስተማረን መንፈሳዊ መመዘኛዎች መሠረት በማንመርጥበት ጊዜ፣ መሪዎቹ የበለጠ እውቅና ለማግኘት እርስ በርሳቸው ይጣላሉ:: ከድህነታቸው፣ ካለመማራቸውና ከተፈላጊው ጎሳ ባለመወለዳቸው ምክንያት ለአገልግሎት ሳይመረጡ የሚታለፉ ሰዎች ደግሞ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ነኝ ብለው ለማሰብ ይቸገራሉ:: እንዲህ ዓይነት ችግሮች እስካሉብን ድረስ በቤተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ሰላም ሊኖር አይችልም፤ እንደ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንም ዓለምን ለመለወጥ የሚያስችል ኃይል አይኖረንም:: ይህንን ችግር ለመፍታት ዓለማዊ መስፈርቶችን ትተን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሪነት ወደሚያስተምረው እውነት መመለስ አለብን::



## ሁለተኛ ቀን

ብዙዎቻችን የራሳችን የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ከሁሉም የተሻለ እንደ ሆነ እናስባለን:: (ማስታወሻ:- መዋቅር ስንል የተለያዩ ቤተ እምነቶች የቤተ ክርስቲያን አመራራቸውን የሚያደራጁበት መንገድ ማለታችን ነው:: በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ ቤተ ክርስቲያን በቄስ፣ በሽማግሌ ወይም በመጋቢ ልትመራ ትችላለች:: ነገር ግን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደረጃዎች ያሏቸው ቤተ እምነቶች አካል ናቸው:: የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ቤተ እምነታዊ መዋቅር አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን፣ ሲኖዶሶችን፣ አውራጃዎችንና ብሔራዊ ጽ/ቤትን ሊያካትት ይችላል::) ካቶሊክ ወይም ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ትክክለኛው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በጠበቀ የጳጳሳትና የቀሳውስት መዋቅር አማካኝነት አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ የሚቆጣጠር ነው ብለው ያስባሉ:: ሌሎች እንደ መካነ ኢየሱስ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ካህናት የሚሾሙበት ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት ብሔራዊ መዋቅር ከሁሉም የተሻለ ነው ብለው ያስባሉ:: እንደ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ያሉ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በበኩላቸው የተለያዩ ደረጃዎች ባሏቸው ሽማግሌዎች የሚመራ ብሔራዊ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ተመራጭነት እንዳለው ያምናሉ:: እንደ ሙሉ ወንጌል በአካባቢያዊ የአስተዳደር መዋቅር ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም አሉ:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በነጻነት የራሷን አገልግሎቶች እንድታካሂድ ይፈቅዳሉ::

> 11ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ እምነታችሁን መዋቅር አብራራ:: ለ) ከላይ ከተመለከቱት የአመራር መዋቅሮች የትኛውን ይከተላል? ሐ) የዚህ ዓይነት መዋቅር ጥቅሞች ምንድን ናቸው? መ) የዚህ ዓይነት መዋቅር ድክመቶችስ ምን ምንድን ናቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን የትኛውን አስተዳደራዊ መዋቅር መከተል እንዳለባት መመሪያ አይሰጥም:: ይህ ምናልባትም የትኛው መዋቅር በይበልጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው

ብለን እንዳንጨነቅ ሊያግዘን ይችላል። ይሁንና፣ መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች አመራርንና ይህም አመራር በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተ ዳደራዊ መዋቅር ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደሚያስከትል እንዲገነዘቡ ለማገዝ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ይሰጣል።

አብያተ ክርስቲያናት የቤተ ክርስቲያን መሪን ሚና በተመለከተ ም የተለያዩ ግንዛቤዎች አሏቸው። ካቶሊክ ወይም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሱን የምትመለከተው ቤተ ክርስቲያን ምን ልታምንና ልትለማመድ እንደሚገባት የመወሰን ሥልጣን እንዳለው መንፈሳዊ «ንጉሥ» ነው። ሌሎች እንደ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ያሉት ደግሞ ለአጥቢያ ካህናት ከካቶሊኮቹ ያነሰ ሥልጣን ይሰጣሉ። ይሁንና፣ ቅዱስ ቁርባን ለመስጠትና ጥምቀት ለማካሄድ ልዩ ሥልጣን እንደ ተሰጣቸው አገልጋዮች አድርገው ይመለከቷቸዋል። በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ መጋቢው ከሽማግሌዎች (እና ከዲያቆናት) ጋር አብሮ በመሥራት አገልግሎቱን ያበረክታል። በታሪካቸው ሽማግሌዎች መንፈሳዊ ምሪት እንዲሰጡ የሚያደርጉ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ወንጌላውያንና መጋቢዎች ካሉ፣ ከሽማግሌዎች ሥር የሚያገለግሉ ደመወዝተኛ ሠራተኞች ሆነው ተግባራቸውን ያከናውናሉ።

እዚህ ላይም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን አንዱን ዓይነት የመሪዎች ግንዛቤ ብቻ እንድትይዝ የመረጠ አይመስልም። ነገር ግን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት ራሳቸውን መመልከት እንዳለባቸው የሚያሳዩ አሳቦችን ይሰጣል። በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት በታሪክ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን የመሩትን የተለያዩ ሰዎች ታሪክ በመዳሰስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራርና መዋቅር ከመጽሐፍ ቅዱስና ከታሪክ ጠቃሚ ትምህርቶችን ለማግኘት እንሞክራለን።

## የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር መግቢያ

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ሳሙ. 8:1-22ን አንብቡ። ሀ) ሕዝቡ ለምን ነበር ንጉሥ የፈለጉት? ለ) ሳሙኤል ንጉሥ ምን ያደርግባችኋል አለ? ሐ) የዓለምን የአመራር ምሳሌነት ስለ መከተል ከዚህ ምን እንማራለን? |



የመሪነት ግንዛቤያችን ከሁለት ምንጮች እንደሚቀዳ ተ መልክተናል። አንደኛው ምንጭ ዓለም ነው። በ1ኛ ሳሙኤል ታሪክ ውስጥ፣ የእስራኤል ሕዝብ እንደ ሳሙኤል ባሉና «መሳፍንት» ተ ብለው በሚጠሩ ጊዜያዊ መሪዎች ለመመራት አለመፈለጉን እናነብባለን። ንጉሥን ነበር የፈለጉት። ንጉሥ የፈለጉት ደግሞ እንደ ሌሎች አገሮች ዓይነት የአመራር መዋቅር እንዲኖራቸው በመፈለጋቸው ነበር። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ንግሥና ሥር ከመኖር ይልቅ ንጉሥ እንዲገዛቸው በመጠየቃቸው፣ እግዚአብሔር የሰውን ንጉሥ በመምረጥ እርሱ ንጉሣቸው እንዳይሆን እንደ ናቁት ተናግሯል።

በዓለም ላይ ሁሉም ባህል መሪ ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት የየራሱ ግንዛቤ አለው። ይህ የአመራር ግንዛቤ ጠንካራ በመሆኑ፣ ሰዎች ይህንኑ አሳብ ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ። ለምሳሌ፣ በ1ኛ ሳሙኤል በእስራኤል አካባቢ የሚኖሩ አገሮች ሁሉ በንጉሥ ይገዙ ነበር። ንጉሡ ቀረጥ በመሰብሰብና አገሪቱን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ወታደሮች እንዲወጣጡ በማድረግ ሕዝቡን ይቆጣጠራል። ንጉሡ ሕዝቡ ምን ማመንና እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚወስን እምባገነን ነበር። የአገሪቱን ሕግጋት የሚያወጣው እርሱ ነው። ተራው ሰው በመንግሥትና በደንቦቹ ላይ ለውጥ ለማምጣት ብዙም መብቶችና ሥልጣን አልነበረውም። ይህ በአገራችን ውስጥ የነበረውን የኃይለ ሥላሴን አገዛዝ የሚመስል ነው።

በብዙ የአፍሪካ አገሮች ጎሳዎች በጎሳ አለቆች ይገዙ ነበር። ብዙውን ጊዜ ይህ አገዛዝ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ነበር። ከእነዚህ አለቆች መካከል አንዳንዶቹ እንደ ነገሥታት በሕዝቡ ላይ ፍጹማዊ አገዛዝ ነበራቸው። በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ የጎሳ አለቃውን የሚመክሩ ሽማግሌዎች ይኖራሉ። አለቃው አማካሪዎ ቹን ካልሰማ፣ በሌላ ይተካል። አለቃው አማካሪዎቹን ሰምቶ የሚሰጠው ውሳኔ ግን በሕዝቡ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። በብዙ መንገዶች ዛሬ በሽማግሌዎች የሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታ ጎሳዊ አገዛዝን የሚከተሉትን ይመስላል። እንደ ጎሳ አለቆች ሁሉ

«የተማሩ» ሽማግሌዎች ለሌሎች ምርጥ የሆነውን ነገር እንደሚያውቁ በማሰብ ተራው ሕዝብ ተግባራዊ የሚያደርጋቸውን ውሳኔዎች ይሰጣሉ።

ዘመናዊነት በአመራር ግንዛቤ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል። ዛሬ በምዕራቡ ዓለምና በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሕዝቡ ሁሉንም ነገር መወሰን አለበት የሚል አመለካከት አስከትሏል። በመሆኑም፣ መሪ ዎች ሕዝቡ የሚፈልገውን ነገር ለማወቅና ለመተግበር ይሞክራሉ። የአመራር ሥልጣን የሚወሰነው አንድ ግለሰብና አሳቦቹ ባገኙት የድምጽ ቁጥር ነው። ሰዎች ግለሰቡንና ለአገሪቱ የወጠናቸውን አሳቦች ካልወደዱ፣ ድምጽ በመንፈግ መሪ እንዳይሆን ያደርጋሉ።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፦ ሀ) «የንጉሥን»፣ የ«ጎሳ አለቃን»፣ የ«ዴሞክራሲን» ወይም የ«ኮሚኒስት» ዓይነት አመራር ብንከተል፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል ግለጽ። በአያንዳንዱ ምሳሌ ውሳኔዎችን የሚሰጠው ማን ይሆናል? በእነዚህ ውሳኔዎች ውስጥ የምእመናን ሚና ምን ይሆናል? ለ) ከእነዚህ የአመራር ዓይነቶች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ በብዛት የሚታየው የትኛው ነው? |

የዓለምን የአመራር ዓይነት የፈለገችውን የእስራኤልን ምሳሌነት መከተሉ ለቤተ ክርስቲያን ቀላል ነው። ብዙውን ጊዜ የዓለምን የመሪነት ግንዛቤ እንቀዳለን። የአመራር መዋቅሮችንም ከዓለም እንቀዳለን። ስለዚህ፣ አምባገን መሪ ካለበት ማኅበረሰብ ከመጣን፣ ጠንካራ መሪን የሚሾም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር እንመርጣለን። ጎሳዊ መዋቅርን የለመድን እንደ ሆነ፣ ጠንካራና ውሳኔዎችን ሁሉ የሚሰጥ የ«ጎሳ አለቃ-መሳይ» የቤተ ክርስቲያን መሪ እንፈልጋለን። ከዴሞክራሲያዊ አመራር ጋር የተላመድን ከሆነ ደግሞ፣ ምእመናን በቤተ ክርስቲያኒቱ ውሳኔዎች ውስጥ ድምጽ የሚሰጡበትን አመራር እንፈልጋለን።

ይሁንና፣ መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን አመራር ከዓለማዊ አመራር የተለየ መሆኑን ይናገራል (ማቴ. 20:25-28)። ስለዚህ እነዚህን የአመራር ዓይነቶች ላለመከተል ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን ዝም ብለው የሚታዘዟቸውን ትእዛዛት የሚሰጡ ነገሥታት አይደሉም። ንጉሡ እግዚአብሔር



ብቻ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ሕዝቡ በድምጽ ብልጫ ደስ ያለውን ነገር የሚወስንበተን ዴሞክራሲያዊ አሠራርም መከተል የለበትም። እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ልንመርጥ ወይም ደግሞ ካልወደድነው ሌላውን ልንመርጥ አንችልም። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንደ ጎሳ አለቆች እየተሰባሰቡ ምእመናን የሚፈጽሟቸውን ውሳኔዎች ይሰጣሉ። ከእነዚህ የጎሳ አለቆች ወይም ሽማግሌዎች አንዱ መሆን እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ሰዎች ከዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ነገሮችን ያዛባሉ፤ ከቦታው ላይ የደ ረሱም ላለመውረድ ሲሉ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ሽማግሌነት የሚያመጣው ሥልጣንና ክብር እጅግ ደስ ያሰኛቸዋል። የቤተ ክርስቲያን አመራር አገራችን ከምትተዳደርበት ፖለቲካዊ አመራር ጋር አንድ ዓይነት ነው ብለን ከማሰብ ይልቅ፣ ፊታችንን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ፣ በተለይም ወደ አዲስ ኪዳን መመለስ ይኖርብናል። በዚያ ስለ አመራርና አስተዳደራዊ መዋቅሮች የእግዚአብሔር አመለካከት ምን እንደ ሆነ ልንረዳ እንችላለን።

የቤተ ክርስቲያን አመራርን በምናጠናበት ጊዜ፣ ሁለት የማይነጣጠሉ ነገሮችን ማሰብ አለብን። አንደኛ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዴት መደራጀት እንዳለባቸው እንደሚያስተምር ለመረዳት የአመራርን አስተዳደራዊ «መዋቅር» መመርመር አለብን። ሁለተኛ፣ መጽሐፍ ቅዱስ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ያህል የሥልጣን ደረጃ እንዳለውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል ስላለባቸው ልዩ ልዩ ዓይነት አገልጋዮች የሚናገረውን ማጥናት አለብን።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ምን ዓይነት መሪዎችና አስተዳደራዊ መዋቅሮች ሊኖሩን እንደሚገባ ለመረዳት፣ በታሪክ ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዴት እንደ ተመሩ መመርመሩ ጠቃሚ ነው። የቤተ ክርስቲያን አመራራችንን በዓለማዊ መጻሕፍት ላይ መመሥረት የለብንም። መሪያችን የእግዚአብሔር ቃል መሆን አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ አመራር ብዙ ትምህርቶችን እናገኛለን። እነዚህን ትምህርቶች ዛሬ ከቤተ ክርስቲያናችን ጋር ልናዛምድ እንችላለን። ዓለማዊ መጻሕፍትን መጠቀም ያለብን

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አመራር የሚናገረውን የሚደግፉ ሲሆኑ ብቻ ነው:: ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራርና የአስተዳደር መዋቅር በምናጠናበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን በታሪክ ሁሉ እንዴት እንደ መራው ለመመርመር ከብሉይ ኪዳን እንጀምራለን::

**የቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደራዊ መዋቅሮች ትምህርት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ (ክፍል 1 - ብሉይ ኪዳን)**

ብሉይ ኪዳን በቀዳሚነት አይሁዶች ስለ ተባሉት የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚናገር ነው:: ከአብርሃም ዘር ሕዝቡ ወደ ታላቅ አገርነት አደጉ:: ከዘፍጥረት 12 ጀምሮ፣ ብሉይ ኪዳን ስለ አይሁዶች ይናገራል:: እግዚአብሔር ከእነዚህ አይሁዶች ጋር ልዩ ቃል ኪዳን አድርጎ ነበር:: ነገር ግን ልምምዳችንን ሙሉ በሙሉ በብሉይ ኪዳን ላይ መመሥረት የለብንም:: ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው የአይሁዶች ሁኔታ በአዲስ ኪዳን ዘመን ካለችው ቤተ ክርስቲያን የተለየ ነው:: እስራኤል እካላዊ ዳርቻዎች፣ ወታደሮች፣ የቀረጥ አሰባሰብ፣ ፖለቲካዊ መሪዎች፣ ወዘተ. . . የነበሩባት አገር ነበረች (ኤፌ. 6:10-18):: የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመደገፍ ቀረጥ አንሰበስብም፣ በዘር የሚተላለፍ አገዛዝ አንከተልም፣ ወዘተ. . . :: ይህ ማለት አመራርን ከእስራኤል ብቻ ሳይሆን፣ ከቤተ ክርስቲያንም አንጻር መመልከት እንዳለብን ያሳያል::

1. አመራር ከአዳም እስከ ዮሴፍ:-

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ:- ሀ) በዚህ ጊዜ ውስጥ የነበሩትን ዐበይት መንፈሳዊ መሪዎች ስም ዘርዝር:: ለ) እነዚህ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሚመሩት ማንን ነበር? |

ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስራኤል እስከ ተመሠረተችበት ጊዜ ድረስ ለብዙ ሺህ ዓመታት፣ መንፈሳዊ አመራር በሩቅ ዘመዶች ላይ ነበር ያረፈው:: አባት የቤተሰቡ ራስ እንደ መሆኑ መጠን፣ የሚስቱ፣ የልጆቹ፣ የአማቶቹና የእነርሱ ልጆች መሪ ነበር:: አባት ቤተሰቡ እግዚአብሔርን እንዲከተል የማድረግ ኃላፊነት ነበረበት:: የሩቅ ዘመዶቹ ጭምር የሚገኙበት ቤተሰቡ እውነተኛውን አምላክ እንዲከተሉ የማድረግ ኃላፊነት ነበረበት::



በአምልኮም ቤተሰቡን የሚመራ ካህን ነበር:: ለምሳሌ፣ ኖኅ ቤተሰቡን ወደ መርከቡ እየመራ ሲያስገባና የጥፋት ውኃው ካለቀ በኋላ መሥዋዕቶችን ሲሠዋላቸው እንመለከታለን (ዘፍጥ. 8:15-21):: በተመሳሳይ ሁኔታ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ የቤተ ሰቦቻቸው መንፈሳዊ መሪዎች ነበሩ:: ያዕቆብ ወደ ግብጽ በሄደ ጊዜ፣ የሩቅ ዘመዶቹን ጨምሮ 70 የቤተሰብ አባላት ነበሩት:: ፓትርያርክ እንደ መሆኑ መጠን፣ ያዕቆብ ለሁሉም መንፈሳዊ መሪ ነበር::

የዚህ ዓይነት መንፈሳዊ አመራር አብቅቶ ይሆን? ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሌሎች ዓይነት መንፈሳዊ መሪዎችን ቢያዘጋጅም፣ ባል በቤተሰበ ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን ያለው መሆኑ አሁንም ቢሆን እጅግ መሠረታዊና አስፈላጊ የመንፈሳዊ አመራር ዓይነት ነው:: እያንዳንዱ አባወራ ለቤተሰቡ የእግዚአብሔርን እውነት ማስተማር አለበት:: ቤተሰቡ እንዴት እውነተኛ አምላክ እንዲያመልክ የማገዝ ኃላፊነት አለበት:: ይህ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:4-5 ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ሰው ቤተሰቡን በመንፈሳዊ መንገድ የማይመራ ከሆነ፣ ብቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የመሆን ብቃት እንደሌለው አመልክቷል::

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር አንድ ሰው ለቤተሰቡ መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ካልቻለ ሽማግሌ የመሆን ብቃት የለውም የሚለው ለምንድን ነው? ለ) በኢትዮጵያ ክርስቲያን ባሎች በቤታቸው መልካም መንፈሳዊ መሪዎች ይመስሉሃል? መልስህን አብራራ:: ሐ) ይህ የቤተሰብ አመራር ዛሬ ቸል የሚባለው እንዴት ነው? ይህ የመንፈሳዊ አመራር አለመኖር የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው? መ) አንድ አባወራ ለቤተሰቡ መንፈሳዊ ምሪት ለመስጠት ሊያደርጋቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? |

አንድ አባወራ በቤተሰቡ ላይ ያለው መንፈሳዊ ሥልጣን በብዙ መንገዶች እየተሸረሸረ በመሄድ ላይ ይገኛል::

በመጀመሪያ፣ በብዙ ቤተሰቦች ባል ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ሲል በዓመቱ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ከቤተሰቡ ተለይቶ ይኖራል:: አንዳንድ ባሎችና ሚስቶች በሥራ ምክንያት በተለያዩ ከተሞች ውስጥ ይኖራሉ:: አንዳንድ ወንጌላውያን ቤተሰቦቻቸውን ትተው

ለአገልግሎት ወደ ሌሎች አካባቢዎች ይሄዳሉ:: አንድ አባት ከቤተሰቡ ጋር ካልኖረ፣ ለቤተሰቡ መንፈሳዊ መሪ ሊሆን አይችልም:: አባት ከእምነቱ ካፈነገጠ፣ እግዚአብሔር በኃላፊነት ይጠይቀዋል:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው ቤተሰቡን እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እየመራ ስላልሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የመሆን ብቃት የለውም::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ከዓለም የባልን የመንፈሳዊ መሪነት ሥልጣን የሚቀናቀን ጠንካራ ውጥረት አለ:: ዓለም ወንድና ሴት እኩል ናቸው ትላለች:: አንዳንድ ክርስቲያኖችም ይህንን ተከትለው ባልና ሚስት በቤተሰብ ውስጥ እኩል መንፈሳዊ ሥልጣን እንዳላቸው ይናገራሉ:: በእርግጥ፣ ወንድና ሴት በእግዚአብሔር ዓይንና በቤተ ክርስቲያን እኩል ዋጋ አላቸው (ገላ. 3:28):: ባሎች ሚስቶቻቸው ምንም ነገር እንደማያውቁ ወይም ዝም ብለው ብቻ እንዲታዘዙ ከመጠበቅ ይልቅ፣ በቤተሰብ ውስጥ ባልና መሪ መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በትክክል መረዳት አለባቸው:: ሴቶች በእግዚአብሔር ፊት ማን እንደ ሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት መገንዘብ አለባቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶችም ልክ እንደ ወንዶች በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል ብሎ ያስተምራል (ዘፍጥ. 1:26-27):: የመጀመሪያዋ ሴት የተፈጠረችው የወንዱ እኩል አጋር እንድትሆን ነበር:: ይህ ሁለት በሬዎች አብረው በመጠመድ ከሚታረሱበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው (ዘፍጥ. 2:18):: ሴቶች ለእግዚአብሔር ክብር ሊጠቀሙ የሚችሏቸው መንፈሳዊ ስጦታዎችም አሏቸው (1ኛ ቆሮ. *12:7-11*):: ስለዚህ፣ ባሎች የቤተሰቡ መንፈሳዊ መሪዎች ናቸው ሲባል ሚስቶቻቸው ምንም ነገር እንደማያውቁ በማሰብ የፈለጉትን ሁሉ እንዲያደርጉላቸው ማዘዝ የለባቸውም:: ጳውሎስና ጴጥሮስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በወደደበት መንገድ ሚስቶቻቸውን ለማይወዱና ለሚበድሏቸው ባሎች ከባባድ ማስጠንቀቂያዎችን ሰጥተዋል:: (ኤፌ. 5:25-33፤ 1ኛ ጴጥ. 3:7ን አንብብ::) ለልጆች መንፈሳዊ እውነት በማስተማሩ በኩል ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር ተጋግዘው መሥራት አለባቸው:: ይሁንና፣ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ወንዶች የቤተሰቡ መንፈሳዊ መሪዎች



መሆን እንዳለባቸውና ልጆች የእግዚአብሔርን መንገድ መከተላቸውን ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ያስተምራል:: የዓለምን ፍልስፍና በመከተል ይህንን ጠቃሚ መንፈሳዊ መርሕ መዘንጋት የለብንም::

<u>ሦስተኛ</u>፣ ብዙ ወንዶች ቀን ሥራ ላይ ደክመው ስለሚገቡ፣ ለልጆች መንፈሳዊ አመራር መስጠት የሚስቶች ኃላፊነት እንደ ሆነ ያስባሉ:: ልጆቹን የማስተማሩን ኃላፊነት ለሚስቶቻቸው በውክልና ያስተላልፉላቸዋል:: ምንም እንኳን ሚስት ልጆቹ እግዚአብሔርን እንዲወዱ በማስተማሩ ረገድ ጠቃሚ ሚና ቢኖራትም፣ ይህ ግን ባል እግዚአብሔር የሰጠውን ኃላፊነት መተው አለበት ማለት አይደለም:: ባል ልጆች እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ጥረት በማድረጉ በኩል ተሳትፎ የማያደርግ ከሆነ፣ ብዙ ልጆች ጤናማ ቤተሰብ ለመመሥረት የሚያስችል የወንዶች አገዛ ስለማያገኙ፣ ቤተ ክርስቲያን እየተዳከመች እንደምትሄድ ከታሪክ እንማራለን::

<u>አራተኛ</u>፣ ብዙ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ባሎችን ተክታ ለቤተሰቦች መንፈሳዊ አመራር እንድትሰጥ ይጠብቃሉ:: በዚህም ምክንያት፣ ብዙ ክርስቲያን ባሎችና ሚስቶች ልጆቻቸው ክርስቶስን እንዲያውቁትና እንዲከተሉት ከማስተማር ይቆጠባሉ:: አብረው በማምለክ የሚያሳልፉት ጊዜ ጥቂት ነው:: ልጆች ስለ እግዚአብሔር እንዲማሩ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ይልኳቸዋል:: ልጆች በጋራ የጸሎት ጊዜ በአምልኮ ውስጥ እንዲሳተፉ ይጠብቃሉ:: ልጆችን እግዚአብሔርን እንዲወዱና እንዲያከብሩ በማገዙ በኩል የሰንበት ትምህርት ቤትና ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ሚናዎችን ይጫወታሉ:: ነገር ግን፣ ይህ በቤት ውስጥ የሚካሄደውን የወላጆች ትምህርትና መንፈሳዊ ምሪት፣ እንዲሁም አምልኮ ሊተካ አይችልም::

16ኛ ጥያቄ:- ሀ) እነዚህና ሌሎችም በቤተሰብ ላይ የሚታዩ ውጥረቶች አባት ልጆቹን በመንፈሳዊ መንገድ እንዳያስተምር መሰናክል የሚፈጥሩት እንዴት ነው? ለ) ከዚህ የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ አሉታዊ ውጤቶች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) በቤት ውስጥ ተገቢውን መንፈሳዊ ምሪት ለመስጠት ባሎችና ሚስቶች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

እነዚህ ችግሮች ለቤተ ክርስቲያን አደገኞች ናቸው:: ቤተ ክርስቲያን በጠንካራ ቤተሰብ ላይ ትደገፋለች:: ነገር ግን ብዙ ቤተ ሰቦች ልጆቻቸው እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ተግተው አያስተምሩም:: ባሎችና ሚስቶች ሥራ ስለሚበዛባቸው፣ ሰቤተሰቦቻቸው መንፈሳዊ ምሪት ለመስጠት በቂ ጊዜና ጉልበት አይኖራቸውም:: ልጆች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከወላጆቻቸው ጋር ሳይሆን፣ እርስ በርሳቸው ወይም ከሌሎች ልጆች ጋር በመጫወት ሊሆን ይችላል:: ይህ ደግሞ በቂ ትምህርት ሳያገኙ እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል:: ቤተሰቦቻችን፣ አብያተ ክርስቲያኖቻችንና ማኅበረሰቦቻችን ቤተሰብ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እየተዳከመ መሆኑን ይገነዘባሉ::

እጅግ አስፈላጊውና መሠረታዊው የመንፈሳዊ አመራር ቦታ ቤት ነው:: እግዚአብሔር ባል ቤተሰቡን እንዲመራ፣ ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንገዶቹ እንዲያስተምር፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን በማምለኩ ረገድ እንዲመራቸው ኃላፊነት ሰጥቶታል:: በዚህ ደረጃ ያለው አመራር ለሌሎች አመራሮች ሁሉ መሠረታዊ ነው:: ይህ ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣ የእምልክ ስፍራ ነው:: የሚያሳዝነው፣ ክርስቲያን መሪዎችም ሳይቀሩ ይህንን የመሪነት ደረጃ ቸል ይላሉ:: በአመዛኙ የወንጌላውያንና የሽማግሌዎች ልጆች በማኅበረ ምእመናኑ ውስጥ ያልተቀጡና ዐመፀኞች ሆነው ይገኛሉ:: ይህ እነዚህ መሪዎች እግዚአብሔር ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስተምሩ የሰጣቸውን ቀዳሚ ኃላፊነት ቸል ማለታቸውን የሚያሳይ ነው::

2. አመራር ከሙሴ እስከ ንጉሥ ሳኦል:-

እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ አውጥቶ ተስፋ ወደ ተገባላቸው ምድር እንዲመራቸው በጠራው ጊዜ፣ ከብዙ ዓመታት በፊት ለአብርሃም ቃል የተገባለት ሕዝብ መፈጠር ጀመረ:: የያዕቆብ ቤተሰቦች የነበሩት አይሁዶች 12 ነገዶች ያሉት ሕዝብ ሆኑ:: በመጨረሻም፣ በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ሊኖሩ ቻሉ:: ከሙሴ እስከ ንጉሥ ሳኦል በነበሩት ዓመታት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት የተለያዩ ዓይነት መሪዎችን ተጠቅሟል::



ሀ. የጎሳ መሪዎች:- የእግዚአብሔር ሕዝብ እያደጉ መጥተው ወደ ጎሳና ብሔር ሲያድጉ፣ መንፈሳዊ አመራር ይለወጥና ይስፋፋ ጀመር:: በዘፍጥረት 12:2፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጆቹ ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ ቃል ገባለት:: ከያዕቆብ ሞት ጀምሮ እግዚአብሔር ሙሴን እስካስነሣበት ድረስ ባሉት 400 ዓመታት ውስጥ የአይሁዶች ቁጥር ከ1 ሚሊዮን አለፈ:: በዚህ ጊዜ ውስጥ የነበረው አመራር ምን እንደሚመስል ብዙም የምናውቀው ነገር የለም:: ይሁንና፣ አመራሩ የሚሰጠው በጎሳና ነገድ ይመስላል:: 12ቱ የእስራኤል ነገዶች የራሳቸው ጎሳዎች ነበሯቸው፣ ጎሳዎቹም በሽማግሌዎች ይመሩ ነበር:: እያንዳንዱ ጎሳ የየራሱ ቃል አቀባይ ወይም መሪ ነበረው:: የጎሳዎቹ ሽማግሌዎች እንዴት ይመረጡ እንደ ነበረ አናውቅም:: ምናልባትም አመራሩ የሚተላለፈው ለታላቅ ልጅ ሊሆን ይችላል:: (ለምሳሌ፣ የሌዊ ታላቅ ልጅ ጎሳውን ሲመራ ቆይቶ በሞተ ጊዜ አመራሩን ለታላቅ ልጁ አስተላልፎአል:: ለዚህ ነው የሌዊ ታላቅ ልጅ የነበረው አሮን ሊቀ ካህናት እንዲሆን የተመረጠው::) እንደ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ጎሳዊ ማንነት ለአይሁዶች በአብዛኛው ታሪካቸው ውስጥ ጎሳዊ ታማኝነት ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል:: እንደ ሳኦልና ዳዊት ያሉ ነገሥታት የገዙት ሊከተሏቸው በመረጡት ሰዎች ላይ ነበር:: ሰዎች በንጉሡ ደስተኞች በማይሆኑበት ጊዜ አይከተሉትም:: የሰሎሞን ልጅ ሮብአም በነገሠ ጊዜ ብዙ ሰዎች ይህንኑ ነበር ያደረጉት::

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይህ የሽማግሌዎች አመራር ለእስራኤል የአመራር መሠረት ሆነ:: እንደ ነገሥታት፣ ነቢያትና ካህናት ያሉ ሌሎች መሪዎች ቢኖሩም፣ ሁልጊዜም መሠረታዊ አመራር የሚሰጡ ሽማግሌዎች ነበሩ::

*17ኛ ጥያቄ:- ዘጸአ. 18:13-26ን አንብብ:: ሀ) የሙሴ አማት ሙሴ የአመራር ሸክሙን ለማቃለል ምን እንዲያደርግ መከረው? ለ) የእነዚህን ሽማግሌዎች መመዘኛዎች ዘርዝር:: ሐ) ምን ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር?*

እግዚአብሔር ሙሴን በጠራ ጊዜ የሽማግሌዎች የመሪነት መዋቅር በሁለት መንገዶች ተልወጠ።

እግዚአብሔር እስራኤል አስተዳደራዊ መዋቅር ለመጀመር የሽማግሌዎችና ወታደራዊ መዋቅሮችን እንድታዋህድ ረድቷታል። በእነዚህ መዋቅሮች የሚገኙ የመሪዎች ደረጃዎች ለሰዎች ሁሉ የቅርብ ክትትልና ምሪት ይሰጡ ነበር። የእነዚህ መሪዎች ቀዳሚ ተግባር አስተዳደራዊ ሥራዎችን ማከናወን ሳይሆን፣ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ማገዝ ነበር። ይህ መዋቅር አሥር፣ ኀምሳ፣ መቶ እና ሺህ ሰዎች የሚገኙባቸውን ቡድኖች ያካተተ ነበር። እነዚህ መሪዎች የተመረጡት በኀላዊ የሽምግልና መመዘኛ ሳይሆን (ለምሳሌ፣ ሥልጣኑ የተመሠረተው የመጀመሪያ ልጅ ወይም የተወሰነ ነገድ አባል በመሆን ላይ አልነበረም)፣ በመንፈሳዊ መመዘኛ ነበር የተመረጡት። የእግዚአብሔርን ቃልና ባሕርይ በማወቃቸውና ሰዎችን ያለ አድልዎ በማስተናገዳቸው ነበር። የዚህ ዓይነቱ አመራር አይሁዶች ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላም ይቀጥል አይቀጥል የምናውቀው ነገር የለም። ምክንያቱም ብሉይ ኪዳን ስለዚህ ጉዳይ የሚለው ነገር የለም። ምናልባትም አመራሩ ሳይቀጥል ቀርቶ ይሆናል።

ከዚህ የአመራር መዋቅር አንዳንድ ጠቃሚ ትምህርቶችን ልናገኝ እንችላለን። በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በቁጥር እየበዙ በሚሄዱበት ጊዜ፣ ሁሉም ሰው መንፈሳዊ ክትትል ይደረግለት ዘንድ አስተዳደራዊ መዋቅሩም መስፋት አለበት። አብያተ ክርስቲያኖቻችን በሚያድጉበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እያንዳንዱ አማኝ የቅርብ ክትትል ሊያገኝ የሚችልበትን መዋቅር መዘርጋት አለባቸው። ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት ልክ ሙሴ እንዳደረገው ማኅበረ ምእመኖቻቸውን በአነስተኛ ቡድኖች ቢከፋፍሉ፣ እያንዳንዱን አማኝ በመንፈሳዊ እድገቱ መርዳት ይቻላል።

ሁለተኛ፣ መዋቅሩ መዘጋጀት ያለበት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማስተዳደር ሳይሆን፣ የቅርብ መንፈሳዊ ክትትል ለማድረግ ሊሆን ይገባል። ማስተዳደር ከመንፈሳዊ እንክብካቤ ያነሰ ጠቀሜታ ነው



ያለው። ይሁን እንጂ፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን አብዛኞቹ መዋቅሮቻችን በአስተዳደር ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ብዙ ሽማግሌዎች የምእመኖቻቸውን ስም እንኳን አያውቁም። እያንዳንዱ ምእመን በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ ስለ መሆኑ ወይም ስላለመሆኑ የሚያውቁት ነገር የላቸውም። ይህ በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ከሚታዩት ታላላቅ ድክመቶች አንዱ ነው።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ወደ ቤተ ክርስቲያናችሁ ለአምልኮ የሚመጣ እያንዳንዱ ሰው መንፈሳዊ ክትትል እንዲያገኝ የሚያስችልና በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ አገዛ የሚደርግ አንድ የመንፈሳዊ ክትትል መዋቅር አዘጋጅ። ለ) ይህ አሁን በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ካለው መዋቅር እንዴት እንደሚለይ ግለጽ። |

ሽማግሌዎች ስእግዚአብሔር ሕዝብ ክትትል ያደርጋሉ። እነዚህ 70 የበላይ መሪዎች ከሙሴ ጋር አብረው በመሥራት ለሕዝቡ አመራር ይሰጡ ነበር (ዘጸአ. 24:1)። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ግማሽ መንገድ ያህል ወደ ተራራው እንዲወጡ ጠይቆአቸው ነበር። በኋላም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሱን በመስጠት የሰባዎቹን ሽማግሌዎች አመራር አጸና (ዘኁል. 11)።

አይሁዶቹ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ፣ እነዚህ 70 ሽማግሌዎች በከነዓን አገር በፖለቲካው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መሪዎች ሆኑ። በአዲስ ኪዳን የእነዚህ ሽማግሌዎች ቡድን ሸንጎ (ሳንሀድሪን) በመባል ይታወቃል (ማቴ. 26:59)። ከመጀመሪያዎቹ ሰባ ሽማግሌዎች በኋላ እነዚህኞቹ ስባ ሽማግሌዎች እንዴት እንደ ተመረጡ አይታወቅም። ምናልባትም እነዚህ ሰዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ በጥበባቸው የታወቁ በመሆናቸው፣ ሰዎች ለእርዳታ ወደ እነርሱ ይሄዱ የነበረ ይመስላል። ሌሎች ሽማግሌዎችም ይህንን አይተው እንዲቀላቀሏቸው ጠየቋቸው። ምናልባትም ልክ እንደ ወታደራዊ አሠራር ከአሥር አለቅነት ወደ ኀምሳ አለቅነት፣ ከዚያም ወደ መቶ አስቅነትና ሺህ አለቅነት እየተዘዋወሩ የሠሩ ይመስላል። ይህም የሆነው ሰዎች ጥበባቸውን፣ ብስለታቸውንና የአመራር ክህሎቶቻቸውን በማጤናቸው ሳይሆን አይቀርም።

ነገር ግን በአገሪቱ ሁሉ ውስጥ ማኅበረሰቦችን ሁሉ የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ነበሩ:: በሙሴ ሕግ ውስጥ፣ ሽማግሌዎች ክርክሮችን የሚዳኙበትና በከነዓን ለሚኖሩ አይሁዶች ዳኝነት የሚሰጡበት አስፈላጊ ሚና ተሰጥቷቸዋል (ዘዳግ. 19:12፤ 21:1-4):: የሽማግሌዎች አመራር በጣም አስፈላጊ ስለ ነበር፣ አያንዳንዱ ከተማ የራሱ የሆነ የሽማግሌዎች ቡድን ነበረው (መሳ. 8:14):: ብዙውን ጊዜ ክርክሮችን ለመዳኘት በከተማው መግቢያ በር ላይ ይሰበሰቡ ነበር (ሩት 4:1-2):: የእስራኤል ሽማግሌዎች ወደ ሳሙኤል መጥተው ንጉሥ እንዲመርጥላቸው ጠየቁት (1ኛ ሳሙ. 8:4):: እርሱም የዳዊትን ንግሥና አጸና (2ኛ ሳሙ. 5:3):: እነዚህ ሽማግሌዎች በእስራኤል ታሪክ ሁሉ ከነገሥታት ጎን ለጎን አመራር ይሰጡ ነበር:: በምርኮ ዘመን ሳይቀር አይሁዶች በሽማግሌዎች ይመሩ ነበር (ሕዝ. 8:1)::

የዚህ ዓይነቱ የአመራር ዘዴ (የነገሥታት፣ የነቢያት፣ የካህናት) ለረዥም ጊዜ መቆየቱ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት የሽማግሌዎችን ዓይነት አመራር የሚመርጥ መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል:: በአዲስ ኪዳንም እንኳን፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አመራር ለመስጠት የተጠቀመው በሽማግሌዎች ነበር:: ሐዋርያት፣ ነቢያትና ወንጌላውያን ከቦታ ቦታ እየዞሩ የሚያገለግሉ ሲሆን፣ እነዚህ ሽማግሌዎች ነበሩ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በመሆን የሚያገለግሉት:: እነዚህ ሽማግሌዎች ከሕዝቡ ጋር ቅርበት ስላላቸው በሚገባ ያውቋቸው፣ ይመሯቸውና ችግሮች በሚደርሱባቸው ጊዜ ይረዷቸው ነበር:: በአንጻሩ፣ ነገሥታትና ሊቀ ካህናት ከሰዎችና ከችግሮቻቸው የራቁ ነበሩ:: ስለዚህ እነዚህ ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ሕዝብ አመራር ውስጥ አጅግ ጠቃሚ ደረጃ ነበራቸው::

> 19ኛ ጥያቄ:- የእስራኤልን ሽማግሌዎች ኃላፊነት ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ኃላፊነት ጋር አነጻጽር:: የሚለያዩትና የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ለ. <u>የሃይማኖት መሪዎች</u>:- በእስራኤል የነበሩት ሌሎች መሪዎች የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ:: እነዚህ «ካህናት» በመባል



የሚጠሩ መሪዎች ከሙሴ ዘመን ጀምሮ ቤተ መቅደሱ እስከ ተደመሰሰበት እስከ 70 ዓ.ም. ድረስ ቆይተዋል:: ሁሉም የሌዊ ነገድ አባላት ነበሩ:: ሁሉም የመጡት ከአሮን ጎሳ ነበር:: ከሌዊ ጎሳ የሆኑና ዳሩ ግን ከአሮን ወገን ያልሆኑ ሰዎች የተጠሩት ካህናት እንዲሆኑ ሳይሆን፣ የካህናት ረዳቶች እንዲሆኑ ነበር:: የአይሁዶች የሃይማኖት አመራር «ሊቀ ካህናት» ሆ በሚሠራ በአንድ ሰው ላይ ያረፈ ነበር:: ይህ ሥልጣን ከአሮን ወደ ታላቅ ልጁ እያለ በዘር የሚተላለፍ ነበር::

የካህናት አመራር የእስራኤልን አገር ሃይማኖታዊ ጉዳይ ብቻ የሚመለከት ነበር:: የአነርሱ ኃላፊነት ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነበር:: ይህም ሕዝቡ በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን እንዲጠብቁ ያስችላቸው ነበር (ዘሌዋ. 10:11):: በቤተ መቅደስ ውስጥም የእግዚአብሔርን አምልኮ ይመሩ ነበር:: የእንስሳት መሥዋዕት ያቀርቡና በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች ይንከባከቡ ነበር:: በኋላ ሌዋውያን ለአይሁዶች የመዝሙር አገልግሎት መስጠት ጀመሩ (1ኛ ዜና 25:6-31)::

ካህናት የፖለቲካ ሥልጣን አልነበራቸውም:: ይህ የፖለቲካ መሪዎችና የሽማግሌዎች ተግባር ነበር:: ካህናት ከፖለቲካው ገለል ብለው ለሁሉም የፖለቲካ መሪዎች መመሪያ መስጠት ያስፈልጋቸው ነበር:: ይህም መመሪያ እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር የገባውን ቃል ኪዳን የሚያንጸባርቅና የፖለቲካ መሪዎች በዚሁ ሕገ መንግሥት ተመርተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲመሩ የሚጠይቅ ነበር:: ካህናት እንደ ተቀሩት ሰዎች መሬት መያዝም ሆነ ንብረት ማፍራት አይፈቀድላቸውም ነበር:: በአንድ ከተማ ውስጥ ተቀምጠው በሚሰጣቸው አነስተኛ መሬት ላይ ያርሱ ነበር:: ዋናው ገቢያቸው የሚመጣው አይሁዶች ለእግዚአብሔር ከሚሰጡት አሥራት ነበር::

> 20ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከብሉይ ኪዳን ሃይማኖታዊ መሪዎች ልንማር የምንችላቸው አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አመራር ትምህርቶች ምን ምንድን ናቸው? ለ) በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል የሚታዩትን የሽማግሌዎች አመራር ልዩነቶች ግለጽ::

ክብሉይ ኪዳን የሃይማኖት መሪዎች አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮችን ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ልንማር እንችላለን::

1) በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የሃይማኖትና የፖለቲካ አመራርን በግልጽ ለይቷል:: እንደ ነገሥታት ያሉ የፖለቲካ መሪዎች የካህናትን ሥራዎች እንዲያከናውኑ አልተፈቀደላቸውም ነበር:: ለዚህ ነው እግዚአብሔር በሳኦል (1ኛ ሳሙ. 13:1-4) እና በዖዝያን (2ኛ ዜና 26:16-21) ላይ ፍርድን የሰጠው:: ካህናትም ቢሆኑ በፖለቲካዊ አመራር ውስጥ ገብተው እንዲሳተፉ አልተፈቀደላቸውም ነበር:: ይህ የሆነበት ምክንያት የሃይማኖት ሰዎች በፖለቲካ ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እውነታ ለፖለቲካው ጥቅም ሊለውጡ ስለሚችሉ ነው:: ይህ ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል ብዬ አምናለሁ:: በቀጥታ የፖለቲካ አመራር ኃላፊነት መያዝ የለብንም:: ይህንን የምናደርግ ከሆነ የቤተ ክርስቲያኑን አመራር መልቀቅ አለብን:: ፖለቲካ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የቅርብ ግንኙነት በሚመሠርትበት ጊዜ፣ በአመዛኙ የቤተ ክርስቲያን ንጽሕናና ምስክርነት እንደሚጎድፍ ከታሪክ እንረዳለን:: (ለምሳሌ፣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንንና የኢትዮጵያ ነገሥታትን፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንንና የሮም መንግሥትን ታሪክ መመልከት ይቻላል::) (ማስታወሻ:- ጠንካራ እምነት ያላቸውና የፖለቲካውን አመራር ፈተናዎች ሊቋቋሙ የሚችሉ ክርስቲያኖች በፖለቲካ ውስጥ ቢሳተፉ መልካም ነው:: ልክ እንደ ዳንኤልና ዮሴፍ እግዚአብሔር ክርስቲያን ፖለቲከኞችን በመጠቀም አገራቸው በይበልጥ እግዚአብሔር የሚፈልገውን የፍትሕና የጽድቅ መሥመር እንድትይዝ ያደርጋል::)

21ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ሽማግሌ የፖለቲካ አመራር ውስጥ በመግባቱ ምክንያት መሪነቱ የተበላሸበትን አጋጣሚ ጥቀስ:: ለ) በፖለቲካ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች በፖለቲካው እንዳይወሰዱ ምን ዓይነት ምክር ትሰጣቸዋለህ?

2) እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት ሁሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቀዳሚ አገልግሎት የእግዚአብሔርን ሕዝብ መንፈሳዊ



ፍላጎቶች ማሟላት ነው:: ልክ እንደ አዲስ ኪዳን ሐዋርያት፣ ሽማግሌዎች የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት በመምራቱ ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል:: (የሐዋ. 2:42፤ 6:2-4ን አንብብ::) ዋናው የአመራር መሣሪያቸው ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነው:: ለዚህ ነው ጳውሎስ ሽማግሌዎች ማስተማር መቻል አለባቸው ያለው (1ኛ ጢሞ. 3:2):: አማኞች እንደ እግዚአብሔር ትእዛዛትና መመሪያዎች እንዲኖሩ ማዘጋጀት አለብን:: ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማኅበረሰብ መንፈሳዊ አምልኮ መከታተል አለባቸው:: ሽማግሌዎች እንደ ልማት፣ ግንባታ፣ ወዘተ. . . በመሳሰሉት የአስተዳደር ሥራዎች በሚጠመዱበት ጊዜ፣ ለመንፈሳዊ ጉዳዮች ትኩረት ላይሰጡ ይችላሉ:: ሽማግሌዎች ለምእመናን በመጸለይና ቃሉን በማስተማር ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው መንፈሳዊ ጉዞ እንዲያድጉ የማገዝ ኃላፊነት አለባቸው:: ከዚህ አገልግሎት ሽማግሌዎችን የሚያደናቅፉ ሌሎች ሥራዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን የሚያዳክሙ ናቸው:: ሐዋርያት አስተዳዳሪዎች እንሆንም በማለታቸው ምን ያህል አስተዋዮች ነበሩ!

22ኛ ጥያቄ:- የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ከሆንክ፣ ከጊዜህ ምን ያህሉን መቶኛ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማርና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ትሰጣለህ? ምን ያህሉንስ ለአስተዳደራዊ ሥራዎች ታውላለህ? የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ካልሆንክ፣ በቤተ ክርስያናችሁ ውስጥ ላለ አንድ ሽማግሌ ይህንን ጥያቄ አቅርብ:: ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአስተዳደራዊ ሥራዎች ላይ በማተኮር የምእመኖቻቸውን መንፈሳዊ ሕይወት በማይከታተሉበት ጊዜ የሚከሰቱት ችግሮች ምን ምንድን ናቸው?

3) ብሉይ ኪዳን አባላት (ካህናት ያልሆኑ አይሁዶች) ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው መንፈሳዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ደፋ ቀና ለሚሉት ካህናትና ሌዋውያን የሚያስፈልገውን ነገር ለማድረግ አሥራት ማውጣት እንዳለባቸው ያስተምራል:: ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው የማስተማር፣ የስብከት፣ የጉብኝት፣ አዳዲስ አማኞችን ደቀ መዛሙርት የማድረግ፣ ወዘተ. . . አገልግሎት ለሚሰጡት ሰዎች ደመወዛቸውን ካልከፈልን፣ እነዚህ አገልጋዮች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት የመተዳደሪያ ገንዘብ ለማግኘት የተለያዩ

ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ጊዜ ምእመናንን ለማገልገል ብዙ ጊዜ አይኖራቸውም። በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ ሕዝቡ ካህናትን ለመደገፍ አሥራት በማይሰጡበት ጊዜ፣ ካህናቱ በግብርናና በንግድ ሥራ ላይ ስለሚሰማሩ፣ ሕዝቡን ለማስተማርና አምልኮውን ለመምራት ጊዜ ያጥራቸው ነበር። ይህ ደግሞ የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ይጎዳ ነበር (ነህ. 13:10-13)። አብያተ ክርስቲያኖቻችን ተዳክመው እንዲታዩ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ይሄ ይሆን? መንፈሳዊ ሰዎች መንፈሳዊ ፍላጎቶችን እንዲያሟሉ ዕድሉን አንሰጣቸውም፤ ለደመወዝ መክፈያ የሚሆን ገንዘብ እንዲኖር በቂ አሥራት አንሰጥም። ስለዚህ፣ አገልጋዮች እኛን ለማገልገል ሲሉ ትርፍ ጊዜያቸውን በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ያደርጋሉ። ጳውሎስ እንደሚለው የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ልምምድ ለአገልጋዮች ደመወዝ መክፈል ነው (ሉቃስ 10:7፤ 1ኛ ቆሮ. 9:9-12፤ 1ኛ ጢሞ. 5:17-18)። ሰዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው እንዲያገለግሉ ካልሾምንና እነርሱም አገልግሎታቸውን በሚያካሂዱበት ጊዜ ተገቢውን ደመወዝ እንዲያገኙ ካላደረግን፣ ራሳችንን እየጎዳን ነው። በምንታመምበት ጊዜ ለሚያክሙን ሐኪሞች ደመወዝ በመክፈሉ ቅር የሚለው ሰው የለም። «መንፈሳዊ ሐኪሞቻችን» እንክብካቤ እንዲያደርጉልን ደመወዝ ቢከፈላቸው ስምን ይከፋናል?

4) ነገር ግን በብሉይ ኪዳን መንፈሳዊ መሪዎች (ካህናት) እና በአዲስ ኪዳን መንፈሳዊ መሪዎች መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። የብሉይ ኪዳን አገልግሎት የሚሰጠው በተመረጡት አይሁዶች ሲሆን፣ አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ በሙሉ ካህናት መሆናቸውን ይናገራል። (1ኛ ጴጥ. 2:5፣ 9ን አንብብ።) አሁን መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ያድራል። እርሱ አማኞችን በማስተማር፣ ኃይልን በማላበስና መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን በመጠቀም አንዳችን ሌላውን እንድናገለግል ያስችለናል። ችግሩ፣ ቤተ ክርስቲያን «ልዩ» ናቸው የምትላቸው ሰዎች መንፈሳዊ መሪዎች እንዲሆኑ ታደርጋለች። እነዚህም ካህናት፣ ጳጳሳት፣ ሊቀ ጳጳሳት ወይም መጋቢዎች ናቸው። ይህ ደግሞ በአገልጋዮችና በምእመናን መካከል ልዩነት እንዲፈጠር ያደርጋል።



በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን እንዲህ ዓይነት ልዩነት አልነበረም። ሁሉም የእግዚአብሔር አገልጋዮች ተደርገው ነበር የሚታዩት። ሰዎች ለአገልግሎት የሚመረጡት በመንፈሳዊ ብስለታቸው እንጂ ልዩዎች ወይም ከሌሎች ሰዎች የተለዩ በመሆናቸው አልነበረም። ስለሆነም፣ በምእመናን ዘንድ ልዩ ተደርገው የሚታዩ አገልጋዮችን ላለመፍጠር ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ይህ ምእመናን ቁጭ ብለው እየተመለከቱ አገልጋዮቹ ሥራውን ለማካሄድ እንዲገደዱ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ከምንም ነገር በላይ ቤተ ክርስቲያንን ያዳክማል።

23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በምእመናን መንፈሳዊ ፍላጎቶች ላይ የሚያተኩር መንፈሳዊ አገልጋይ አስመኖሩ ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ የሚሆነው እንዴት ነው? ለእነዚህ አገልጋዮች በቂ ደመወዝ መክፈል አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) ጥቂት ሰዎች ብቻ እንዲያገለግሉ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ምእመናን ሁላችንም ካህናት ነን ብለን ማሰባችን ጠቃሚ የሚሆነው እንዴት ነው?

ሐ. <u>ጊዜያዊ የፖለቲካ/ወታደራዊ መሪዎች፡-</u>

24ኛ ጥያቄ፡- መሳ. 21:25ን አንብብ። ንጉሥ ባለመኖሩ ምክንያት በእስራኤል ምን ተከሰተ?

እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳኑን በመሠረተ ጊዜ፣ የእስራኤል «ንጉሥ» ተደርጎ እንደሚታይ ግልጽ ነበር። እንዲያውም ምሑራን የሲና ተራራው ቃል ኪዳን የአሕዛብ ነገሥታት ከማረኩአቸው ነገሥታት ጋር ቃል ኪዳን የሚገቡበትን መንገድ የተከተለ ነው ብለው ያምናሉ። ገዥው ንጉሥ የተሸናፊውን ንጉሥ ታማኝነትና ታዛዥነት ይወስን ነበር። በምላሹ ገዥው ንጉሥ ለደኅንነቱ ዋስትና ይሰጠዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ ነበር። እስራኤላውያን እርሱን ብቻ እስካመለኩትና ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እስከ ጠበቁ ድረስ እንደሚባርካቸው ተናግሯል። እስራኤላውያን የሰው ንጉሥ እንዲነግሥላቸው በጠየቁ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን አገዛዝ መቃወማቸው ነበር።

ሁሉንም አንድ የሚያደርግ አካላዊ የእስራኤል ንጉሥ ሳይኖር እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የሚነግሠው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ቀደም ሲል ሦስት ዓይነት መሪዎችን ሰጥቶአቸው ነበር። በመጀመሪያ፣ የቤተሰብ መሪዎች የሆኑት ባሎች ቤተሰቦቻቸው እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ የማድረግ ኃላፊነት ነበራቸው (ዘዳግ. 6:1-25)። ሁለተኛ፣ ሽማግሌዎች ነበሩ። እነዚህ መንፈሳዊና ጥበብ የሞላባቸው በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች በቤተሰቦች ወይም በጎሳዎች መካከል የሚከሰቱትን ችግሮች የመፍታት ኃላፊነት ነበራቸው። ሦስተኛ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን መባረኩንና መጠበቁን ይቀጥል ዘንድ ለሕዝቡ ቃል ኪዳኑን የሚያስተምሩ ካህናት ነበሩ። እነዚህ መሪዎች ተግባራቸውን በተገቢው መንገድ ከተወጡና ሕዝቡም ከታዘዘ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከውጭ ወራሪዎችና ከአደጋዎች ለመጠበቅ ቃል ገብቷል። ከዚህም የተነሣ ብሔራዊ መሪ አስፈላጊ አይሆንም። እግዚአብሔር በእነዚህ ሦስት ዓይነት መሪዎች አማካኝነት ንጉሣቸው ሆኖ ይሠራ ነበር።

ነገር ግን አንድ ችግር ቢፈጠርስ? ሠራዊትን ለውጊያ ማደራጀት ቢያስፈልግስ? እግዚአብሔር «መሳፍንት» የሚባሉትን ልዩ መሪዎች በመጥራት ሕዝቡን ለአጭር ጊዜ እንዲመሩ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ ሕዝቡ በግብጽ ባሪያዎች በሆኑ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ ተገልግሎበታል። ሕዝቡ ወደ ከነዓን መግባትና በዚያ የነበሩትን ሰዎች በማሸነፍ ምድሪቱን መቆጣጠር ባስፈለገው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን ጠርቷል። ኢያሱ ከሞተ በኋላ፣ እስራኤላውያን ቃል ኪዳኑን ባፈረሱ ጊዜ ሁሉ፣ ሕዝቡ ለሌሎች አገሮች እንዲገዙ ያደርግ ነበር። ንስሐ በሚገቡበት ጊዜ ደግሞ እንደ ጌዴዎን፣ ዮፍታሄ፣ ኤውድ፣ ሳምሶንና ሳሙኤል የመሳሰሉትን ወታደራዊ መሪዎች ያስነሣላቸው ነበር። እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ በሰዎች ፊት እርባና-ቢስ የሚመስሉትን ሰዎች በመምረጥ በመንፈስ ኃይልን ያሳብባቸው ነበር። ሕዝቡም ከሥራው እግዚአብሔር የመረጠው ሰው መሆኑን በመረዳት ይከተሉትና ይታዘዙት ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን ግለሰቡን ከተጠቀመ በኋላ፣ ግለሰቡ ለአገሪቱ እንደ አስተዋይ አማካሪ ያገለግል ነበር። ቀዳሚው የመሪነት ተግባር ግን በአባቶች፣



በሽማግሌዎችና በካህናት ላይ ያርፍ ነበር። መሪው ከሞተ በኋላ፣ እግዚአብሔር ሌላ ሰው እስኪያስነሣ ድረስ ሌላ ፈራጅ አይኖርም ነበር።

አባቶች፣ ሽማግሌዎችና ካህናት እግዚአብሔር የጠየቃቸውን ቀጣይነት ያለው አገልግሎት በማይሰጡበት ጊዜ ምን ይከሰት ነበር? ወላጆች ለልጆቻቸው ቃል ኪዳኑን ሳያስተምሩ ሲቀሩ፣ ሽማግሌዎች እግዚአብሔርንና ታላቅ ኃይሉን ሲዘነጉ፣ እንዲሁም ካህናት የእግዚአብሔርን ሕግ ለሕዝቡ ሳያስተምሩ ሲቀሩ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በፍጥነት ችግር ውስጥ ይገባ ነበር። በመጀመሪያ፣ አካባቢ እያንዳንዱ ሰው በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ስለሚያደርግ ማኅበረሰቡ የፈራረሰ ሕይወት ለመምራት ይገደዳል (መሳ. 21:25)። ከዚያም በጠላቶቻቸው ተሸንፈው ባሮች ይሆኑ ነበር።

25ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በዚህ የታሪካቸው ወቅት በፖለቲካዊ መልኩ ለመምራት ከፈለገበት መንገድ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ልንማር እንችላለን?

እስራኤላውያን በመሳፍንት የሚመሩበት ይህ የታሪካቸው ወቅት ዛሬ ለእኛ እያሌ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጠናል።

1) መሪዎች በቀላሉ እውነተኛው መሪ ማን እንደ ሆነ ሊዘነጉ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የምንመራው እኛው ነን ብለን እናስባለን። አንዳንድ መሪዎች፣ «እኛ እንወስናለን፣ እናንተ ሥራውን ትፈጽማላችሁ» ይላሉ። ብዙም ሳይቆይ ኃላፊነቱ የራሳቸው እንደ ሆነ አድርገው ይመራሉ። ይህንን በማድረጋቸው ደግሞ ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ራስ መሆኑን ይዘነጋሉ። ምእመናን የእርሱ እንጂ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም የቤተ እምነቱ አይደሉም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ራስ ሳለመሆን መጠንቀቅ አለብን። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የትኩረት ማዕከል በመሆን «ነገሥታት» ለመምሰል በሚሞክሩበት ጊዜ የኢየሱስን የመሪነት ስፍራ እየተቀናቀኑ ናቸው ማለት ነው። ከዚህ ይልቅ፣ ሕዝቡ ራሳችን የሆነውን ኢየሱስን እንዲያዳምጡ ማድረግ አለብን። ምእመናን

ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለማግኘት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይልቅ ወደ ኢየሱስ መመልከት አለባቸው።

2) እንዲሁም ደግሞ እያንዳንዱ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተግባሩን በአግባቡ በማይወጣበት ጊዜ፣ ችግሮች እንደሚፈጠሩ እንመለከታለን። ወላጆች ልጆቻቸውን ሳያስተምሩ ሲቀሩ፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን መንጋ ሳያስተ ምሩና በእረኝነት ሳያገለግሉ ሲቀሩ፣ ሕዝቡ ይዳከሙና በቀላሉ በጠላታቸው በሰይጣን ይጠቃሉ። ከዚያ በኋላ ሕዝቡ ኢየሱስ እንደሚፈልገው ሳይሆን ራሳቸው እንደሚፈልጉት ይኖራሉ። አብያተ ክርስቲያኖቻችን በሐሰተኛ ትምህርት፣ በክፍፍልና በሌ ሎችም ችግሮች እየዛሉ ያሉት መሪዎች እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ባለመምራታችን ሊሆን ይችላል።

3) ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን፣ እግዚአብሔር የፈለገውን ሰው ለመሪነት የመምረጥም ሆነ የመሾም መብት አለው። በመሪነት ላይ ያሉት ሰዎች ሕዝቡን እርሱ በሚፈልገው መንገድ በማይመሩበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ለውጥና ማዳን ለማምጣት ሲል ያልተጠበቁትን ሰዎች ለመሪነት ያስነሣል። ይህ ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የታየ ነገር ነው። ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሁኔታዋ በምታሽቆለቁልበት ጊዜ፣ ተሐድሶ ለማምጣት ወይም አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት አንድን ሰው ይጠራል። (ለምሳሌ፣ ሉተር የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን መሥራች ሲሆን፣ ካልቪን የፕረስቢቴሪያን [ቤተል ሲኖዶስ መካነ ኢየሱስ] ቤተ ክርስቲያን፣ ጆን ዌስሊ ደግሞ የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መሥራች መሆኑን ከታሪክ እናውቃለን።) እኛም በዘመናችን እርሱ እንደሚፈልገው አድርገን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት የማናገለግል ከሆነ እኛን አስወግዶ ሌሎች መሪዎችንና ቤተ እምነቶችን በማስነሣት ሥራውን ሊያከናውን ይችላል።

በመሪነት ላይ ያለን ሰዎች እግዚአብሔር የሚጠቀመው እኛኑ ብቻ ነው የሚል አቋም ሊኖረን አይገባም። እግዚአብሔር ለመሪነት ወይም ሕዝቡን ለማዳን ወይም በቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ሥራ ለማከናወን የፈለገውን ሰው ሊመርጥ እንደሚችል መረዳት



አለብን። በኢየሱስ ዘመን እንደ ነበሩት ፈሪሳውያን የሰማዩ አባታችን የፈለገውን ሰው እንዲጠቀም ካልፈለግን፣ መንፈስ ቅዱስን የምንቃወም የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ልንሆን እንችላለን። እንዲሁም ደግሞ ምእመናን ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ራሳቸውን ወይም ወዳጆቻቸውን ከመሪነት ላይ ለማስቀመጥ መጣራቸው ስሕተት ነው። ለአንድ መሪ ልጁን ከሥልጣን ላይ ስማስቀመጥ መጣሩ ትክክል አይደለም። ይህ እግዚአብሔር የፈለገውን ሰው እንዳይመርጥ የሚያደርግ መሰናክል ነው።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ዛሬ ሰዎች ከንጉሣችን ኢየሱስ በላይ በሰው መሪዎች ላይ የሚያተኩሩባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ። ለ) ሽማግሌዎች የማስተ ማርና የእረኝነትን አገልግሎታቸውን በማይወጡበት ጊዜ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱትን ችግሮች ግለጽ። ሐ) ብዙ ሽማግሌዎች የኢየሱስን የመሪነት ተግባር ለመንጠቅ የሚፈልጉት እንዴት ነው? መ) በሚገባ የተደራጁት መሪዎች ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የፈለገውን ሰው በመሪነት በመሾም ለውጥ እንዳያመጣ የሚከላከሉት ለምንድን ነው? |

## ሦስተኛ ቀን

### የቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደራዊ መዋቅር ትምህርቶች ከእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ (ትምህርት 2 - ብሉይ ኪዳን)

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንዴት እንዳደራጀ ተ መልክተናል። እርሱ ንጉሣቸው ነበር። የቤት ውስጥ አመራር የሚሰጡ «አባቶች»፣ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚሰጡ «ሽማግሌዎች» እና ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር፣ ብሎም በቤተ መቅደስ ውስጥ አምልኮውን በመቆጣጠር የሚሠሩ «ካህናት» የእግዚአብሔር ረዳቶች ሆነው ያገለግሉ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ችግር ሲፈጠር እግዚአብሔር አንድ ሰው ጊዜያዊ መሪ ሆኖ እንዲሠራ ያደርግ ነበር። ሳኦል የእስራኤል ንጉሥ በሆነ ጊዜ፣ አዲስ አመራር ተመሠረተ። ነገሥታት፣ ካህናትና ሽማግሌዎች ብልሹ ሕይወት በመምራታቸው እግዚአብሔር የ«ነቢያት»ን አገልግሎት አስፋፋ። ከዚህ አዲስ አመራር ምን እንማራለን?

3. ከንጉሥ ሳኦል እስከ ብሉይ ኪዳን ዘመን ፍጻሜ ድረስ የእግዚአብሔር ሕዝብ አመራር፡

| |
|---|
| 27ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ሳሙ. 8:1-9:27ን አንብብ:: ሀ) ሽማግሌዎች ሳሙኤል ምን እንዲያደርግ ጠየቁት? ለ) ያንን ዓይነት አመራር የፈለጉት ለምን ነበር? ሐ) ሳሙኤል ምን ዓይነት ምላሽ ሰጠ? መ) እግዚአብሔርስ ምን ዓይነት ምላሽ ሰጠ? ሠ) ሳሙኤል በለዚህ ዓይነቱ አመራር ምን ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሰጠ? ረ) ሳኦል የተመረጠበትን መሠረት በተመለከተ ታሪኩ ምን ያሳያል? የተገለጸው እንዴት ነበር? ሰ) ሆሴዕ 13:9-11ን አንብብ:: እግዚአብሔር እስራኤላውያን ንጉሥን በመጠየቃቸው ምን አለ? |

ሀ. <u>ነገሥታት</u>:- አንዳንድ ጊዜ በተሳሳተ ልባዊ ፍላጎት እግዚአብሔር አንድ ነገር እንዲያደርግልን በምንጠይቅበት ጊዜ፣ እርሱ የምንፈልገውን ነገር ሊሰጠን ይችላል:: ነገር ግን የምርጫችን መዘዞች እንዲደርሱብን ያደርጋል:: እስራኤላውያን እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሰጣቸው በጠየቁት ጊዜ ይህ ነበረ የሆነው:: የመጨረሻው መስፍን የነበረው ሳሙኤል ሲያረጅ፣ የእስራኤል ሽማግሌዎች ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ጠየቁት:: ለምን ነበረ ንጉሥ የፈለጉት? <u>በመጀመሪያ</u>፣ ሊያዩት በማይችሉት መሪ መመራቱ ስጋት አሳድሮባቸው ሊሆን ይችላል:: እግዚአብሔር የመሪነቱን ዙፋን ይዞ ችግሮች በሚፈጠሩበት ጊዜ፣ ጊዜያዊ መሪዎችን ማስነሣቱ ለብዙ ሰዎች ሊቀበሉት የሚቸግር ነገር ነበር:: ዛሬም ቢሆን በእምነት ለመኖርና እግዚአብሔር መሪያችን እንዲሆን መፍቀዱ ከባድ ሊሆንብን ይችላል:: ከዚህ ይልቅ፣ ሰዎች መፍትሔ እንዲሰጡን ማድረጉ ይቀላል:: ይሁን እንጂ፣ መፍትሔ ፍለጋ ወደ ሰዎች መሄዱ **በእግዚአብሔር** ላይ ማመፅ ነው:: እግዚአብሔር በዚህ **ጊዜ የደረሰበት ሐዘንን** ከ500 ዓመታት ያህል በኋላ ሕዝቡ አመራሩን በተቃወሙ ጊዜ በሆሴዕ ላይ ሲደርስ እንመለከታለን::

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ:- አማኞች ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ራስ መሆኑን በመዘንጋት ምሪት ለመቀበል በእምነት ወደ እርሱ ከመመልከት ይልቅ የሰዎችን መሪዎች መከተል ለምን እንደሚቀልላቸው ምሳሌዎችን ስጥ:: |

በሳሙኤል ዘመን እንደ ነበሩት አይሁዶች ሁሉ፣ እኛም ችግሮቻችንን ይፈቱልን ዘንድ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባሉት



ሰዎች ላይ ለመደገፍ እንፈተናለን:: ኢየሱስ ፍላጎታችንን እንዲያሟላልን ካልተደገፍንበት፣ በእርሱ ላይ እያመፅን ነው ማለት ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥንቃቄ ማድረግ ካለባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ምእመናን ለችግሮቻቸው ከሰዎች ይልቅ በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ማገዝ ነው:: ሰዎች መልስ ፍለጋ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መምጣታቸው የመሪዎችን የተፈላጊነት ስሜት ሊጨምር ቢችልም፣ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሰዎች ወዳለማመን፣ ብሎም በኢየሱስና በመንፈስ ቅዱስ አመራር ላይ እንዲያምፁ ሊያደርግ ይችላል:: ሰዎች እግዚአብሔርን ከመተማመን ይልቅ ወደ እኛ እንዲመጡ የምናበረታታ ከሆነ፣ አይሁዶች እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዳይሆን በተቃወሙ ጊዜ የፈጸሙትን ዓይነት ጥፋት እንፈጽማለን:: መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ይልቅ በሰዎችና በሥጋዊ ሀብት ላይ መደገፍን ይቃወማል:: (ኢሳ. 31:1-3ን አንብብ::)

አይሁዶች ንጉሥ የፈለጉበት <u>ሁለተኛው</u> ምክንያት በአካባቢያቸው እንዳሉት ሌሎች ሕዝቦች ለመሆን በመፈለጋቸው ነበር:: ሌሎች ንጉሥ ካላቸው፣ እኛስ ለምን ንጉሥ አይኖረንም? ሲሉ አሰቡ አይሁዶች:: ይህ ንጉሥ የሌላቸው ሕዝብ በመሆናቸው ምክንያት በሚያላግጡባቸው ሌሎች ሰዎች ፊት እንዲከበሩ ያደርጋቸዋል:: የተጨነቁት ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰዎች አሳብ ነበር:: ይህ በቤተ ክርስቲያንም ላይ የሚታይ ችግር ነው:: ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ለመፎካከር ብለን ትላልቅ ሕንጻዎችን ስንገነባ፣ በሙዚቃ መሣሪያዎች ላይ ብዙ ገንዘብ ስናፈስ፣ ወይም ሌሎችን ለመኮረጅ ብለን ታላላቅ የመዘምራን ቡድኖችን ስንመሠርት እንዲህ ዓይነት ችግር ውስጥ በመግባት ላይ ነን ማለት ነው:: አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በመንግሥት ለመመስገን ወይም ከእኛ የበለጠ ክብር አግኝተዋል ከሚሏቸው ሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር ለመፎካከር ሲሉ አስተዳደራዊ መዋቅሮቻቸውን ይቀይራሉ:: ነገር ግን ሌሎችን ከመኮረጅ ይልቅ ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ እግዚአብሔርን መጠየቁ አይሻልምን? እግዚአብሔር ከሚፈልገው በላይ በሌሎች ፊት «የበታች» መሆኑ የበለጠ ያስጋናል ማለት ነው?

29ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ከሚፈልገው ይልቅ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በሚያደርጓቸው ነገሮች ላይ ተ መሥርተው ውሳኔዎችን እንደሚሰጡ የሚያሳዩትን ምሳሌዎች ጥቀስ:: ለ) እንዲህ ዓይነቱ አመሰካከት በእግዚአብሔር ፊት ዐመፅ የሚሆነው ለምንድን ነው?

ሳሙኤል «ንጉሡ» ውድና ሕዝቡን የሚጨቁን አዲስ ቢሮክራሲያዊ አገዛዝ እንደሚጀምር ተረድቶ ነበር:: ቤተ መንግሥቶች፣ የጦር ሠራዊት፣ ወዘተ. . . ይመሠረታሉ:: ንጉሡም ብዙ ሀብት ለራሱ ለማጋበስ ይፈልጋል:: ይህ ገንዘብ የሚመጣው ከየት ነው? ሠራዊቱስ የሚመጣው ከየት ነው? ንጉሡ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያሟሉት ራሳቸው እስራኤ ላውያን ነበሩ:: እስራኤላውያን ንጉሥ በማግኘቱ ክብር ስለ ተ መሰጡ፣ ኪሳራውን ለማሰብ አልፈለጉም:: ሳሙኤል እንዳስጠነቀቀው፣ ንጉሥ አለን የሚለው ክብር የኋላ ኋላ ለአይሁዶች ሸክም ሆነባቸው:: ከ120 ዓመታት በኋላ ንጉሥ ሰለሞን ቤተ መቅደሱንና ታላላቅ ቤተ መንግሥቶቹን ለመገንባትና ለራሱም ሀብት ለመሰብሰብ ሲል ከሕዝቡ ብዙ ቀረጥ ከሰበሰበ በኋላ፣ ሕዝቡ ተዳከመ:: እርሱ ከሞተ በኋላ ልጁ ሮብዓም ቀረጡን እንዲቀንስላቸው ለመኑት:: ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ፣ ሽማግሌዎቹ በእርሱ ላይ በማመፃቸው አሥር ነገሥታት ኢዮርብዓምን ንጉሣቸው አድርገው ተከተሉት (1ኛ ነገሥ. 12:1-24)::

30ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሌሎችን የምታስደንቅና ለምእመናን ችግሮች ሁሉ መፍትሔ ለመስጠት የምትችል ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ስንል በምእመናን ላይ ሸክም የምንፈጥርባቸውን መንገዶች አብራራ:: ለ) ለምእመናን ቢሮክራሲያዊ መዋቅሩ ለመሸከም የሚከብድ ሲሆን ምን ይከሰታል?

ይህ ለእኛ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው:: ለምእመናን እንክብካቤ ለማድረግ ስንል ቢሮክራሲያዊ መዋቅሮችን በምንመሠርትበት ጊዜ፣ ታላላቅ ችግሮች ይፈጠራሉ:: በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አምስት ዓይነት የአመራር ደረጃዎች አሉ- አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ክፍለ ማኅበር፣ ክፍለ ማኅበራት ኅብረት፣ ቀጣና፣ ዋና ጽ/ቤት:: እያንዳንዱ ደረጃ የራሱ የሆነ ቢሮና ሠራተኛ ይፈልጋል::



ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመፎካከር ምርጥ ቢሮ፣ የሠለጠኑ ሠራተኞች፣ ምርጥ ሕንጻዎች፣ ወዘተ. . . የማግኘት ፈተናዎችም ይኖራሉ:: ለመሆኑ ለእነዚህ ሁሉ ሠራተኞችና መዋቅሮች የሚያስፈልገው ገንዘብ የሚመጣው ከየት ነው? ገንዘቡ የሚመጣው ከምእመናን ነው:: እነዚህ ምእመናን መሪዎቻቸው ሁልጊዜም ገንዘብ እንደሚጠይቋቸው ያስባሉ:: ከምእመናኖቻቸው ገንዘብ በመጠየቅ የታወቁ ቤተ እምነቶችም አሉ:: ስለሆነም ምእመናን ልክ እንደ እስራኤላውያን ሸክም በሆኑባቸው መዋቅሮች ላይ እንዳያምፁ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:: በርግጥ መሪዎች እንዲቀየሩ የግድ ላይሉ ይችላሉ:: ነገር ግን ሸክሙ ቀለል ብሎ ወደሚታይባቸው ቤተ እምነቶች በመፍለስ ሊያምፁ ይችላሉ:: ወይም ደግሞ ለሕይወታችን አስፈላጊ አይደለም ብለው ለሚያስቡት ተግባር ገንዘብ ሳይሰጡ በመወሰን ሊያምፁ ይችላሉ::

31ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ሳሙ. 16:1-13ን አንብብ:: ሀ) እግዚአብሔር አንድን መሪ የሚመርጥበት መንገድ ሰዎች ከሚመርጡበት መንገድ እንደሚለይ ሳሙኤል ምን ተማረ? ለ) ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር መመዘኛ ዎች ይልቅ የዓለምን መመዘኛዎች ተከትለው መሪዎችን እንደሚመርጡ የሚያሳዩትን ምሳሌዎች ስጥ:: ብዙውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ አመራር የሚያስከትለው ውጤት ምን ዓይነት ነው? ሐ) በእግዚአብሔር መመዘኛ መሠረት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የመምረጥን ጥቅሞች ዘርዝር:: ይህንን እውነት እንዴት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንደ ተመለከትክ ግለጽ::

የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት ፖለቲካዊ አመራር ከንጉሥ ሳኦል እስከ ንጉሥ ዘካርያስ ድረስ ለ500 ዓመታት ያህል ሲሠራበት ቆይቶአል:: ይሁዳ በተማረከ ጊዜ ነበር የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ያበቃው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መደበኛ አይሁዳውያን ነገሥታት አልታዩም:: ንጉሥ ሄሮድስ ከፊል አይሁዳዊ ብቻ ነበር፣ ከዳዊት ዘር ባለመወለዱም አይሁዶች እንደ እውነተኛ ንጉሣቸው አድርገው አልተመለከቱትም ነበር::

ነገሥታት የሰጡትን አመራር በምንመለከትበት ጊዜ፣ (ይህ 1ኛ ሳሙኤል፣ 2ኛ ሳሙኤል፣ 1ኛ ዜና፣ 2ኛ ዜና ውስጥ ተመልክቷል) ሁለት ጠቃሚ ትምህርቶችን እናገኛለን:-

1) የአመራሩ ውጤታማነት የሚወስነው በንጉሡ መንፈሳዊ ሕይወት ነበር:: እንደ ሳኦል ወይም ሮብዓም ያሉት ነገሥታት ራሳቸውን የእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋዮች አድርገው ባለመመልከታቸው፣ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ቀስቅሰዋል:: በፍጥነት ሕዝቡን ወደ ጣዖት አምልኮ መርተዋል:: ነገር ግን እንደ ዳዊት ያሉትን ሌሎች ነገሥታት እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ ተ ጠቀምባቸዋል:: እነዚህ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚወዱ መሪ ዎች ነበሩ:: በብዙ መንገዶች የንጉሡ መንፈሳዊ ሕይወትና ባሕርይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ታዛዥነት ይወስናል ልንል እንችላለን:: ዛሬም ቢሆን ምእመናን እግዚአብሔርን እንዲወዱና እርሱን በሚያስከብር መንገድ እንዲኖሩ የሚያደርገው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊ ባሕርይና እርሱን ለመታዘዝ መቁረጣቸው ነው:: እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዳስተማረው፣ ሰዎች ውጫዊ የአመራር ነገሮችን (ለምሳሌ፣ ትምህርት) በሚመለከቱበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መልካም የሚመስሉ መሪዎች ሊመረጡ ይችላሉ:: በኋላ ግን እነዚህ መሪዎች ሕዝቡን ከእግዚአብሔር በማራቅ ልክ እንደ ሳኦል በችግር ውስጥ ይዘፍቁታል:: ለሕዝቡ በ ረከት የሚያመጣ እንደ ዳዊት ያለ መንፈሳዊ መሪ ማግኘት የሚቻ ለው በመሪው ልብ፣ በመንፈሳዊ ባሕርዩና ለማገልገል ባለው ፍላጎት ላይ ትኩረት ሲደረግ ብቻ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ብዙ ክፍፍሎችና ሌሎችም ችግሮች እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆኑትን ሰዎች ያለመምረጣችን ውጤቶች ይሆኑ? የዘራነውን በማጨድ ላይ እንሆን ይሆን?

32ኛ ጥያቄ:- የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መንፈሳዊ ደረጃ የምእመናን መንፈሳዊ ደረጃ ሊወስን፣ በክፉም ሆነ በደግ፣ እንዴት እንዳየህ ግለጽ::

2) የምእመናንና የእብያተ ክርስቲያናት ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከጊዜ ወደ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት በሚዳከምባቸው ዑደቶች ውስጥ ማለፍ ነው:: ለምሳሌ፣ ዳዊት



እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ ይወድ ነበር:: ልጁ ሰሎሞን ግን ለሴቶችና ለሀብት ከፍተኛ ፍቅር ስለ ነበረው፣ እግዚአብሔርን በከፊል ልቡ ነበር የሚወደው:: በመጨረሻም የሰሎሞን ልጅ ኢዮርብዓም እግዚአብሔርን በመተው የራሱን ክብር ብቻ በመፈለጉ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉዳትን አስከትሏል:: በኋላም እግዚአብሔርም በሌላ ንጉሥ ሕይወት ታላቅ ሥራ በመሥራት እርሱን እንዲፈራው አደረገ:: እግዚአብሔር ንጉሡን ብቻ ሳይሆን የይሁዳን ሕዝብ ጭምር ነበር የሚባርከው:: ነገር ግን ልጁና የልጅ ልጁ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እየተዳከሙ ይሄዳሉ:: (ለምሳሌ፣ መንፈሳዊ መሪዎች በነበሩት እንደ ሕዝቅያስ፣ ያዝያንና ኢዮስያስ ያሉትን ነገሥታት መመልከት ይቻላል::) ይህ እውነት በእግዚአብሔር ሕዝብም ሕይወት ይታያል:: የእግዚአብሔር ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ ይሄዳል:: ከጥንቆላ ወይም ከታላቅ ኃጢአት የዳነው የመጀመሪያው ትውልድ እግዚአብሔርን ከልቡ በመውደድ በልበ ሙሉነት ያገለግለዋል:: ልጆቻቸው ግን (ሁለተኛ ትውልድ አማኞች) እምነታቸውን ባይተ ዉም፣ እግዚአብሔርን በመሥዋዕትነት ከማገልገል ይልቅ የራሳቸውን ፍላጎቶች ይከተላሉ:: ሦስተኛው ትውልድ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ወደ ዓለም ይመለሳል:: እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች በዓለም እንዳይዋጡ ታላቅ ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል:: ይህ ካልሆነ ግን፣ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር በታላቅ ኃይሉ የሠራባት ቤተ ክርስቲያን ትሞታለች:: ይህንን እንደ እንግሊዝ ባሉት አገሮች ውስጥ እንመለከታለን:: በእንግሊዝ በአንድ ወቅት ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩት፣ አሁን ልጆች የወላጆቻቸውን እምነት በመተ ዋቸው፣ በመስጊዶች ተተክተው ይታያሉ:: የእያንዳንዱ ቤተ እምነት መሪዎች የሁለተኛና ሦስተኛ ትውልድ አማኞችን ሕይወት በመመርመር በታላቅ ጸሎት ተሐድሶ ለማምጣት መጣር አለባቸው::

33ኛ ጥያቄ:- ከትውልድ ትውልድ የምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት እየተ ዳከመ ሲሄድ የተመለከትከው እንዴት ነው? ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ይህንን ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ለመቀልበስ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

ሰ. ነቢያት፦ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የመጨረሻው የመሪ ዓይነት ነቢያት የተሰኘው ነው። አብርሃምና ሌሎችም ሰዎች ነቢያት ቢባሉም፣ የነቢያት መደበኛ ሚና የታየው በሙሴ አገልግሎት ነው። አይሁዶች ሙሴን የነቢይ ምሳሌ አድርገው ይመለከቱት ነበር። እግዚአብሔር በቀጥታ ለዚህ አገልግሎት የጠራው ሲሆን፣ ሥራውም የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ ማዳረስ ነበር። ይህ መልእክት አልፎ አልፎ ወደፊት የሚከሰቱትን ነገሮች የሚያመለክት ቢሆንም (ለምሳሌ፣ ዘዳግ. 18:15)፣ ብዙውን ጊዜ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በሚያስከብርና የቃል ኪዳን ግዴታቸውን በሚያሟላ መንገድ እንዲኖሩ የሚቀሰቅስ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ልዩ ግንኙነት የተነሣ፣ ነቢያት «የእግዚአብሔር ሰው» ተብለው ይጠሩ ነበር (ለምሳሌ፣ 1ኛ ሳሙ. 2:27፤ 9:6፤ 1ኛ ነገሥ. 13:1)። ከይሁዳ ነገድና ከዳዊት የዘር ሐረግ ከመጡት ነገሥታትና ከሌዊና ከአሮን የቤተሰብ ሐረግ ከመጡት ካህናት በተቃራኒ፣ እግዚአብሔር ነቢያትን የጠራው ከብዙ የተለያዩ ጎሳዎችና ቤተሰቦች ነበር።

የነቢያት አመራር ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲለወጥ ቆይቶአል። እንደ ነቢይ ሳሙኤል ተቀባይነት የተሰጠው መንፈሳዊ መሪና አማካሪ ነበር። በሳሙኤል ዘመን የነቢያት ማኅበረሰብ ጎልብቷል (ለምሳሌ፣ 1ኛ ሳሙ. 19:20)። እነዚህ ነቢያት በእስራኤል ሁሉ እየዞሩ የእግዚአብሔርን ቃል እየተናገሩ አብረው ይኖሩ ነበር። እግዚአብሔር አንድን ነቢይ በሚጠራበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚናሩትን «ደቀ መዛሙርት» ይሰበስብ ነበር። እነዚህ ነቢያት በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ቆይተዋል። ቢያንስ እስከ ኤልያስና ኤልሳዕ (2ኛ ነገሥ. 2:3፣ 5) እና አሞጽ (7:14) ዘመን ድረስ።

በዳዊት ዘመን፣ ነቢያት ብዙውን ጊዜ የንጉሥ አማካሪዎች ነበሩ። ዳዊት ለሕይወቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቁን ለማረጋገጥ ፈልጎ ነበር። ስለሆነም በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ እንደ ናታንና ጋድ ያሉትን ነቢያት ይጠይቅ ነበር። በካህናት ዘመን እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው ነቢይ እንዲሆን ይጠራና ለንጉሡ



መልእክት እንዲያደርስ ይልከው ነበር። ይህንንም የሚያደርገው ብዙውን ጊዜ ንጉሡና ሕዝቡ ባስመታዘዛቸው ምክንያት ፍርድ እንደሚመጣባቸው በመግለጽ ነው (ለምሳሌ፣ 1ኛ ነገሥ. 11:29-39)። ብዙውን ጊዜ ግስሰቡ መልእክቱን ካደረሰ በኋላ፣ ወደ ቀድሞ ሥራው ይመለሳል።

የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት በእግዚአብሔር ላይ ማመፃቸውን በቀጠሉበት ወቅት፣ የነቢያት አገልግሎት እየተጠናከረ ይሄድ ጀመር። ኤልያስና ኤልሳዕ በሕይወት ዘመናቸው አብዛኛውን ጊዜ በነቢይነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ትልቁ አገልግሎታቸው ነገሥታትና ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ፈጸሙት ዐመፅ መጋፈጥና ስለሚመጣባቸው የእግዚአብሔር ፍርድ ማስጠንቀቅ ነበር። ኤልሳዕ ከሞተ በኋላ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡ ከኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡና ይህ ካልሆነ እግዚአብሔር በዘዳግም 11 ከነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚያፈርስ ለማስጠንቀቅ አያሌ ነቢያት አስነሥቷል። ከእነርሱ በፊት ከነበሩት ነቢያት በተቃራኒ፣ እነዚህ ነቢያት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበሉትን መልእክት በጽሑፍ በማስፈር ሕዝቡ እግዚአብሔር ለምን እንደ ቀጣቸው እንዲያውቅ አድርገዋል። እነዚህ መልእክቶቻቸውን በጽሑፍ ያሰፈሩ ነቢያት ከኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ የሚገኙት ናቸው።

እነዚህ ነቢያት በእስራኤል ሕዝብ አመራር ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ሃይማኖተኞች ወይም የፖለቲካ መሪዎች እንደ ሆኑ ደመወዝ ስለማይከፈላቸው፣ ተጠሪነታቸው ለእግዚአብሔር ብቻ ነበር። ስለዚህ ሥራዬን አጣለሁ የሚል ፍርሃት ሳይኖርባቸው የእግዚአብሔርን መልእክት በድፍረት ይናገሩ ነበር። ፖለቲከኞች ወይም ሃይማኖታዊ መሪዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል በማይመሩበት ጊዜ፣ ነቢያት ይጋፈጧቸውና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ያደፋፍሯቸው ነበር፤ ይህ ካልሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚደርስባቸው ያስጠነቅቁአቸው ነበር።

ነገር ግን ነቢያትም ትንቢታዊ አመራራቸውን አላግባብ የመጠቀም ፈተና ነበረባቸው። አንደኛ፣ ነቢያት ሳይሆኑ

የነቢይነትን ክብር የሚፈልጉ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ነቢይ ለመምሰል ይሞክሩ ነበር። እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት እግዚአብሔር ሳይናገራቸው ተናግሮናል ይሉ ነበር (ኤር. 5:31፤ 8:10-12፤ 14:13-16)። ከሰዎች ክብር ለማግኘት ብለው መልእክቶችን ይናገሩ ነበር። ወይም ደግሞ ክንቱ ሥራ ለማግኘት ማዕረጋቸውን ይጠቀሙ ነበር። ሁለተኛ፣ ሥራቸውን ሳለማጣት ሲሉ እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልእክት የለወጡ ነቢያት ነበሩ። ለምሳሌ፣ ስለሚመጣው ፍርድ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ይልቅ፣ ሁሉም ነገር ሰላም እንደሚሆን ይናገሩ ነበር (1ኛ ነገሥ. 22:1-18፤ ኤር. 14:13-16)። እነዚህ እግዚአብሔር ተናግሮናል እያሉ ሰዎች መስማት የሚፈልጓቸውን ነገሮች ብቻ የሚናገሩት ነቢያት የእውነተኛ ነቢያት ጸር ነበሩ።

34ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪ ተግባር ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) ዛሬ መሪዎች ሰዎችን ለማስደሰት ሲሉ የትንቢት ተግባራቸውን እንዴት ሊሰውጡ እንደሚችሉ ግለጽ።

ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ምሳሌዎች እያሌ ቁም ነገሮችን ልንማር እንችላለን።

1) እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕዝቡ በሙሉ ልባቸው እርሱን እንዳይከተሉ የሚያደርጉትን ነገሮች እንዲያስጠነቅቁ ይፈልጋል። የሚኖሩበትን ዘመን ማወቅ አለባቸው። የእግዚአብሔርንም ቃል ማወቅ አለባቸው። ሕዝቡ እውነተኛ ያልሆነ ትምህርት ሲቀበል ወይም ሥነ-ምግባራዊ ንጽሕናቸውን ሲያጡ፣ መሪዎች በድፍረት የእግዚአብሔርን እውነት መናገር አለባቸው። በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነት የማትረፍ ፍላጎታቸው ለዘመናቸው የእግዚአብሔርን እውነት በድፍረት እንዳይናገሩ ሊያደርጋቸው አይገባም። ነገር ግን ለእግዚአብሔር በሚኖሩበት ጊዜ፣ ሌሎች መሪዎችን ጨምሮ ሰዎች እንደሚቃወሟቸው መረዳት አለባቸው። እውነተኛ ነቢያት እውነትን በሚናገሩበት ጊዜ ይሰደዱ ነበር? (ማቴ. 5:11-12ን አንብብ።)



2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን ለማስደሰት ብለን እግዚአብሔር እንድንናገር የሚፈልገውን ነገር እንዳንለውጥ መጠንቀቅ አለብን። ሰዎች ስለማይወዱት ወይም ሌሎች ሰዎች ምን ይሉ ይሆን፧ በሚል ፍርሃት እውነቱን የማንናገር ከሆነ፣ የብሉይ ኪዳንን ሐሰተኛ ነቢያት መስለናል ማለት ነው። በተለይ የቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ሥራቸውን እንዳያጡ ሊፈሩ ይችላሉ።

3) እግዚአብሔር ነቢያትን የጠራው ከተለመዱት መሪዎች ውጭ ነው። ይህንን ባደረገ ጊዜ፣ ሌሎች መሪዎች አገልግሎታቸውን ይቃወሙ ነበር። እግዚአብሔር ለእኛ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ነው የሚናገረው የሚል አሳብ ካለን፣ እግዚአብሔር የጠራቸውንና መልእክት የሰጣቸውን ሌሎች ሰዎች ላንሰማ እንችላለን። እንዲያውም፣ ለእነዚህ ሰዎች የአገልግሎት በር በመዝጋትና ስማቸውን በማጥፋት ወይም ከቤተ ክርስቲያን እንዲባረሩ በማድረግ፣ ቀናተኛነታችንን ልናሳይ እንችላለን። ዛሬም እግዚአብሔር ሰዎችን ከተለመደው የመሪነት መዋቅር ውጭ በመጥራት አዲስ ሥራን ይሰጣቸዋል። እኛስ ለመስማት ፈቃደኞች ነን? ወይስ ሃይማኖተኞች በመሆን በሐዋርያት ሥራ 9:1-6 ሳውል እንዳደረገው ከእግዚአብሔር ጋር እንዋጋለን?

እግዚአብሔር በእነዚህ ነቢያት አማካኝነት፣ ሲመጣ ስላው አዲስ ቀን፣ ማለትም አዲስ ቃል ኪዳን ስለሚጀመርበት ቀን ተናግሯል (ኢዩ. 2:28-29፤ ኤር. 31:31-34)። ስብሉይ ኪዳን ቁልፍ መሪዎች ኃይልን የሰጠውና በነቢያት ውስጥ የሠራው መንፈስ ለእግዚአብሔር ተከታዮች ሁሉ ይሰጣል። ከዚህም የተነሣ፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት ይለወጣል። በእግዚአብሔር ሕዝብ አመራርም ላይ አንዳንድ ለውጦች ይደረጋሉ።

4. በብሉይ ኪዳን የሁሉም መሪዎች ኃላፊነት የእግዚአብሔር ሕዝብ እረኝነት ነበር።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ትልቅ የአመራር ጥያቄ አንድ ሰው መሪነት በመያዙ ላይ ሳይሆን፣ እንዴት እየመራ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው:: አይሁዶች አመራርን የቀዱት ከዓለም ነበር፣ ይህም የነገሥታት አመራር ነበር:: በተጨማሪም የመሪዎችን የአምባገነንነት‧ና አመራርን ለራስ ጥቅም የማዋልን ሁኔታዎችንም ጨምረው ቀድተው ይሆን? ወይስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመሩት በተለየ አመለካከት ነበር?

> 35ኛ ጥያቄ፡- መዝ. 23ን አንብብ:: ሀ) በዚህ መዝሙር ውስጥ እግዚአብሔር የተገለጸው እንዴት ነው? ለ) መዝሙረኛው እግዚአብሔር ለእኛ ስለሚያደርጋቸው ነገሮች የገለጻቸውን ተምሳሌታዊ ነገሮች ግለጽ:: ሐ) መዝ. 78:71-72ን አንብብ:: መዝሙረኛው ዳዊት በእስራኤል ላይ የነበረውን አመራር ምን ብሎ ጠራው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንመለከተው እጅግ የተለመደው የመሪነት ምሳሌ «እረኝነት» ነው:: አንድ መሪ ሕዝቡን በኃይል በሚገዛ ንጉሥ ወይም ወታደራዊ ኃይልን በሚጠቀም ወታደር፣ ወይም ሰዎች የራሱን ሥራ እንዲሠሩ በሚያደርግ አስተዳዳሪ አልተመሰለም:: ዓለም አመራርን ሲረዳ የኖረው በዚህ መንገድ ነው:: የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች የእግዚአብሔርን በጎች የሚጠብቁ እረኞች ነበሩ:: የሚያሳዝነው፣ አይሁዶች ዓለማዊውን የአመራር ባሕርይ ይከተሉ ነበር:: በብሉይ ኪዳን ሰዎች ንጉሥ ለመሆን ሰዎችን ሲገድሉ ወይም ሌሎችን ለመቆጣጠር ወታደራዊ ኃይል ሲጠቀሙ እንመለከታለን::

ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ መሪነት ያለውን ግንዛቤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የሚያሳየው በጎችን የሚጠብቅ እረኛ ነው:: ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ እግዚአብሔር እረኛ፣ ሕዝቡ ደግሞ የእርሱ በጎች መሆናቸውን እናነብባለን:: እግዚአብሔር ይህንን ምሳሌ የተጠቀመው ለሕዝቡ ያለውን ልዩ እንክብካቤና አመራር ለማሳየት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በጎቹን ወደ ልቡ አቅርቦ የሚሸከም እረኛ መሆኑን ይነግረናል (ኢሳ. 40:11):: ወደ በኋላ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከበደሉት ብዙ ሕዝብ በተቃራኒ ኢየሱስ መልካም እረኛ መሆኑን እናነብባለን (ዮሐ. 10:1-18):: እንዲሁም ደግሞ የትኞቹም ዓይነት መሪዎች (ሽማግሌዎች፣ ነገሥታት፣ ካህናት፣ ነቢያት) እረኞች፣ የተቀሩት ሕዝብ ደግሞ እረኞቹ ሊንከባከቧቸው የሚገቡ በጎች መሆናቸውን እንረዳለን (ሕዝ. 34):: በአዲስ ኪ.ዳን ውስጥ ሳይቀር አመራር የእረኝነት ተግባር መሆኑ ተመልክቷል (1ኛ ጴጥ. 5:2-3)::



እግዚአብሔር የመሪነትን ምሳሌ ለማሳየት እረኛንና መንጋውን የተጠቀመው ለምንድን ነው? ምናልባትም ይህንን ምሳሌ የመረጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር ምን እንደ ሆነ በትክክል ስለሚገልጽ ይሆናል:: ነገር ግን መጋቢ የሚለው ቃል ምንጭ የሆነውን የእረኛ ምሳሌ ከመረዳታችን በፊት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እረኛ ምን እንደ ሆነ መመልከት ይኖርብናል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንመለከተው የእረኛ ተግባር በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታየው የበጎች እንክብካቤ የተለየ ነው::

ብዙውን ጊዜ የተማሩና የሠለጠኑ ሰዎች የእረኝነትን ሥራ ቢንቁም፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አይሁዶች በጎችን ያረቡ እንደ ነበረ እንረዳለን:: ከብቶች ለቦረና ሰዎች በጣም አስፈላጊዎች እንደ ሆኑ ሁሉ፣ ለአይሁዶች በጎች ወሳኝ ነበሩ:: ኑሯቸው የተመሠረተው በበጎች ላይ ነበር:: በጎች የገንዘብ፣ የምግብ፣ የልብስ ምንጭ በመሆን ያገለግሉ ነበር:: ለእግዚአብሔር በቀዳሚነት የሚቀርበው የበግ መሥዋዕት ነበር:: ስለዚህ አይሁዶች በጎችን በሚገባ ይንከባከቡ ነበር:: ከዚህ በታች አይሁዶች (እና ዛሬም በመካከለኛው ምሥራቅ ያሉት ሰዎች) በጎችን የሚንከባከቡበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ካለው ሁኔታ እንዴት እንደሚለይ እንመለከታለን:-

ሀ. እረኞቹ የበጎቹ ባለቤቶች ወይም የባለቤቶቹ ልጆች ናቸው:: እረኞችን መቅጠር የሚችሉት ሀብታሞች ብቻ ነበሩ:: በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታየው በተቃራኒ፣ ባለ በጎቹ ውድ በጎቻቸውን ለትናንሽ ልጆች እምነው አይሰጡም ነበር::

ለ. እረኛው እያንዳንዱን በግ ያውቀዋል:: የእያንዳንዱን በግ ሁኔታ፣ በቀላሉ ሊጠፋ ወይም ሊፈራ መቻሉን፣ ወዘተ. . . ያውቃል:: እንዲሁም ለእያንዳንዱ በግ ልዩ ስም ይሰጠዋል:: ቁጭ

ብሎ በመዳሰስ እንዲተማመኑበት ያደርጋል፡፡ ስማቸውን ይማራል፣ ድምጻቸውንም ይሰያል፡፡

ሐ. እረኛው በጎቹ ወደሚፈልግበት ስፍራ እንዲደርሱለት ከኋላ ሆኖ በበትር አይመታቸውም ወይም ድንጋይ አይወረውርባቸውም፡፡ እረኛው ከበጎቹ ፊት ፊት ይሄዳል፡፡ በጎቹ እረኛቸው በሚጠራቸው ጊዜ ወደ ሣር ወይም ወደ ውኃ እንደሚወስዳቸው ያውቁ ነበር፡፡ እረኛቸውን መተማመንና መከተል ተምረዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉት አያሌ እረኞች በጎቻቸውን በአንድ ስፍራ ያኖሩ ነበር፡፡ ጠዋት ወደ ተሰያዩ መስኮች በጎቻቸውን በሚያሰማሩበት ጊዜ፣ የበጎቻቸውን ስሞች ይጠራሉ፡፡ እነዚህም በጎች ከሌሎች ተሰይተው እረኛቸውን ይከተላሉ፡፡ ሌሎች እረኞች ስማቸውን ቢጠሩ አይከተሏቸውም፣ ከእነርሱ ጋር የግል ግንኙነት የላቸውምና፡፡

መ. በአብዛኛው የፍልስጥኤም ክፍል ሣር ማግኘቱ አስቸጋሪ ስለሆነ፣ እረኞቹ ጥሩ ሣር በመፈለግ ብዙ ጊዜ ያሳልፉ ነበር፡፡ የኩሬ ውኃ በጎችን ለበሽታ ያጋልጣቸዋል፣ ወራጅ ውኃም ሊያስምጣቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ እረኛው ጥሩ የምንጭ ውኃ መርጦ እንዲጠጡ ያደርጋል፡፡ የእረኛው ጭንቀት ለበጎቹ ከፍተኛ እንክብካቤ ማድረግ እንጂ የራሱን ምቾት መጠበቅ አይደለም፡፡

ሠ. እረኞች ብዙውን ጊዜ በትርና ምርኩዝ ይይዙ ነበር፡፡ በትሩ በጎችን እንደ አንበሳና ተኩላ ካሉት አራዊት ለመከላከል የሚያገለግል ነበር፡፡ ምርኩዝ ደግሞ የበጎቹን ሁኔታ ለመርመርና ቁስል እንዳለባቸው ለመመልከት በጎቹን ሳብ በማድረግ ወደ ራሱ ለማስጠጋት የሚጠቀምበት ነበር፡፡ ቁስል ካለባቸው ዘይት ያፈስበታል፡፡ ይህም ዝንቦች በቁስሎቹ ላይ እንቁላል እንዳይጥሉና ቁስሉ እንዳይባባስ የሚያደርግ ነበር፡፡ ዳዊት በትርህና ምርኩዝህ ያጽናኑኛል ማለቱ አስገራሚ አይደለም!

ረ. በጎቹ ጥሩ ሣር ፍለጋ ረዥም ርቀት መጓዝ ስላለባቸው፣ እረኞቹ ከእነርሱ ጋር በሜዳው ላይ አብረው ይቆያሉ፡፡ በጎች ማታ ተበታትነው እንዳይጠፉ ለማድረግ እረኛው ከድንጋይ ከምር



ማደሪያ ይሠራል፡፡ በየምሽቱ በጎች ወደዚሁ ማደሪያቸው ይገባሉ፡፡ አይሁዶች በእነዚህ የበጎች ማደሪያዎች በር ላይ በሮችን ከማኖር ይልቅ እሳት አንድደው እየሞቁ እዚያው ያድራሉ፡፡ ይህ በጎቹ ወጥተው እንዳይጠፉና በአራዊት እንዳይጠቁ ያደርጋል፡፡ የዱር አራዊት በጎቹን ሊያጠቁ የሚችሉት መጀመሪያ እረኛውን ማጥቃት ሲችሉ ነው፡፡ እረኛው «ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል፡፡»

36ኛ ጥያቄ፡- መዝ. 23 እና ዮሐንስ 10፡1-18ን አንብብ፡፡ ከዚህ የእረኛና በጎች ምሳሌ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስላለው ግንኙነት ምን እንማራለን?

እግዚአብሔር ከማያምኑ ሰዎችና ከአሕዛብ ጋር ባለው ግንኙነት ራሱን እንደ ንጉሥ ቢገልጽም፣ ለሕዝቡ ራሱን የሚገልጸው እንደ እረኛ ነው፡፡ እርሱ እያንዳንዳችንን በግል ያውቀናል፡፡ እርሱ ለግል ፍላጎታችን የሚያስብ አምላክ በመሆኑ፣ ችግሮቻችንን ይቋቋምልናል፣ ወደ በረከትም ስፍራ ይወስደናል፡፡ እኛም እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ቀረብ ብለን ድምጹን ልናውቅና ከሐሰተኛ እረኞች ወይም ከሰይጣን ድምጽ ልንለይ ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር እንደሚያስብልን በማሰብ ልንከተለው ይገባል፣ መንገዱ አስቸጋሪ በሚመስልበት ጊዜ ሳይቀር ልንከተለው ይገባል፡፡

በተጨማሪም ይህ የመሪዎች (ሽማግሌዎች፣ ነገሥታት፣ ካህናት፣ ነቢያት) ከእስራኤላውያን ጋር ያላቸው ግንኙነት ምሳሌ ሊሆን ይገባ ነበር (ሕዝ. 34፡1-24)፡፡ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር መንጋ ነበሩ፡፡ እነርሱ የገዥዎች ንብረት አልነበሩም፡፡ ነገር ግን ነገሥታት፣ ካህናትና ነቢያት የእግዚአብሔርን መንጋ የመንከባከብ ኃላፊነት ነበረባቸው፡፡ የሚመሩት ለራሳቸው ሳይሆን፣ ለሕዝቡ ጥቅም ነበር፡፡ ትልቁ ጥያቄ «ሕዝቡ ጤናማ ለመሆን ምን ያስፈልጋቸዋል? በፖለቲካዊ፣ በመንፈሳዊና በማኅበረሰባዊ መልኩ ምን ያስፈልጋቸዋል?» የሚለው ነበር፡፡ እነዚህ መሪዎች ራሳቸውን በመስጠት አመቺ በማይሆንበት ጊዜ ሳይቀር የሕዝቡን ጥቅም ከራሳቸው ማስቀደም ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የታየው ይኸው የመንፈሳዊ መሪ ምሳሌ ነው፡፡

*37ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመሪነታቸውን ምሳሌ የሚወስዱት ከእረኝነት ነው ወይስ ከመንግሥት ባለ ሥልጣን? ለ) አንድ መሪ ራሱን ከአለቃ ይልቅ እንደ እረኛ ቢመለከት እንዴት የሚለወጥ ይመስልሃል? ሐ) ሕዝ. 34፡1-24፤ ዘካ. 10፡3ን አንብብ። መልካም እረኞች ላልሆኑት መሪዎች እነዚህ ጥቅሶች ምን ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ? ስለ ኢየሱስ አመራር ምን ዓይነት ትንቢቶችን ይናገራሉ?*

የሚያሳዝነው፣ የእስራኤል መሪዎች አመራርን እንደ ዓለም ተመለከቱ። ይህም የኃይልና የጥቅማ ጥቅም ስፍራ አድርገው ማየታቸው ነበር። እግዚአብሔር በነቢዩ ሕዝቅኤል በኩል በአይሁድ መሪዎች ደስ አለመሰኘቱን ተናግሯል። ነገሥታት፣ ካህናት፣ ሽማግሌዎችና ነቢያት ሁሉ ለገንዘብ ሲሉ ሕዝቡን በመበደል ላይ ነበሩ። እግዚአብሔር እንደሚፈርድባቸውና ለሕዝቡ የእረኝነትን አገልግሎት የሚሰጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚያስነሣ ተናገረ።

ሽማግሌዎችና አገልጋዮች የሆንን ሰዎች እረኞች እንድንሆን መጠራታችንን ረስተን ይሆን? ስለ «መሪነት» የምናስበው ልክ እንደ ዓለማውያን ነውን? እንደ ሽማግሌ፣ ወንጌላዊ ወይም መጋቢ ሆኖ በእረኝነት ለማገልገል መጠራት ትልቅ ዕድል ነው። በተጨማሪም ይህ ትልቅ ኃላፊነት ነው። የመሪነት ሥልጣን የተሰጠን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንድንከባከብ ነው። ስለ ሕዝባችን የሚኖረን አውቀት የሩቅ ሳይሆን የግል ሊሆን ይገባል። በርኅራኄ ልንሞላና ፍላጎታቸውን ለማሟላት ልንጥር ይገባል። ከሕዝቡ በምናገኘው ጥቅም ላይ ትኩረት ብናደርግ፣ እንዲሁም ለሰዎች ፍላጎትና መንፈሳዊ እድገት እንደሚያስብ መልካም እረኛ ተገቢውን አገልግሎት ባናበረከት፣ ተጠያቂዎች እንደምንሆን የእግዚአብሔር ቃል ያስጠነቅቀናል። እግዚአብሔር ይቀጣናል። እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከፈለግን፣ መሪነትን የምንረዳበትን ሁኔታ መቀየር አለብን። ዓለም በአመራር ክብር፣ እንዲሁም መሪነት በሚያመጣው ኃይል፣ ሀብትና ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ትኩረት ያደርጋል። በሕዝቡ ላይ አለቃ በመሆን ወይም ክርቀት ለመምራት ሊፈልጉ ይችላሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር ሕይወታችንን ለሌሎች



ጥቅም አሳልፎ መስጠት ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ እየመራን ነው? እግዚአብሔር ይርዳን!

*38ኛ ጥያቄ፡- በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ከመከፈታቸው በፊት መሪዎች የሚሠለጥኑት እንዴት ነበር?*

5) የመሪነት ሥልጠና በብሉይ ኪዳን፡-

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር መሪዎችን የሚያሠለጥነው በትምህርት ቤት ብቻ ነው ብለን እናስባለን። አንድ ሰው ብዙ ዓለማዊ ትምህርት ከሌለው ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ካልተማረ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ሊሆን አይችልም ብለን እናስባለን። አንድ ሰው ብዙ ትምህርት ካለው፣ የተሻለ ይሆናል ብለን እናስባለን።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህንን አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መሪዎቹ የአመራርን ንድፈ-አሳብ ወደሚማሩበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማስገባቱን የገለጸበት ክፍል የለም። ነገሥታት እንዴት ነገሥታት መሆን እንደሚቻል ወደሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች አልገቡም፤ ሊቀ ካህናት እንዴት በሊቀ ካህንነት ማገልገል እንደሚቻል ወደሚያስተምር ትምህርት ቤት አልገቡም፤ ነቢያትም እንዲሁ። እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ነበር ያሠለጠናቸው። (ማስታወሻ፡- ይህ ማለት ግን መደበኛ የሆነ ዓለማዊና ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት መከታተል አያስፈልግም ማለት አይደለም። ይህ ለመሪነት ለሚዘጋጁ ሰዎች ጠቃሚ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር መሪዎችን በዚህ መንገድ ያዘጋጃል ከሚለው ቅድመ-ግንዛቤአችን [እና ትዕቢታችን] መውጣት አለብን።) በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሰዎችን ለመሪነት ለማዘጋጀት ሦስት ዐበይት መሣሪያዎችን ተጠቅሟል፡-

ሀ. <u>እግዚአብሔር ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት ለመስጠት ቤተሰብንና ካህናትን ተጠቅሟል።</u> በዘዳግም 6፡4-9 እግዚአብሔር ወላጆች ልጆቻቸውን በጥንቃቄ እንዲያስተምሩ አዝዟቸዋል። እግዚአብሔርን መከተል ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ለማብራራት

ሁሉንም አጋጣሚዎች እንዲጠቀሙ ተነግሯቸዋል። ካህናትም የሰንበት ቀናትን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ሕግጋት እንዲያስተ ምሩ ታዝዘዋል። እንደ ዳዊት ያሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ማንነት የተረዱትና እርሱን መከተል የጀመሩት በዚህ ዓይነቱ ሂደት ነበር።

ለ. እግዚአብሔር የሕይወት ሁኔታዎችን በመጠቀም ሰዎች ሕዝቡን የሚመሩበትን መንገድ አስተምሯል። ዳዊት በጎችን ከአንበሶችና ከድቦች በሚጠብቅበት ጊዜ ሕይወቱን ለበጎቹ መስጠትን ከመማር አንሥቶ ለሕዝቡ ሕይወቱን ስለ መስጠት ጭምር ተምሯል (1ኛ ሳሙ. 17:34-37)። እግዚአብሔር ዳዊት ከሳኦል ጋር ባሳለፈው መራራ ትግል ውስጥ ለመሪነት መታገል ጥሩ ነገር አለመሆኑን እንዲማር ረድቶታል። እግዚአብሔር አብርሃም ማንንም ሰው ከእርሱ በላይ እንዳይወድ ለማስተማር ልጁ ይስሐቅን እንዲሠዋለት ጠይቆታል። ጌዴዎንም በእግዚአብሔር መተማመንን እንዲማር ለማስቻል በ300 ወታደሮች ብቻ እንዲዋጋ አድርጓል።

ሐ. እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀመው እጅግ የተለመደው የመሪነት ሥልጠና ዘዴ ልምድ ያለው መሪ የሚሰጠው ሥልጠና ነበር። አዲሱ ሊቀ ካህናት አባቱን በመመ- ልከትና በአባቱ ክትትል የሊቀ ካህንነትን አገልግሎት በማካሄድ ትምህርት ያገኛል። ኢያሱ አመራርን የተማረው ሙሴን በመርዳት ነበር (ዘጸአ. 24:13-14)። ዳዊት ንግሥናን የተማረው ከሳኦል ቤተ መንግሥት ነው። ኤልሳዕ ነቢይነትን የተማረው ነቢዩ ኤልያስን በመርዳት ነበር።

39ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙውን ጊዜ መደበኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመሪነት ለማዘጋጀት የሚጠቀምበት ብቸኛው (እና ምርጡ) መንገድ ነው ብለን የምናስበው ለምንድን ነው? ለ) እግዚአብሔር ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ነገሮች በመጠቀም አንተን ለአገልግሎት ያዘጋጀህ እንዴት ነው?

40ኛ ጥያቄ፡- የሁለተኛና ሦስተኛ ቀን ትምህርቶችን ከልስ። ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ አመራር ልንማር የምንችላቸውን መርሆዎች ዘርዝር።



ማጠቃለያ፡- ብሉይ ኪዳን ስለ መሪነት በሚናገሩ ጠቃሚ ትምህርቶች የተሞላ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊውን አመራር ካልተ ረዳን ስለ አመራር ዓለምና ባህላችን የሚናገሯቸውን ነገሮች እንኮ ርጃለን። ከብሉይ ኪዳን ዘመን የምንማራቸው ትምህርቶች ከዚህ በታች በማጠቃለያ መልክ ቀርበዋል።

1. መሪነት የሚጀምረው ከቤት ነው። እያንዳንዱ አባት የቤተ ሰቡ መንፈሳዊ መሪ በመሆን ሚስቱና ልጆቹ እግዚአብሔርን እንዲከተሉ መምራት ይጠበቅበታል። ይሄኛው አመራር በሚገባ ካልተከናወነ፣ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ደካማ መሆኗ የማይቀር ነው።

2. ሁለተኛው እጅግ አስፈላጊ የአመራር ደረጃ ሽማግሌዎች የሚገኙበት ነው። ለሕዝቡ ቅርበት ያላቸውና በሚገባ የሚያውቋቸው መሪዎች ነበሩ። ሽማግሌዎች የሚመረጡት ሰዎች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዲኖሩ ለመምከር ነበር። እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቁና እርሱን ለማስከበር የሚፈልጉ ነበሩ።

3. የመጀመሪያው ዕቅድ ራሱ እግዚአብሔር የሕዝቡ ንጉሥና ካህን እንዲሆን ነበር። ካህናትን፣ ነቢያትን፣ ሽማግሌዎችንና ጊዜ ያዊ የፖለቲካ መሪዎችን በመጠቀም ለሕዝቡ ምሪት ይሰጥ ነበር። ነገር ግን ሁልጊዜም እግዚአብሔር ንጉሥ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋቸው ነበር። ሕዝቡ ግን የዓለምን የአመራር መዋቅር ለመከተል ፈለጉ። እግዚአብሔርም ንጉሥ እንዲኖራቸው ፈቀደ። ነገር ግን እነዚህ ነገሥታት ሕዝቡን ይበድሉ ነበር። በቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ሰዎች የዓለምን የመሪነት መዋቅር ለመከተል ይፈልጋሉ። ይህ የመሪነት መዋቅር ጥሩ መስሎ ቢታይም፣ የኋላ ኋላ ሕዝቡን የሚጎዳ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ሰዎች ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር እንዲጠጉ ማበረታታት አለብን። ሰዎች ከንጉሣቸው ከእግዚአብሔር ይልቅ ወደ ሌሎች ሰዎች በመጠጋት መፍትሔ ለማግኘት መጣራቸው አደገኛ ነው።

4. መሪዎች የመሪነትን ተግባር ሳያከናውኑ ሲቀሩና ሕዝቡ የፈለገውን እንዲያደርግ ሲተዉ፣ ሁሉም ሰው የመሰለውን ያደርጋል። ሕዝቡ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ እውነተኛ ሆኖ እንዲኖር ከተፈለገ፣ የማያቋርጥና ገርነት የሞላበት ምሪት መስጠቱ አስፈላጊ ነው። መሪዎች በቀዳሚነት ሰዎችን በማዳመጥ የመሪነትን ተግባር በማያከናውኑበት ጊዜ፣ ምእመናን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ያፈነግጣሉ።

5. እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠራው እንድ ወጥ አድርጎ አይደለም። አንዳንዶች ወጣቶች ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ አረጋውያን ነበሩ። የተማሩና ያልተማሩ፣ ወንዶችና ሴቶች፣ ወዘተ. . . ነበሩ። አንዳንዶች በቀጥታ ወደ መሪነት ሲገቡ፣ ሌሎች ደግሞ ብዙ ጊዜ መጠበቅ ነበረባቸው። እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ መሪነት የሚያመጣው በተለያዩ መንገዶች ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው በልበ-ሙሉነት ለማገልገል በእግዚአብሔር መጠራት አለበት።

6. ውጤታማ መሪ ለመሆን ወሳኙ ጉዳይ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚረጋገጥ መንፈሳዊነት ነበር። ከመሪዎች የሚፈለጉት እንደ አካላዊ ጥንካሬ፣ ትክክለኛ ቤተሰብ ወይም ትምህርት ያሉ ነገሮች ሳይሆኑ፣ እምነትና ታዛዥነት ናቸው።

7. በብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን ውስጥ የመሪነት ትልቁ ትኩረት «እረኝነት» ነው። ሕዝቡ እንደ እግዚአብሔር በጎች ሲሆኑ፣ መሪዎች የእግዚአብሔርን በጎች መንከባከብ ያስፈልጋቸው ነበር። መሪዎች በመሥዋዕትነት በማገልገል በጎቹ ጤናማ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር። እንድ እረኛ ለራሱ ሕይወትን ለማቃለል እንደማይጥር ሁሉ፣ መንፈሳዊ እረኞች የሆኑት ሽማግሌዎችም የመሪነትን ተግባር ማከናወን ያለባቸው ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለሕዝቡ መንፈሳዊ ጥቅም ነው።

8. ብዙውን ጊዜ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት የሚወሰነው በመሪው መንፈሳዊ ሕይወት ነው። መሪዎች በሙሉ ልባቸው እግዚአብሔርን በሚያገለግሉበት ጊዜ፣ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ይታዘዛል። ነገር ግን ሕዝቡ ራስ-ወዳዶች ወይም መንፈሳዊነት



የሚጎድላቸው በሚሆኑበት ጊዜ፣ ሕዝቡም እግዚአብሔርን በመተው ከእርሱ ፈቃድ ውጭ ይኖራሉ።

9. እግዚአብሔር ምእመናን ለኃጢአታቸው ተጠያቂ ቢያደርጋቸውም፣ ሕዝቡ ከእውነት በሚርቁበት ጊዜ አብዛኛውን ጥፋት የሚያኖረው በመሪዎች ላይ ነው። በአመዛኙ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር የሚርቁት መሪዎቻቸውን ተከትለው ነው።

10. እግዚአብሔር ሰዎችን ለተለያዩ ዓይነት አመራሮች ይጠራል። በብሉይ ኪዳን ነገሥታት እንደ ፖለቲካ መሪዎች ሕዝቡን የማስተዳደር ኃላፊነት ነበረባቸው። ካህናት ሕዝቡን ወደ እውነትና አምልኮ ይመሩ ነበር። ነቢያት በችግር ጊዜ የእግዚአብሔርን ልዩ መልእክት ያስተላልፉ ነበር። በአዲስ ኪዳን ጥናታችን ውስጥ እንደምንመለከተው፣ ሽማግሌዎች የነገሥታትን አንዳንድ አስተዳደራዊ ኃላፊነቶች ቢጋሩም፣ የነገሥታት ሥራ ለዓለማዊ መንግሥት ተሰጥቶአል። ሽማግሌዎች ከካህናት ኃላፊነቶች የተወሰኑትን ወስደዋል። የእግዚአብሔርን ቃል የማስተማርና ሕዝቡን በአምልኮ የመምራት ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። በተጨማሪም እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎች እንደ ነቢያት እውነቱን ለሕዝቡ እንዲናገሩ ያደርጋል። ይህ ትንቢታዊ ሚና በተለይ አዲስ ኪዳን ተጽፎ ከማለቁ በፊት አስፈላጊ ነበር።

11. ብሉይ ኪዳን አዲስ ኪዳን እንደሚጀመር ተስፋ በመስጠት ይጠናቀቃል። በአዲሱ ቃል ኪዳን፣ የእድሜ ወይም የጾታ ገደብ ሳይደረግ እያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚያስችል የመንፈስ ቅዱስ እገዛ ይደረግለታል። ይህም ቀደም ሲል የነበረውን አመራር የሚለውጥ ነው።

> 41ኛ ጥያቄ፡- እነዚህን 11 ዐበይት ነጥቦች ከልስ። ሀ) ከእነዚህ ነጥቦች መካከል ባህላችን ስለ መሪነት ካለው ግንዛቤ የሚለዩት የትኞቹ ናቸው? ለ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚዘነጓቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

## አራተኛ ቀን፡- ለሳምንታዊ ውይይት በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

*የመወያያ ጥያቄዎች፡-*

1. ሀ) የብሉይና የአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦችን አነጻጽር። የሚመሳሰሉትና የሚለያዩት እንዴት ነው? ለ) ልዩነቶቹ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ግለጽ። ሐ) የቤተ ክርስቲያን አመራር ብዙውን ጊዜ ከአዲስ ኪዳን እውነታዎች ይልቅ በብሉይ ኪዳን አመለካከቶች ላይ ትኩረት የሚያደርገው እንዴት ነው? አዲስ ኪዳን ስለ አመራር የሚናገራቸውን እውነቶች ብንኖር የቤተ ክርስቲያን አመራር እንዴት የሚለወጥ ይመስልሃል?

2. ሀ) የቤተ ክርስቲያን አመራር የነገሥታትን፣ የአለቆችን፣ ዴሞክራሲያዊ እና ኮሙዩኒስታዊ መዋቅሮችን ቢከተል ምን ሊመስል እንደሚችል ግለጽ። በእያንዳንዱ ምሳሌ ውስጥ ውሳኔውን የሚሰጠው ማን ነው? በእያንዳንዱ የአመራር መዋቅር ውስጥ የተራው ሕዝብ ሚና ምን ይሆናል? ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ በሰፊት የሚታየው የትኛው ዓይነት የአመራር መዋቅር ነው? ሐ) በብሉይና አዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ መሪነት የተሰጡትን ትምህርቶች ብንከተል መሪነት እንዴት ሊለወጥ ይችላል?

3. ሀ) እግዚአብሔር አንድ መሪ የቤተሰቡ መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ካልቻለ ሽማግሌ ሊሆን አይችልም የሚለው ለምንድን ነው? ለ) በኢትዮጵያ ክርስቲያን ባሎች በቤታቸው ጥሩ መንፈሳዊ መሪዎች ናቸው ብለህ ታስባለህ? መልስህን አብራራ። ሐ) ይህ የቤተሰብ አመራር ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችል የሚባልባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ። ይህ ችግር ምን ዓይነት ውጤቶችን ያስከትላል? መ) አባት ለቤተሰቡ መንፈሳዊ አመራር ለመስጠት ምን ሊያደርግ ይችላል?

4. መሪነት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚለው ጥናታችን እነዚህን 11 ዐበይት ነጥቦች ከልስ። ሀ) ከእነዚህ ነጥቦች መካከል ባህላችን ስለ መሪነት ካለው ግንዛቤ የሚለዩት የትኞቹ ናቸው? ለ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚዘነጓቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?



# ትምህርት ሃያ

## አንደኛ ቀን

## የቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር መዋቅሮች ትምህርት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ (ክፍል 3 - አዲስ ኪዳን)

አሥር በዓለም እጅግ ኃያላን የሆኑ ሰዎች አንድ ላይ ተሰባሰቡ እንበል። በዚህ ክፍል ውስጥ የአሜሪካ፣ የሩስያ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የቻይናና የሌሎችም ታላላቅ አገሮች መሪዎች ይገኛሉ። የስብሰባው ሊቀ መንበር በአሁኑ ሰዓት የዓለም ኃያል አገር የምትባለው አሜሪካ ፕሬዚዳንት ናቸው። ሁሉም መሪዎች ወታደራዊ ኃይላቸውን የሚቆጣጠር የአዲሱ ድርጅት መሪ ሆነው ለመመረጥ መፈለጋቸውን በመግለጽ ይከራከራሉ። በክፍሉ ውስጥ ከአሥሩ መሪዎች በስተቀር ሌላ ማንም ሰው አልነበረም። በድንገት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ብድግ ብለው ለተቀሩት ዘጠኝ ሰዎች እንደ ሻይ፣ ቡናና ለስላሳ ያሉትን ነገሮች ማደል ጀመሩ። ከዚያም ኮታቸውን አውልቀው ውኃ በባልዲ ቀዱና ከዘጠኙ መሪዎች ፊት በርከክ ብለው ጫማቸውን አወለቁ። ከዚያም እግራቸውን አጠቡላቸው።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ዘጠኙ መሪዎች ለአሜሪካ ፕሬዚዳንት ተግባር ምን ዓይነት ምላሽ የሚሰጡ ይመስልሃል? ለምን? ለ) ዓለም ሥልጣንንና መገልገልን አስመልክቶ አመራርን የምትረዳው እንዴት ነው? ሐ) ፊልጵ. 2፡3-11ን አንብብ። የፖለቲካ መሪዎችን ባሕርይ የነገሥታት ንጉሥና አምላክ የሆነው ክርስቶስ ካሳየው ሁኔታ ጋር አነጻጽር። |

ከላይ የቀረበው ምሳሌ ዓለም የሚመለከተው አመራር ክርስቶስ ካሳየው የተለየ መሆኑን ለማመልከት ጠቃሚ ይሆናል የሚል ግምት አለን። በርግጥ፣ ማንም ሰው በዓለም እጅግ ኃያል የሆነው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በፈቃደኝነት ሌሎችን ሰዎች ይረዳል የሚል ግምት አይኖረውም። እጅግ ታላቅ በመሆኑ ምክንያት ሌላ ሰው (ምናልባትም ከትናንሽ አገሮች መሪዎች አንደኛው) ተነሥቶ እንዲያገለግል ሊያደርግ ይችላል። ማንም የአገር መሪ ደግሞ ሌላውን ለማገልገል ሲል ራሱን ዝቅ አያደርግም። አገልጋዮች ማድ

ረግ ያለባቸው ይህንን ነው። ከዓለም አመለካከት አንጻር መሪዎች ክብራቸውን መጠበቃቸው አስፈላጊ ነው። ይህ የሚገለጸው ደግሞ በክብር ስፍራ ላይ በመቀመጥ፣ ሌሎች እንዲሰሟቸውና እንዲታዘዟቸው በማድረግ እንጂ፣ ሌሎችን በማገልገል አይደለም።

ክርስቶስ ከዚህ ምንኛ የተለየ ነበር! እርሱ መሪነትን የተመለከተው ክብርን እንደ መጠበቅ ሳይሆን፣ በማገልገል መሆኑን አሳይቷል። ክርስቶስ እንዳለው፣ ታላቅ መሪ ለመሆን የሚፈልግ ማንም ቢሆን ሌሎች ታላቅ አገልጋይ ሊሆንና ሕይወቱን አሳልፎ ሊሰጥ ይገባል (ማቴ. 20:26-28)። ስለዚህ፣ በክርስቶስ ዓይን ብዙ ሠራዊትና ሀብት ካለው ከአሜሪካ ፕሬዚዳንት ይልቅ የካቶሊክ መነኩሲት የሆኑት እማሆይ ተሬዛ የሕንድ ለምጻሞችን፣ ማኅበረሰቡ ያገለሳቸውንና ኤድስ ያጠቃቸውን ሰዎች መርዳታቸው የላቀ ግምት ይኖረዋል። ምናልባትም ክርስቶስ በታላቅ መሪነት የሚመለከተው የቤተ ክርስቲያንን የሽማግሌዎች ቦርድ ሳይሆን፣ ነፍሷን ጥላ ቤተ ክርስቲያንን የምታጸዳውን ወይም ቡና የምታፈላውን ምስኪን ሴት ሊሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ አመራርን የሚመለከተው ከባህላችን ግንዛቤ በተለየ መንገድ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ አመራር ምን እንደሚመስል ለመረዳት ከፈለግን፣ የእግዚአብሔር ቃል አስተሳሰባችንን እንዲለውጥ መፍቀድ አለብን።

በታሪክ ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲመሩ የኖሩት እንዴት ነበር? ከብሉይ ኪዳን፣ ከአዲስ ኪዳንና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለ አመራር ምን እንማራለን? የታሪክ ትምህርቶች ዛሬ መምራት ስላለብን መንገድ ምን ያስተምሩናል? ታሪክ ለቤተ ክርስቲያን እጅግ ጠቃሚ መሆኑን የሚያሳየው መዋቅር አለ? ለቀጣይ ሁለት ሳምንታት የምናጠናው በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ይሆናል።

በትናንትናው ዕለት የብሉይ ኪዳንን የአመራር ሁኔታ አጥንተናል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመንከባከብ እንዴት የተለያዩ ዓይነት መሪዎችን እንደ ሾመ ተመልክተናል። <u>ባሎች</u> ቤተሰቦቻቸውን፣ <u>ሽማግሌዎች</u> የሕዝቡን ማኅበራዊ ጉዳዮች እንዲመሩ፣ <u>ነገሥታት</u> ፖለቲካዊ መሪዎች እንዲሆኑ፣ <u>ካህናት</u> በሃይማኖታዊ



መሪነት እንዲያገለግሉ፣ እንዲሁም ነቢያት የእግዚአብሔር ቃል አቀባዮች እንዲሆኑ አድርጓል። እነዚህ ሁሉ መሪዎች ራሳቸውን እንደ «እረኞች» በመመልከት፣ የእግዚአብሔርን መንጋ እንዲንከባከቡና ሕዝቡን ለማገልገል ራሳቸውን እንዲሰጡ ተጠይቀው ነበር። ነገር ግን አብዛኞቹ መሪዎች አመራር ሲሰጡ የነበሩት ባህላቸው የሚነግራቸውን አሳብ በመከተል እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ምሪት በመጠበቅ አልነበረም። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የተጋፈጠው ችግር የበቂ መሪዎች አለመኖር አልነበረም። ችግሩ መሪዎቹ ትክክለኛ ባሕርይና ሕዝቡን የማገልገል ዝንባሌ ያልነበራቸው መሆናቸው ነው።

## ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የአይሁዶች አመራር።

እግዚአብሔር የእስራኤልንና የይሁዳን ሕዝብ በኃጢአታቸው ምክንያት ለምርኮ አሳልፎ ከሰጣቸው በኋላ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ አመራር መለወጥ ጀመረ። ከዚያ በኋላ ከዳዊት ወገን የሆነ ንጉሥ አልነበራቸውም። በምርኮ አገር ሳሉ፣ ሽማግሌዎች በሕዝቡ ላይ ማኅበራዊ ቁጥጥር ያደርጉ ነበር (ሕዝ. 8:1)። አይሁዶች በዘሩባቤል መሪነት ወደ አገራቸው ሲመለሱ፣ መጀመሪያ ሦስት ዓይነት መሪዎች ነበሯቸው። <u>ሽማግሌዎች</u> ነበሩ። እነዚህ ሽማግሌዎች ለሕዝቡ ስለ ሰጡት አመራር ብዙም የምናውቀው ነገር የለም። በአሕዛብ ነገሥታት ሥር በአስተዳዳሪነት የሚሠሩ የፖለቲካ መሪዎችም ነበሩ። ለዚህ አብነት ከሚሆኑት መካከል ዘሩባቤልና ነህምያ ሊጠቀሱ ይችላሉ። አዲስ በተገነባው ቤተ መቅደስ ውስጥ አምልኮውን የሚከታተሉና ሕዝቡን የሚያስተምሩ እንደ ዕዝራ ያሉ ካህናት አሉ።

ከዕዝራ ዘመን በኋላ፣ የካህናት ሥልጣን ጨምሯል። እነዚህ ካህናት የሃይማኖት መሪዎች በመሆናቸው ብቻ ስላልረኩ የፖለቲካ መሪዎችም ጭምር ሆኑ። ክርስቶስ ከመወለዱ ከ160 ዓመታት በፊት አካባቢ፣ አንዳንድ ካህናት የፍልስጥኤም ገዥዎች በነበሩት የፋርስ መሪዎች ላይ ዐመፅ አካሄዱ። ለ100 ዓመታት እነዚህ ካህናት የእስራኤልን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ አመራር ለመቆጣጠር

ቻሉ። ሮማውያን ፍልስጥኤምን ከተቆጣጠሩ በኋላ፣ እነዚህ ካህናት የፖለቲካና የሃይማኖት ሥልጣን ይዘው ለመቆየት ሞክረዋል። ካህናቱ ሸንጎ የተባለው ገዥ ቡድን ለመመሥረት ችለው ነበር።

በክርስቶስ ዘመን የነበሩት ዋና ዋና መሪዎች የሚከተሉት ነበሩ፡-

1. ሰዱቃውያን፡- እነዚህ የቤተ መቅደሱን አምልኮና ሲቻል ደግሞ የይሁዳን ፖለቲካ የሚቆጣጠሩ ነበሩ። ብዙዎቹ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር። ግሪኮች ወይም ሮማውያን አይሁዳውያን ባህላቸውን ቀይረው ይበልጥ እነርሱን እንደሚመስሉ ቢጠይቋቸው፣ እነዚህ ካህናት የተባሉትን ለማድረግ ፈቃደኞች ነበሩ። ከሀብታም ነጋዴዎችም ጋር በቅርበት ይሠሩ ነበር። ለብዙዎቹ ካህናት ከመንፈሳዊ ንጽሕና በላይ የፖለቲካ ኃይልና ገንዘብ አስፈላጊ ነበር። ሰዱቃውያን ኢየሱስ በሮም ላይ ዐመፅ እንዳይጀምርና እነርሱን ተወቃሽ እንዳያደርጋቸው ይፈሩ ነበር። መሪያቸው እንዳለው፣ ሮም እነርሱንና አገሪቱን ከምታጠፋ ይልቅ፣ አንዱን ንጹሕ ሰው (ኢየሱስን) ቢገድሉ ይሻላቸው ነበር (ዮሐ. 11:49-52)። በ68 ዓ.ም. አይሁዶች በሮም ላይ ባመፁ ጊዜ፣ ለዱቃውያን የፈሩት አልቀረላቸውም፣ ተወቃሽ ሆኑ፤ ከመሪነታቸውም ተነሡ። ይህም የሆነው በ70 ዓ.ም. ሮማውያን ኢየሩሳሌምን በደመሰሱበት ወቅት ነበር።

በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ፖለቲካዊ ወይም አስተዳደራዊ ጫና ለማሳደር መፈለግና የገንዘብ ፍላጎት እንዴት በመንፈሳዊ አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ትኩረት እንደሚያዳክም ሰዱቃውያን በምሳሌነት ያሳዩናል። ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ መሪ ዎች የሚያምኑትን ነገር ሕዝቡ ከሚፈልገው አንጻር በማስተካከል ሌሎች ሃይማኖቶችን የመቀበል፣ መንግሥትንና ሀብታም ሰዎችን ለማስደሰት ወይም ሥልጣናቸውን ለመጠበቅና ለመጨመር ይሞክራሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ ለጥመው በሚገቡበት ጊዜ፣ ከመንፈሳዊ መሪነት ወደ ፖለቲካዊ መሪነት ለመሸጋገር ይፈተናሉ። እነዚህ መሪዎች የሰዱቃውያንን ምሳሌነት እየተከተሉ መሆናቸው ግልጽ ነው።



2ኛ ጥያቄ፡- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዛሬም በሰዱቃውያን ጉድጓድ ውስጥ ሊወድቁ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

2. ፈሪሳውያን፡- እነዚህ የብሉይ ኪዳን ሕጎችን በከፍተኛ ጥንቃቄ ለመከተል የሚፈልጉ ሰዎች ነበሩ። የብሉይ ኪዳን ሕጎችን በመጠበቅ እግዚአብሔርን ለማስደሰት በመፈለጋቸው፣ ብሉይ ኪዳን ባዘዛቸው ሕጎች ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ሕጎችን ጨመሩ። ይህንን በምሳሌ ለማብራራት፣ የሰንበትን ጉዳይ እናንሣ። ብሉይ ኪዳን ሰዎች በሰንበት እንዳይሠሩ ያዝዛል። ፈሪሳውያኑ በዚህ ላይ ተመሥርተው ማንም ሰው ከአንድ ኪሎ ሜትር በላይ እንዳይጓዝ አዘዙ። አንድ ሰው ሁለት ኪሎ ሜትር ቢጓዝ «ሥራ» እንደ ሠራ ይቆጠራል አሉ። ፈሪሳውያን የፖለቲካ ሥልጣን ፍላጎት ቢኖራቸውም፣ የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ለሃይማኖታዊ ሥልጣን ነበር። ሰዎች እንደ «ቅዱሳን» እንዲመለከቷቸው ስለሚፈልጉ፣ ለየት ያለ ልብስ ይለብሱ ነበር። ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለረዥም ሰዓታት ይጸልያሉ። ተራው ሕዝብ «ራባይ» ወይም መምህር ብሎ እንዲጠራቸው ይፈልጋሉ። አብዛኛው ጥ ረታቸው የሕዝቡን ከበሬታ ማግኘት ነበር። ፈሪሳውያን ራሳቸውን የሚመለከቱት ከተራው ሕዝብ የተሻሉ፣ የበለጠ ቅዱሳንና በእግዚአብሔር ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት ያላቸው አድርገው ነበር። ሕዝቡን የሚመሩት በሃይማኖታዊ ኩራት ነበር። ብዙውን ጊዜ ሌ ት ወይም እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ዓይነት ኃጢአተኛ አለመሆናቸውን በመግለጽ የሚያቀርቡት የፈሪሳውያን ጸሎት ባሕርያቸውን ያሳያል (ሉቃስ 18:9-14)።

እነዚህ መሪዎች የክርስቶስ ቀንደኛ ጠላቶች ነበሩ። ሕጉን ለመጠበቅ ያወጧቸውን ብዙ ደንቦች ስለማያከብር ነበር የሚጠሉት። ከ«ኃጢአተኞች» እና በማኅበረሰቡ ውስጥ ከተናቁት ሰ ዎች ጋር አብሮ መሆኑም ያናድዳቸው ነበር። ኢየሱስ የታወቁ የብሉይ ኪዳን ሕጎችን ይጥሳል የሚል ክስ አቅርበውበት አያውቁም። ራሳቸው የጨመሯቸውን ሕግጋት እንደሚጥስ ብቻ ነበር የሚናገሩት። ፈሪሳውያን ሃይማኖትን የሚጠቀሙት ለራሳቸው የሕዝብን ከበሬታ ለማግኘት እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ጋር

መልካም ግንኙነት ለመመሥረት ባለመሆኑ ይነቅፋቸው ነበር። እነርሱም በሸንጎው ውስጥ ባላቸው ሥልጣን ተጠቅመው ከሰዱቃውያን ጋር በመተባበር ኢየሱስን አሰቀሉት።

3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ፈሪሳውያን ሊያስቡና ሊተገብሩ የሚችሉባቸውን ምሳሌዎች ግለጽ። ለ) መሪዎች እግዚአብሔር ይሠራል ብለው ከሚያስቡት ውጭ የሆኑትን የእግዚአብሔር አሠራሮች እንዴት እንደሚቃወሙ ግለጽ።

የሰዎችን ከበሬታ ለማግኘት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች «መንፈሳዊነታቸውን» ለማሳየት መፈተናቸው ግልጽ ነው። እንዳንድ መሪዎች ወይም ፈሪሳውያን ሰዎችን ለማስደነቅ ብለው ከፍተኛ ትእይንቶችን ሊሠሩ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ረዣዥም፣ ውስብስብ፣ መንፈሳዊ የሚመስሉ ጸሎቶችን ልንጸልይ እንችላለን። እነዚህ ጸሎቶች ብዙውን ጊዜ «በሃሌ ሉያ» የታጀቡ ናቸው። እንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ሕግጋት ላይ የራሳቸውን ሕግጋት ለመጨመር ይፈተናሉ። (ለምሳሌ፣ ሴቶች የከንፈር ቀለም እንዳይቀቡ፣ ሱሪ እንዳይለብሱ፣ ፊልም ቤት እንዳይገቡ፣ ከቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም እንዳይቀሩ፣ ወዘተ. . . የሚጠይቁ ሕጎችን ያወጣሉ።) አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል እነዚህን ሕጎች በማይከተልበት ጊዜ፣ መሪዎቹ ይናደዳሉ። እነርሱ ያወጡትን ሕግ ከሚተላለፍ ይልቅ ቢዋሽ፣ ቢያማ ወይም ለዎችን ባይወድ ይሻላቸዋል። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙውን ጊዜ ከለምጻሞች፣ ከለማኞች ወይም ከሸክላ ሠሪዎች ጋር አብረው ለመሆን ወይም ወደ ቤታቸው ለመጋበዝ አይፈልጉም። ይህ በሰዎች ዘንድ አክብሮት ያሳጣናል ብለው ያስባሉ። በዚህ ዓይነት የፈሪሳውያን መንፈስ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልብ ዘልቆ ይገባል!

3. ጸሐፍት፡- ጸሐፍት የሥነ-መለኮት ሥልጠና ያገኙ አይሁዶች ናቸው። ከዕዝራ ዘመን ጀምሮ ጸሐፍት የተባለው የካህናት ቡድን ብሉይ ኪዳንን በጥንቃቄ በማጥናት ላይ ትኩረት ያደርግ ነበር። ከዚያም እንደ ጠበቃዎች መሥራት ቀጠሉ። የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች የሙሴን ሕግ ትርጉም ለማወቅ



ወደ እነዚህ ሰዎች ነበር የሚመጡት። በኢየሱስ ዘመን በሸንጎው ውስጥ እንደ «ጠበቆች» ይሠሩ ነበር። ይህንንም የሚያደርጉት ስለ ብሉይ ኪዳን ትምህርት መመሪያ በመስጠት ነበር። ጸሐፍት በእግዚአብሔር ቃል እውቀታቸው ይኩራሩ ነበሩ። ለክርስቶስ ጥላቻ ስለ ነበራቸው፣ አላዋቂነቱን ለማሳየት ከብሉይ ኪዳን የተ ወሳሰቡ ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ነበር (ማቴ. 15:1-10፤ ማር. 12:18-34)። እርሱም ሕጉን እያወቁ ሕጉን የጻፈውን አምላክ ባለመከተላቸው ይወቅሳቸው ነበር።

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የሥነ-መለኮት ትምህርት የተከታተሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእነርሱን ያህል ትምህርት ያላገኙትን ሰዎች ሊንቁ የሚችሉት እንዴት ነው? ለ) መሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርቶች ሊያውቁና የመጽሐፍ ቅዱሱን አምላክ በጥልቀት ላያውቁ የሚችሉትስ እንዴት ነው?

የሥነ-መለኮት ትምህርት የተከታተልን ሰዎች የጸሐፍትን እመለካከት ላለመያዝ መጠንቀቅ አለብን። ካልተማሩት ሰዎች እንሻላለን ወይም መንፈሳውያን ነን ብለን ልናስብ እንችላን! የሁሉንም ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄዎች መልስ የምናውቅ ስለሚመስለን፣ ሌሎች ሰዎች የምንናገረውን እንዲሰሙና እንዲታዘዙ ልንፈልግ እንችላለን። ይህም ሆኖ መንፈሳዊ ሕይወታችን ደረቅ ሊሆን ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርቶች ልናውቅና የመጽሐፍ ቅዱሱን አምላክ በጥልቀት ከማወቅና ከመውደድ ልንቆጠብ እንችላለን። ይህም ትልቁን ነገር እንድናጣው ያደርገናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፣ እውቀት ሊያስታብየን ይችላል (1ኛ ቆሮ. 8:1-3)። አስፈላጊው ነገር ብዙ ትምህርት ሳይሆን፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በግል ማወቅና መለማመድ ነው (ፊልጵ. 3:10-14)።

እይሁዶች ባሉባቸው ስፍራዎች ሁሉ፣ ምኩራብ በተባለ ስፍራ ይሰባሰቡ ነበር። በቂ ቁጥር ያላቸው ወንድ አይሁዶች ካሉ፣ ምኩራብ ይገነቡና የአይሁድ ማኅበረሰብን የሚመሩ ሰዎችን ይመርጡ ነበር። ከምኩራቡ ውስጥ አንድ ሰው መምህር ወይም ራባይ በመሆን ያገለግላል። ራባዩ በእግዚአብሔር ቃል የሠለጠነ ሰው መሆን አለበት። ሰዎች በየቅዳሜው ለአምልኮና ትምህርት

የሚመጡት ወደዚሁ ምኩራብ ነበር። እያንዳንዱ ምኩራብ በሌሎች ምኩራቦች ላይ የሚደገፍበት መዋቅራዊ አሠራር አልነበረውም። ሁሉንም ምኩራቦች የሚያስተባብር አንድ ማዕከላዊ አካል አልነበረም። ለምኩራቡ መሠረታዊ መመሪያዎችን የሚሰጡት የብሉይ ኪዳን ትምህርቶችና የሃይማኖት መሪዎች ትምህርቶች ነበሩ። በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የሃይማኖት መሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን አሳቦች ሊልኩ ወይም በትምህርታቸው ተጽዕኖ ሊያደርጉ ቢችሉም፣ በምኩራቦች ላይ የሚያሳድሩት መደበኛ ቁጥጥር አልነበረም። የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስቤተ ክርስቲያን ተከሳ የምኩራቦችን አሠራር ተከትለዋል።

አይሁዶች እንደ ጸሐፍት ወይም ፈሪሳውያን ያሉትን መሪዎች የሚያሠለጥኑት በደቀ መዝሙርነት ነበር። ጸሐፊ ወይም ፈሪሳዊ ለመሆን የሚፈልግ ሰው የአንድ የተከበረ ሃይማኖታዊ መሪ ደቀ መዝሙር ይሆንና የመሪውን ትምህርትና ኑሮ በመመልከት ይማራል። ሐዋርያው ጳውሎስ እጅግ ከታወቁ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች አንዱ የነበረው የገማልያል ደቀ መዝሙር ነበር (የሐዋ. 22:3)። ጳውሎስ ይህንን የደቀ መዝሙርነት ዘዴ በመጠቀም እንደ ጢሞቴዎስ፣ ሲላስና ቲቶ ያሉትን አገልጋዮች አሠልጥኗል። እነርሱም እግዚአብሔርን ስለ ማገልገል ከጳውሎስ ሕይወትና ትምህርት ለመረዳት ችለዋል።

## የመሪነት ትምህርት ከክርስቶስ ሕይወት

አብዛኞቹ መሪዎች ከአመራር ሥራቸው የግል ወይም የፖለቲካ ጥቅም ይፈልጋሉ። ወይም ደግሞ ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት በሰዎች ዘንድ መንፈሳዊ ነው የሚል ስም ለማትረፍ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ውስጥ አገልጋይ እንዲሆን ነበር የላከው። ኢየሱስ አምላክና የነገሥታት ንጉሥ ቢሆንም፣ አመራርን ያሳየው ፍጹም በተለየ መንገድ ነበር።

5ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ፊልጵ. 2:3-11፤ ማር. 10:42-45፤ ዮሐ. 13:1-17ን አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የኢየሱስን ባሕርይ የሚያሳዩትን ነገሮች ዘርዝር። ለ) እነዚህ ባሕርያት አመራሩን የለወጡት እንዴት ነው? ሐ)



በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ካነበብከው አሳብ እኛ አመራርን ከምንመስከትበት መንገድ የተለዩ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

1. ኢየሱስ ስለ አመራር ፍጹም የተለየ አመለካከት ነበረው።

ፍልስጥኤም በተባለች ኋላ ቀር አገር ይኖር የነበረውና ደሀው አይሁዳዊ ኢየሱስ በታሪክ ከማንም በላይ ዓለምን ለውጧል። በዓለም ታሪክ ውስጥ ብዙ ነገሥታት፣ ወታደራዊ አዛዦችና ዝነኛ መሪዎች ታይተዋል። ነገር ግን የኢየሱስን ያህል ዓለምን የለወጠ አንድም የለም። በርግጥ፣ ኢየሱስ አምላክ በመሆኑ ከሰብአዊ መሪዎች የተለየ ነው። ነገር ግን እርሱን በታሪክ ሁሉ የሰዎች ሕይወት ለዋጭ ያደረገው የአመራር ክህሎቶቹ ሳይሆን፣ የኖረበትና ያስተማረው ፍጹም ልዩ የሆነ የአመራር ግንዛቤ ነው። ፍጹም የሰው ልጅ የሆነው ኢየሱስ ፍጹም መሪ ነው። እግዚአብሔርም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲከተለው የሚፈልገው ሞዴል (አርአያ) ኢየሱስ ነው። የእርሱን አመራር በበለጠ በተከተልን መጠን፣ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ልንመራ እንችላለን። በአመራራችን የዓለምን አሴቶችና መንገዶች የምንከተል ከሆነ፣ የኢየሱስን ዓይነት አመራር ሳለመስጠት መርጠናል ማለት ነው። (ማስታወሻ፡- ከእነዚህ አሳቦች አንዳንዶቹን ስለ መንፈሳዊ አመራር ባሕርያት በሚናገረው መጽሐፋችን ውስጥ አጥንተናል። ስለዚህ ኢየሱስ ያሳያቸውን ልዩ የአመራር መንገዶች ብቻ አጠር ባለ መልኩ እናቀርባለን።)

ሀ. ኢየሱስ የመሪነት ክብር (የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ) በአኗኗሩና አገልግሎቱ ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድር አልፈቀደም። ማንኛውም ንጉሥ ወይ የንጉሥ ልጅ የከብር ስፍራ ትቶ ባሪያ፣ የተናቀና ሰዎች የሚያጉላሉት ሰው ለመሆን አይመርጥም። ኢየሱስ ግን ይህንን ነበር ያደረገው። በሰማይ ዘሳሰማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳለ ያንን ሥልጣን ትቶ ወደ ምድር በመምጣት እንደ ባሪያ አገለገለ። ይህንንም ያደረገው የእግዚአብሔር ጠላቶች የነበሩትን ኃጢአተኞች ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ለማሟላት በማሰብ ነበር።

ምድራዊ አመራርና ክርስቶስ ለክብር የሚሰጡትን ስፍራ አነጻጽር:: አንድ ዝነኛ መሪ ወደ አንድ ክፍል በሚገባበት ጊዜ፣ ሁሉም አክብሮት ለመስጠት ሲል ብድግ ብሎ ይቆማል:: መሪዎች ምርጥ የተባሉ መኪኖች ያጅቧቸዋል:: በምርጥ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ:: ዝነኛ መሪዎች በፈቃዳቸው ወደ ጎዳናዎች ወጥተው ምንም ነገር ከሌላቸው ሰዎች ጋር አይኖሩም:: ጫማ ከሚጠርጉ ልጆች (ከሊስትሮዎች) ወይም አንጨት ከሚሸጡ ሴቶች ጋር አይቀመጡም::

የክርስቶስን የመንፈሳዊ አመራር ምሳሌነት ለመከተል ከፈለግን፣ በአመራር ክብር ላይ ትኩረት ልናደርግ አይገባም:: የእኛ ክብር ማግኘት ትልቅ ጉዳይ መሆን የለበትም:: በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች ከፊት በማለፊያ ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ይገኛሉ:: ተጋባዥ ለባኪዎችም ምርጥ የመቀመጫ ስፍራ ይሰጣቸዋል:: በአንድ በኩል ይህ ባህላዊ ሰዎችን የማክበር ዘዴያችን ነው:: እንደ መሪዎች ግን፣ እንዲህ ዓይነቱን የምንጠብቅ ከሆነና ይገባናል የምንለው ክብር በማይሰጠን ጊዜ የምንናደድ ከሆነ፣ የኢየሱስን ዓይነት መንፈሳዊ አመራር ዘንግተናል ማለት ነው:: እንደ ኢየሱስ ዓለም ክብር ከሚሰጣቸው ሰዎች ጋር ብቻ ዝምድና መፍጠር የለብንም:: ከዚህ ይልቅ ከትልቁ እስከ ትንሹ ሁሉንም ሰው ማገልገል አለብን::

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሌሎች አገልጋይ ከመሆን ይልቅ፣ የአመራርን ክብር እንዲፈልጉ የሚያደርጉ ሌሎች ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? |

ለ. ኢየሱስ ገንዘብ በአመራሩ ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድር አልፈቀደም:: የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ወዲያውኑ በምታገኝበት ሀብታም አባት እጅ ነው አንበል ያደግከው:: ያንን ሁሉ ሀብት ጥለህ በወር 100 ብር እየተከፈለህና በጎጆ ቤት ውስጥ እያደርክ ወደምታገለግልበት የገጠር ስፍራ ለመሄድ ፈቃደኛ ትሆናለህ? ብዙዎቻችን ይህንን አናደርግም:: ይህ የኢየሱስን ዓይነት አመራር አንደማንከተል ያሳያል:: ጎዳናዎቿ ወርቅ የተነጠፉባትን መንግሥተ ሰማይን ትቶ ወደ ምድር መጥቶ በከብቶች በረት



ውስጥ ተወለደ:: በኋላ አንደተናገረው፣ በምድር ላይ ምንም ነገር አልነበረውም - የሚንተራሰው ትራስ እንኳ አልነበረውም (ማቴ. 8:19-20):: ኢየሱስ መንፈሳዊ መሪዎች ስለ ቁሳዊ ሀብቶች መጨነቅ እንደሌለባቸው አሳይቷል:: ባስማቋረጥ ተከታዮቹ ገንዘብን ሳይሆን እግዚአብሔርንና መንግሥቱን እንዲሹ ነግሯቸዋል (ማቴ. 6:33):: ደቀ መዛሙርቱ ልባቸውን ለምድራዊ ነገሮች ከሰጡ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚጠብቃቸው አመልክቷል (ማቴ. 6:19-21)::

ኢየሱስ አንድ ሰው ብዙ ደመወዝ ማግኘቱን ወይም ሀብታም መሆኑን አይቃወምም:: ነገር ግን የገንዘብ ጉዳይ እንዲያስጨንቀን አይፈልግም:: እግዚአብሔር በሀብት ከባረከን፣ ይህንን ያደረገው መንግሥቱን ለማስፋትና ድሆችን ለመርዳት እንድንጠቀምበት ነው:: እግዚአብሔር ድሆች እንድንሆን ከመረጠ፣ እርሱ የሚያስፈልገንን እንደሚሰጥ በማወቅ ድህነታችንን ተቀብለን መኖር አለብን:: ለትንሽ ደመወዝ እንድናገለግል ብንጠየቅ፣ የገንዘቡ ጉዳይ በውሳኔያችን ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የለበትም:: ስለ ገንዘቡ የምንጨነቅ ከሆነ፣ የክርስቶስ ዓይነት መሪዎች አልሆንንም ማለት ነው:: ጳውሎስ በማግኘትም ይሁን በማጣት በቃኝ ማለትን ተምሬአለሁ ብሏል (ፊልጵ. 4:11-13):: የዓለም ዓይነቱ የገንዘብ ጥቅም አስተሳሰብ ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ በምንሰጠው አገልግሎት ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር መጠንቀቅ አለብን:: «ዲግሪ ስላለኝ ዲግሪ ያለው ሰው የሚገባውን ደመወዝ ማግኘት አለብኝ» የምንል ከሆነ፣ ክርስቶስ ያሳየውን አመራር መዘንጋታችን አይደለምን? ክርስቶስ እንዲህ የሚል ይመስልሃል? «እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆንኩ፣ ለእግዚአብሔር ልጅ የሚገባውን ያህል ክፈሉኝ:: ይህ ምን ያህል ሊሆን ይችላል? ቢያንስ በቀን አንድ ሚሊዮን ዶላር!» አንድ ጊዜ አንድ ሰው ሲናገር እንዲህ አለ:: «ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቁበት መንገድ አስገራሚ ነው:: ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለው የሚያስቡት ብዙ ደመወዝ እየተከፈላቸው በትልቅ ቤተ ክርስቲያን ማገልገልን ነው::» ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰዎች የገንዘብ ጥቅምን ትተው እንደ ኢየሱስ እንዲያገለግሉ

አይጠይቃቸውም ማለት ነው? አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን «ጀግኖች» ዛሬ የሚከበሩት ላገኙት ጥቅም ሳይሆን ለከፈሉት መሥዋዕትነት ነው:: እንደ ኢየሱስ የራስን ጥቅም ሠውቶ ሌሎችን ከማገልገል ይልቅ፣ የዓለምን የገንዘብና የጥቅም መንገድ መከተሉ ምንኛ ቀላል ነው!

> 7ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 9:10-13፤ 11:19፤ ሉቃስ 15:1-2ን አንብብ:: ሀ) የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን የከሰሱት ምን አድርገሃል በማለት ነበር? ለ) ኢየሱስ «የኃጢአተኞች ወዳጅ» የተባለው ለምንድን ነው? ሐ) ኢየሱስ እጅግ ቅዱስ ሆኖ ሳለ ኃጢአተኞች ከእርሱ ጋር መሆን የሚያስደስታቸው ለምንድን ነው? መ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማኅበረሰቡ ካገለላቸው ሰዎች ጋር አብሮ ማሳለፍ የሚመቻቸው ይመስልሃል? ለምን?

ሐ. የኢየሱስ አመራር በራሱና ማኅበረሰቡ ባገለላቸው ሰዎች መካከል ልዩነት አልፈጠረም:: እርሱ ከሀብታሞች ጋር በመወዳጀት ድሆችን፣ ያልተማሩትን፣ የተናቁትን የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ ሴቶች ወይም ልጆች ዝቅ አድርጎ አልተመለከተም:: እንዲያውም ኢየሱስ ከተራው ሕዝብ ጋር ከፍተኛ ቅርበት ስለ ነበረው፣ የእርሱን ቅዱስነትና የራሳቸውን ኃጢአተኝነት እያወቁ አብረውት ለመሆን ይፈልጉ ነበር:: (ዛሬ ስንት ሴተኛ አዳሪዎች ወይም ሽከላ ሠሪዎች ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር ለመነጋገር ይደፍሩ ይሆን?) ኢየሱስ ከሴተኛ አዳሪዎች፣ ከቀራጮችና ከለካራሞች ጋር መሆኑ የአያሁድ የሃይማኖት መሪዎችን አበሳጭቶ ነበር:: ኢየሱስ ሁሉንም ሰዎች በእኩል ደረጃ ይወድ ነበር:: ድሀ ወይም ሀብታም፣ የተማሩ ወይም ያልተማሩ፣ ወንዶች ወይም ሴቶች፣ ትልልቆች ወይም ልጆች መሆናቸው ምንም ዓይነት የተለየ ስሜት አልፈጠረበትም:: ጥሩ ስም ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑ እንኳን እርሱን አላሳሰበውም:: ኢየሱስ ከሴተኛ አዳሪዎች፣ ጠጪዎች፣ ቀራጮች፣ ለምጻሞች፣ መበለቶች፣ ወዘተ. . . ጋር ግልጽ የሆነ ግንኙነት ነበረው:: ለእያንዳንዳቸው የሚያሳየው አክብሮትና አገዛ አንድ ዓይነት ነበር:: ፈሪሳውያን ከተናቁት ሰዎች ጋር ለምን ይህን ያህል ጊዜ እንደሚያሳልፍ በጠየቁት ጊዜ፣ የሐኪም ዓላማ በሽተኞችን ማከም መሆኑን ገልጾላቸዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ኢየሱስ የመጣው ኃጢአተኞችን ለማዳን ነበር:: ስለዚህ ከእነርሱ ጋር



መሆን ነበረበት:: ፈሪሳውያንም ኃጢአተኞች ነበሩ:: ነገር ግን ኃጢአተኛነታቸውን ለመቀበልና የኢየሱስን ርዳታ ለማግኘት ፈቃደኞች አልነበሩም:: ኃጢአተኞቹ ግን መንፈሳዊ ሕመም እንዳለባቸው ያውቁ ነበር:: ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ጊዜ በማሳለፍ መንፈሳዊ ችግራቸውን ለመፍታት ፈቃደኛ ነበር::

ሁልጊዜም የዓለም አመራር የሚዛመደው አንድ ሰው በማኅበረሰቡ ውስጥ ካለው ደረጃ ጋር ነው:: የተማሩና ሀብታም ከሆኑ፣ ጓደኝነታቸውን ለማግኘት እንጥራለን:: ከዝነኛ ሰው ጋር ጊዜ ለማሳለፍ እንፈልጋለን:: ነገር ግን ያልተማሩና ድሆችን ከጓደኝነት ተራ እናርቃለን:: ሴተኛ አዳሪዎችን፣ ሌቦችን፣ ሽከላ ሠሪዎችን፣ ወዘተ. . . ደግሞ አንንቃለን:: በዚህም ምክንያት ለርዳታ ወደ እኛ አይመጡም:: እኛም ከእነርሱ ጋር ሆነን ለመታየት አንፈልግም:: «ሰው ምን ይለኛል?» እንላለን::

ነገር ግን የክርስቶስን የአመራር ምሳሌነት ለመከተል ከፈለግን፣ የዓለምን አመዳደብ መከተል የለብንም:: ሰዎችን ሁሉ በእኩል ደረጃ መመልከት አለብን:: ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጡር መሆናቸውን ስለምናውቅ፣ በእኩል ደረጃ ልናከብራቸው ይገባል:: ሀብታም ወይም ድሀ፣ ወንድ ወይም ሴት፣ ከጥሩ ቤተሰብ ወይም ከመጥፎ ቤተሰብ ቢወለዱ፣ የተማሩ ወይም ያልተማሩ፣ የተከበረ ሥራ ያላቸው ወይም የሌላቸው ቢሆኑ፣ ሰዎችን በእኩል ደረጃ ማክበር አለብን:: ያዕቆብ 2:1-13 ከድሆች ይልቅ ሀብታሞችን መምረጥ ኃጢአት እንደ ሆነ ይነግረናል:: ዶክተሮች፣ የመንግሥት ሠራተኞችና የተማሩ አባላት ያላት ቤተ ክርስቲያን እንድትኖረን በመጣር የዓለምን የክብር መመዘኛ እየተከተልን ይሆን? ለሽምግልና የምንመርጠውስ በዓለም ዘንድ የተከበሩትን የተማሩና ሀብታም ነጋዴዎችን ይሆን? የምንከተለው የዓለምን ነው ወይስ የክርስቶስን ምሳሌነት?

> 8ኛ ጥያቄ:- ሀ) ኢየሱስ ሰዎች ከየትኛውም የማኅበረሰብ ክፍል ቢመጡ በእኩል የመመልከትን የአመራር ዘዴ ይከተል ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሰዎችን በእኩል ዓይን የመመልከት ጉዳይ ችል በማለቱ አደጋ ውስጥ ያለች ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: ለ) አብዛኞቹ አብያተ

ክርስቲያናት ያልተማሩትና የድሆች አብያተ ክርስቲያናት ከመሆን ይልቅ የተማሩ ሰዎች አብያተ ክርስቲያናት ለመሆን የሚፈልጉት ለምንድን ነው? ሐ) ይህ ለሰዎች ለሰምንሰጠው ዋጋ ምን ያሳያል?

9ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 20:24-28ን አንብብ:: ሀ) ኢየሱስ ከሁሉም የሚልቅ መሪ ማን ነው አለ? ለ) ማቴ. 20:26-28ን በቃልህ አጥና::

መ. ኢየሱስ መሪነትን ጥቅም የሚገኝበት ነገር ሳይሆን፣ ሕይወትን አሳልፎ መስጠት አድርጎ ነበር የተመለከተው:: እውነተኛ አመራር ሌሎችን የማገልገል ብቃት እንደ ሆነ ገልጾአል:: አንድ ሰው ትልቅ መሪ ነው የሚባለው ሰዎችን ብዙ ባገለገለ መጠን ነው:: አገልግሎቱ ሲያንስ፣ እርሱም ታናሽ ይሆናል:: ኢየሱስም ታላቅ መሪ ሊሆን የቻለው ሙሉ በሙሉ ራሱን ለሌሎች አሳልፎ በመስጠቱ ነው:: በጣም ደክሞት ሳለ እንኳን፣ ሰዎች የእርሱን ርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ ያገለግላቸው ነበር:: የእክስቱ ልጅ የሆነው መጥምቁ ዮሐንስ በመሞቱ ምክንያት አዝኖ ሳለ፣ ሰዎችን አገልግሏል (ማቴ. 14:13-14):: ትልቁ የመሪነት አገልግሎቱ የተከሰተው በመስቀል ላይ ነው:: ይህም የሆነው ሰጠሉት ሰዎች ኃጢአት ሕይወቱን በሠዋ ጊዜ ነው::

ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ከዚህ ዓይነቱ አመራር ጥቅም ያገኘው እንዴት ነው? ዓለም እንደ ጥቅም የምትቆጥረው ምንም ነገር አላገኘም:: ደመወዝ አይከፈለውም ነበር:: መሬትም ሆነ ቤት አልነበረውም:: ጓደኞቹ ሳይቀር በሚፈልጋቸው ጊዜ ርቀውታል:: የኢየሱስ ሽልማት የመጣው በሦስት ነገሮች ነበር::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ እግዚአብሔር አብን በመታዘዝ ልቡን እንዳስደሰተ ያውቅ ነበር:: ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አብ በመታዘዝና ለሌሎች ጥቅም በመኖሩ፣ እግዚአብሔር ደስ እንደ ተሰኘበት ያውቅ ነበር:: በአገልግሎቱ መጀመሪያና መጨረሻ አካባቢ እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ደስ መሰኘቱንና እንደሚወደው ተናግሯል (ማቴ. 3:17፤ ማር. 9:7)::



ሁለተኛ፣ ኢየሱስ በአገልግሎቱ ሰዎች ከበሽታ፣ ከአጋንንት እስራትና በዋናነት ከኃጢአት ነፃ ወጥተው ሲደሰቱ በመመልከቱ ደስ ተሰኝቷል (ዕብ. 12:2-3)::

ሦስተኛ፣ በሰማይ የዘላለም ሽልማት ይጠብቀዋል:: እርሱ ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም ተሰጥቶት ነበር:: ሲቃወሙት የኖሩትን ጨምሮ አንድ ቀን ሁሉም ለእርሱ ክብርን ይሰጣል:: ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ክብር ተሰጥቶታል (ፊልጵ. 2:9-11፤ ዕብ. 1:3)::

«ምን እገኝ ይሆን?» ከሚለው የዓለም አመራር በተቃራኒ፣ «ተራውን ሕዝብ እንዴት ሳገለግል እችላለሁ? ሕይወታቸውን ለማሻሻል ምን ላደርግ እችላለሁ?» ብለው የሚጠይቁ ብዙዎች አይደሉም:: ኢየሱስ ባሳየን መንገድ ለመምራት ከፈለግን፣ ከሰዎች ጋር መሆን አለብን:: በቀዳሚነት፣ «ችግራቸውን እንዲቀርፉ ላደርግ የምችለው እንዴት ነው?» የሚል ጥያቄ ልናነሣ ይገባል:: የታመሙ፣ የደኸዩ፣ ሥራ የሌላቸው ወይም የግንኙነት ችግር ያሰባቸውን ሰዎች ለመርዳት ከእጠገባቸው መገኘት አለብን:: ምንም እንኳን ይህ ብዙ ሰዓት ቢፈጅብንም፣ እርሻችን ወይም ሥራችን ቢጎዳ፣ የገንዘብ ችግር የሚያስከትልብን ቢሆን፣ የኢየሱስን ምሳሌነት በመከተል ራሳችንን ለሌሎች እሳልፈን መስጠት አለብን::

ለመሆኑ ለዚህ ሁሉ ሥራ ሽልማታችን ምንድን ነው? የሚገርመው፣ በአመራር ውስጥ የምናገኘው ትልቁ ደስታ ሰዎች እግዚአብሔር ፍላጎታቸውን በማሟላቱና ለክርስቶስ ባላቸው ፍቅር ሲያድጉና ይህም ከፊታቸው ሳይ የሚያሳርፈውን ደስታ ስንመለከት ነው:: እግዚአብሔር እብና የምተልን ኢየሱስ በእኛ ደስ መሰኘታቸውን በማወቅ ከየትኛውም ገንዘብ የበለጠ ውስጣዊ እርካታ እናገኛለን:: አንድ ቀን ጌታ «መልካም አደረግክ ባሪያዬ:: ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» ይለናል (ማቴ. 25:21፣ 23):: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሰማይ በታማኝነት ያገለገሉትን ሰዎች እንደሚሸልም ይናገራል (ማቴ. 16:27፤ ቈላ. 3:23-25):: በምድር ላይ አገልግሎት መሸነፍንና ሌሎችን ለማገልገል ራሳችንን ዝቅ ማድረጋችንን የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይችላል:: ብዙውን ጊዜ ደግሞ

በሌሎች የሥራ መስኮች የተለማሩትን ሰዎች ያህል ገቢ እናገኝም:: በመጨረሻው ግን ይህ ልናደርገው የሚገባን ነገር መሆኑን እንረዳለን::

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን ከማገልገል ይልቅ የዓለምን ምሳሌነት ተከትለው ሰዎች እንዲያገለግሉአቸው ሲፈልጉ የተ መለከትከው እንዴት ነው? ለ) እነዚህ መሪዎች ከምእመኖቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል? ሐ) በመሪዎችና የመሪነትን ቦታ ለመያዝ በሚፈልጉ ሰዎች መካከል የሚታየው የቅንዓት ስሜት ስለ አመራር የተሳሳተ አመለካከት እንዳላቸው የሚያሳየው እንዴት ነው? መ) ፍላጎታቸው የቤተ ክርስቲያኒቱን ምእመናን ማገልገል ብቻ ቢሆን፣ በቤተ ክርስቲያናችሁ የሽማግሌዎች አመራር እንዴት ይለወጥ ነበር? |

2. ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመቆጣጠር «መዋቅር» አላዘጋጀም::

ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑ አንድ ቀን በዓለም ሁሉ እንደምትስፋፋ እያወቀ መዋቅር አለመዘርጋቱ አስገራሚ ነው:: አንድ ቤተ እምነት እንዴት መመሥረት እንዳለበት አላብራራም ነበር:: በደቀ መዛሙርቱ መካከል ግልጽ የሆነ የአመራር ዘዴ አልነበረውም:: አንዱ ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን በሌሎች ላይ የበላይነቱን ያሳየበት ሁኔታም አልነበረም:: ኢየሱስ ትኩረት ያደረገው ለአንድ ዓላማ በሚሠሩ ጓደኞሞች መካከል የቅርብ ግንኙነት በመመሥረት ላይ ነበር:: ያስተማራቸው እርሱንና አብን ሰምተው እንዲታዘዙ ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ እርስ በርሳቸው እንደ ቅርብ ጓደኞች እንዲዛመዱ አስተምሯቸዋል::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት ቤተ እምነት ሊመሠርቱ እንደሚችሉ ያልነገራቸው ለምንድን ነው? ምናልባትም ውጤታማ አመራር እንዲኖር ትልቁ ነገር የቁጥጥር መዋቅር ማዘጋጀት ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ሰው በግሉ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆኑ እንደ ሆነ ስለ ተገነዘበ ይሆናል:: ለዚህ ነው ኢየሱስ የደቀ መዝሙርነትን ምንነት በማስተማር ብዙ ጊዜ ያሳለፈው (ለምሳሌ፣ ማቴ. 8:18-22፤ ሉቃስ 14:25-33):: ደቀ መዛሙርቱ ሰዎች የአንድ ቤተ እምነት አባላት እንዲሆኑ ሳይሆን፣ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ እንዲያግዟቸው አስተምሯል (ማቴ. 28:19):: የኢየሱስ



ደቀ መዛሙርት የሚገኙባት ቤተ ክርስቲያን እምብዛም የመሪዎች ቁጥጥር አያስፈልጋትም:: ምክንያቱም ሁሉም ሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰምቶ ይታዘዛልና::

ኢየሱስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ የመሠረተው መዋቅር 12 ሰዎችን ይፋዊ ተወካዮቹ (ሐዋርያቱ) አድርጎ መምረጡ ነበር:: የእነዚህ ሐዋርያት ቀዳሚ ኃላፊነት ሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮችን ማብራራት እንጂ፣ በአስተዳደራዊ ቁጥጥር ላይ ትኩረት ማድረግ አልነበረም:: እግዚአብሔር ሐዋርያትን የተጠቀመው ቤተ ክርስቲያንን ለመመሥረት ብቻ ሳይሆን፣ እውነትና እውነት ያልሆነውን ነገር ለመወሰን ጭምር ነበር:: ሐዋርያት አብዛኞቹን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የጻፉት ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ እውነት የሆነውንና ያልሆነውን ነገር ለማሳየትና ኢየሱስን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መመላለስ እንደሚገባ ለማመልከት ነበር::

ኢየሱስ ተዋረዳዊ የቤተ ክርስቲያን አመራር መዋቅር ባለመመሥረቱ ጉዳይ ላይ ምን ያህል ትኩረት ማድረግ እንዳለብን ማወቁ አስቸጋሪ ነው:: ይህ ማለት ኢየሱስ የፈለገው ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ድርጅት ሳትሆን፣ ያልተዋቀረች ኅብረት ሆና እንድትኖር ነው ማለት ነው? ምናልባትም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሁሉን ነገር ለመቆጣጠር የሚፈልጉ ነገሥታትና ካህናት እንዳሏት እስራኤል እንድትሆን አልፈለገም ይሆናል:: ምናልባትም የተ ከታዮቹ አጥቢያዊ ቡድኖች እርሱን እንደ «ራስ» በመሰማት በትእዛዛቱ መሠረት አብረው እንዲሠሩ ፈልጎ ይሆናል:: ሽማግሌዎ ቹ (ሐዋርያቱ) ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ነገሮች ከመቆጣጠራቸው ይልቅ፣ ተከታዮቹ ሰዎች ኢየሱስን እንዲከተሉ ይረዷቸው ነበር:: ከዚያም አዳዲስ አማኞች ኢየሱስ ባስተማራቸው መንገድ ያገለግላሉ:: ይህንንም የሚያደርጉት እንደ «መሪዎች» ሳይሆን ሽማግሌዎች ራሳቸውንና እርስ በርሳቸውን በ«ማገልገል» ነው::

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኢየሱስ ቤተ እምነት አለመመሥረቱ ሥልጣንን ከአጥቢያው ሕዝብ የሚነጥቀውን መዋቅር አለመደገፉን ያሳያል ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ኢየሱስ

ይህንን ያደረገው አብያተ ክርስቲያናቸው ለራሳቸው በይበልጥ የሚስማማ መዋቅር እንዲያዘጋጁ ነጻነት ለመስጠት በመፈለጉ ነው ይላሉ:: ኢየሱስ በከፍተኛ ደረጃ የተደራጀ ቤተ እምነት በመመሥረቱ ላይ ትኩረት አለማድረጉን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: የእርሱ ትኩረት የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርትን ማኅበረሰብ መመሥረት ነበር:: ሐዋርያቱም ኢየሱስ ቤተ እምነት ለመመሥረት ያለመፈለጉን ተከትለው የሠሩ ይመስላል:: ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት እንደ ማዕከላዊ አካል ለሌሎች መመሪያዎችን የሚሰጥበትን ሁኔታ አላመለከቱም:: የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እየተሾሙ የሚያገለግሉበትን የምኩራብ አሠራር ተከትላ ነበር የምትሠራው::

ከዚህ በተቃራኒ፣ ዓለም ሰዎች በሥልጣን እርከኖች ላይ ተቆናጥጠው የሚገዙባቸውን መዋቅሮች ታደራጃለች:: ውሳኔዎች በአመራር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ባሉት ሰዎች ይሰጡና በድርጅቱ ውስጥ ወደ ታች እንዲወርዱ ይደረጋል:: የዚህ አሠራር ዓላማ ሁሉም ሰው ከላይ ያሉት መሪዎች የሚፈልጓቸውን ነገሮች እንዲያከናውን ማስቻል ነው:: እንዲህ ዓይነቱ አመራር ሰዎች ድርጅቱ የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንዲያከናውኑ በመቆጣጠሩ ላይ ያተኩራል:: ይህ አሠራር ደግሞ ሰዎች ስጦታዎቻቸውን ተጠቅመው ከፍተኛ ውጤት እንዲያስመዘግቡ አይፈቅድላቸውም::

የሰው ልጅ ተፈጥሮና የሁሉም ድርጅቶች ተፈጥሮ በይበልጥ ሰዎችን የሚቆጣጠሩና የሚገድቡ መዋቅሮችን ማዘጋጀት ነው:: መሪዎች ምን እየተከናወነ እንዳለና ማን ምን እያደረገ እንዳለ ለማወቅ ይፈልጋሉ:: በሰዎች አቅጣጫና ተግባራት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ይፈልጋሉ:: ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮቻችን እያደጉና እየተወሳሰቡ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል:: እነዚህ መዋቅሮች የበለጠ ሰዎችን የመቆጣጠር ዝንባሌ አላቸው:: ሰዎችም ቢሆኑ እግዚአብሔር መመሪያዎችን እንዲሰጣቸው ከመጠየቅ ይልቅ የበላይ መሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲነግሯቸው ይፈልጋሉ::

ምናልባትም ጠንካራ ቤተ እምነት መኖሩ ስሕተት ላይሆን ይችላል:: አዲስ ኪዳን ስለዚህ ጉዳይ የሚለው የለውም:: ነገር ግን



ጥንቃቄ ካላደረግን፣ የትልቅ ድርጅት አንዳንድ እደጋዎች የሰዎችን መንፈሳዊ እድገት ሊያደናቅፉ ይችላሉ::

11ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እያደገች ስትሄድ ምን ዓይነት መዋቅር መጠቀም እንዳለባት ያልተናገረው ለምን ይመስልሃል? ለ) እንደ መንግሥት የተለያዩ የሥልጣን ደረጃዎች ላይ የተቀመጡ መሪዎችን ያካተተ መዋቅር የሚገኝበት ቤተ እምነት የመመሥረት ጥቅሞች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) በዚህ መዋቅር ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉና መጠንቀቅ ያለብን አደገኛ ሁኔታዎች ምን ምንድን ናቸው?

3. ኢየሱስ በዘር የሚተላለፍ የአመራር መዋቅር አልመሠረተም::

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያንን እንዲቆጣጠር ልዩ ሥልጣን እንደ ሰጠውና ይህም ሥልጣን ከአንዱ ጳጳስ ወደ ሌላው እየተላለፈ እንደሚቀጥል ብታስተምርም፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ የኢየሱስ ፍላጎት መሆኑን የሚጠቁም መረጃ አይገኝም:: በመጀመሪያ አካባቢ እግዚአብሔር የተለያዩ ቡድኖችን (አይሁዶችን በሐዋ. 2፣ ክፊል አይሁዶች የሆኑትን ሰማርያውያን በሐዋ. 8፣ እና በሐዋ. 10) እንደ እኩል አካላት ወደ መንግሥቱ ለማምጣት ጴጥሮስን ቢጠቀምም፣ ሐዋርያት ለጴጥሮስ ቋሚ የአመራር ሰፍራ የሰጡት አይመስልም:: በሐዋርያት ሥራ 15 በጉባኤው ውሳኔ ላይ የማጠቃለያ አሳቦችን በማቅረብ አጽንኦት የሰጠውና በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ ላይ ሥልጣን የነበረው ያዕቆብ እንጂ ጴጥሮስ አልነበረም:: ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያንን ለመቆጣጠር ሐዋርያዊ ሥልጣኑን ለመጠቀም የሞከረበት አጋጣሚ አልነበረም:: ከሐዋርያት ወይም ከአዲስ ኪዳን መሪዎች እንዳቸውም ሥልጣናቸውን ከጎሳቸው ለሆነ ሰው ወይም ለልጆቻቸው ያስተላለፉበት ሁኔታ አልነበረም:: ከሐዋርያት ልጆች መካከል አባቶቻቸው ከሞቱ በኋላ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆኑ ሰዎች አልነበሩም:: ከዚህ ይልቅ፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር እግዚአብሔር የሚጠይቀውን መንፈሳዊ ብስለትና ባሕርይ ለሚያሳዩ ሰዎች ሁሉ ክፍት ነበር::

የብሉይ ኪዳን ነገሥታትና ካህናት ሥልጣናቸውን የሚያገኙት የተጠሰኑ ነገዶችና ቤተሰቦች ልጆች በመሆናቸው ነበር:: ሽ

ዎች በራሳቸው ነገድ ላይ ሥልጣን ይሰጣቸው ነበር:: ኢየሱስ ግን የቤተ ክርስቲያን አመራር በተወሰነ ነገድ ወይም ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ መሆኑን አልተናገረም:: ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት ትኩረት ያደረጉት በመንፈሳዊ የአመራር መመዘኛዎች ላይ ነበር:: የየትኛውም ነገድ አባል መሪ ሊሆን ይችል ነበር:: እያንዳንዱ ትውልድ መሪዎችን መምረጥ ያለበት በቤተሰብ ውርስ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ብስለትና ባሕርይ ላይ ትኩረት በማድረግ መሆን አለበት:: ኢየሱስ አመራርን ከጎሳና ከቤተሰብ መሠረቶች ውጭ ማድረጉ እኛም አንድን ሰው ከሆነ ነገድ ወይም ዝነኛ ወላጅ ካለው ቤተሰብ መምረጥ እንደሌለብን ያሳያል:: ኢየሱስ የሰጠን መመዘኛ በመንፈሳዊ ባሕርይ ላይ የተመሠረተ ነው::

> 12ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተማሩ፣ ከቤተ ክርስቲያን መሪ ጋር የሆነ ዝምድና ያላቸው ወይም የሆነ ጎሳ አባል በመሆናቸው ብቻ ለመሪነት ሲመረጡ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያን ላይ አሉታዊ ውጤቶችን የሚያመጣው እንዴት ነው? ሐ) ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዘር የሚተላለፍ አመራር ያልመሠረተው ለምን ይመስልሃል? መ) ቤተ ክርስቲያን ብዙ ደረጃዎች ያሏቸው መሪዎች የሚገኙባቸውን ብዙ የድርጅት እርከኖች ማዘጋጀቷ የሚያስከትላቸውን አንዳንድ ጥሩ ጥሩ ነገሮች ዘርዝር:: ሠ) አሉታዊ ነገሮችስ ምን ምንድን ናቸው?

4. ኢየሱስ በተተኪ መሪዎች መካከል የቅርብ ግንኙነቶችን በመመሥረትና እንዴት እንደ አገልጋይ መሪዎች ሊመሩ እንደሚችሉ በማሳየት ነበር መሪዎችን ያሠለጠነው::

ኢየሱስ የመረጠው ከዓለም እይታ አንጻር እምብዛም መሪዎች የመሆን እቅም ያልነበራቸውን ሰዎች ነበር:: የተናቁ ቀረጥ ሰብሳቢዎችንና እንደ ዓሣ አጥማጆች ያሉትን ሠራተኞች ነበር የመረጠው:: እነዚህ ሰዎች የተመረጡት አይሁዶች ያልሠለጠነች ናት ብለው ከሚያስቧት የገሊላ ከተማ ነበር:: ይህ ብዙ ኢትዮጵያውያን እንደ ቤንሻንጉል ጉሙዝን ወይም ደቡብ ኦሞን ከሚመለከቱበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው:: እነዚህን 12 ሰዎች ለሦስት ዓመታት ካሠለጠናቸው በኋላ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሮም ግዛት ሁሉ ወንጌሉን በማሰራጨት ዓለምን ለወጡ::



ኢየሱስ መሪዎችን ለቤተ ክርስቲያኑ ለማዘጋጀት የአይሁዶችን የሥልጠና ዘዴ ነበር የተጠቀመው:: አንድ የሃይማኖት መሪ ደቀ መዛሙርት የሚያፈራበትን መንገድ ነበር የተጠቀመው:: ይህ የኢየሱስ ዘዴ ምን ይመስላል?

1) ኢየሱስ ያስተማረው ከወደፊት መሪዎቹ ጋር በመኖር ነበር:: ቀን በቀን አብረውት ነበር የሚኖሩት:: ሕይወቱን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ባሕርዩንና ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ይመለከቱ ነበር:: የጸሎት ሕይወቱን ከተመለከቱ በኋላ ነበር ኢየሱስ ጸሎት እንዲያስተምራቸው የጠየቁት::

2) ሁሉንም ሰው በአንድ ዓይነት መንገድ አልነበረም ያሠለጠነው:: ኢየሱስ ከሰዎች ጋር የሚሠራው በደረጃ ነበር:: ብዙ ሕዝብ የሚያስተምርባቸው አጋጣሚዎች ቢኖሩም፣ እነዚህ ሁሉ መሪዎች እንዲሆኑ አልጠበቀም:: ከሕዝቡ ቀረብ አድርጎ የሚያስተምራቸው 70 ሰዎች ነበሩ:: እነዚህን 70 ሰዎች የምጽአቱን የምስራች የሚናገሩ አገልጋዮች አድርጎ ልኳቸዋል (ሉቃስ 10:1-21):: ሐዋርያት የሚላቸው 12 ደቀ መዛሙርትም ነበሩት (ሉቃስ 6:12-16):: እነዚህ ከሌሎች የበለጠ ሥልጣና የተሰጣቸው ሲሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያን የመጀመር ኃላፊነትም የተሰጠው ለእነርሱ ነበር:: ከ12ቱ መካከል ደግሞ ሦስቱ (ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ያዕቆብ) ከእርሱ ጋር የበለጠ ቅርበት ነበራቸው:: እነዚህ ሦስቱ የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ቁልፍ መሪዎች እንዲሆኑ በሚገባ ያሠለጠናቸው ነበሩ (ማቴ. 17:1፣ ማር. 5:37):: በመጨረሻም፣ ዮሐንስ የኢየሱስ ልዩ ጓደኛና ተማሪ እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዮሐ. 13:23)::

3) ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ለማሠልጠን ከመሞከር ይልቅ፣ በጥራት ላይ ነበር ያተኮረው:: መጀመሪያው እካባቢ በ12 ሰዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ጊዜ እንደ ማባከን ሊቆጠር ይችላል:: በመቶዎች የሚቆጠሩ መሪዎች የሚፈልቁበትን ትምህርት ቤት ሊመሠርት ይችል ነበር:: ዓላማውስ ቢሆን ዓለምን ሁሉ ማዳረስ አይደለ! እንዲህ ቢሆን ግን፣ ከማንኛውም ደቀ መዝሙር ጋር ግላዊ የሆነ ቅርበት አይኖረውም ነበር:: ብዙ ሕዝብ የሚያስተምር

ክሆነ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላይ በማተኮር የግል ትምህርቶችን ሊያስተምር አይችልም ነበር። ነገር ግን በጥቂት ሰዎች ላይ በማተኮር በሚገባ ስላሠለጠናቸው፣ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ እርሱ የፈለገውን ባሕርይ በመያዝ ውጤታማ አገልግሎት አካሂደዋል። ውጤታማ ለመሆን ከፈለግክ፣ ብዙ ሰዎችን በመጠኑ ክማሠልጠን ጥቂቶችን በሚገባ ማሠልጠኑ የተሻለ ነው።

4) የኢየሱስ ሥልጠና በንድፈ-አሳባዊ እውቀት ላይ ያተከረ አይደለም። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ሲሠራ የተመለከቷቸውን ነገሮች ያከናውኑ ነበር። ስለሆነም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዐበይት እውነቶችን ካስተማራቸውና እንዴት እንደሚያገለግሉ ካሳያቸው በኋላ፣ ኢየሱስ እውቀታቸውን በሥራ ላይ እንዲያውሉ ልኳቸዋል። ኢየሱስ ሰዎች በታማኝነት ማገልገላቸውን ለመፈተን አነስተኛ ሥራ ስጥቶ ማየት እንደሚሻል ያምን ነበር። ታማኝነታቸውን ካሳዩ በኋላ፣ ተጨማሪ ኃላፊነት ይሰጣቸዋል (ማቴ. 25:21፣ 23)።

5) ኢየሱስ የመሪነት ብቃቶችን የመሠረተው በባሕርይ ላይ ነበር። ለእርሱ የተፈጥሮ ክህሎትና መደበኛ ሥልጠና የባሕርይን ያህል አስፈላጊ አልነበሩም። ኢየሱስ ለሰዎች ሥራን የሚሰጠው እንደ ችሎታቸው ነበር - ለአንዳንዶች ብዙ፣ ለሌሎች ደግሞ ጥቂት ኃላፊነት ይሰጣቸው ነበር።

13ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ኢየሱስ ሐዋርያትን ያዘጋጀበትን ሁኔታ ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማዘጋጀት ከምንፈልግበት መንገድ ጋር አነጻጽር። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለአገልግሎት ስለ ማዘጋጀት ከኢየሱስ ምን ምን ትምህርቶችን እንማራለን?

ይህ ዛሬ ዓለም መሪዎችን ለማሠልጠን ከምትፈልግባቸው መንገዶች በብዙ መልኩ ይለያያል።

1) አሁን ያሉት መሪዎች ብዙውን ጊዜ የሚያገለግሏቸውን ሰዎች እስከዚህም አያቀርቧቸውም። ሰዎች በቅርበት እንዲያዩአቸውና ስውር የልብ ፍላጎታቸውን፣ ባሕርያቸውን፣ ወይም ተግባራቸውን እንዲያውቁባቸው አይፈልጉም። መሪዎች ሰዎች በቅርበት ካወቋቸው፣ ድክመቶቻችንን በመመልከት ሳያከብሩን ይቀራሉ የሚል ግምት ይኖራቸዋል።



2) አብዛኞቹ የሥልጠና ፕሮግራሞች ንድፈ-አሳብ በማስተማር ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ስለ አመራር «መረጃዎችን» በመስጠት ሰዎችን እናሠለጥናለን ብለን እናስባለን። አንድ ሰው እነዚህን መረጃዎች ካወቀ የመምራት ብቃት ይኖረዋል ብለን ሰለምናስብ፣ ፈተናችንም ምን ያህሉን መረጃ ያውቀዋል? በሚል አሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። በወደፊት መሪዎች ባሕርይ ላይ ብዙም ትኩረት አናደርግም። የኢየሱስን ዓይነት የአገልጋይ መሪ አመለካከት፣ መንፈሳዊ ባሕርይና ብስለት ያላቸውን ሰዎች ብቻ የሚያስመርቅ የሥነ-መለኮት ትምህርት የታለን? ተማሪዎች እንዴት የአገልግሎት ክህሎት እንዲያገኙ ለማስቻል እምብዛም ጥረት አናደርግም። በመደበኛ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞቻችን ክህሎትን ለማሳደግ ረዥም ጊዜ ይፈጃል።

3) ሰዎች መደበኛ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አገልግሎት እናስማራቸዋለን። መጀመሪያ አነስተኛ ኃላፊነት በመስጠት ግለሰቡ ታማኝነቱንና ትምህርቱን እንዲያሳይ በማድረግ፣ ከዚያ በኋላ ተጨማሪ ኃላፊነት የመስጠት ልምድ አላዳበርንም። ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን አንድ የሥነ መለኮት ምሩቅ በምትቀጥርበት ጊዜ ራሷን ለኪሳራ እንድታጋልጥ ያደርጋታል። ግለሰቡ ምን ዓይነት መሪ እንደሚሆንና ሥራው የሚጠይቀውን ኃላፊነት ማሟላት አለማሟላታቸውን ማወቅ አይቻልም። ተመራቂዎቹ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የማይችሉ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ፣ የቀጠረቻቸው ቤተ ክርስቲያን ታዝናለች። ሌሎች ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ ችግር ውስጥ ላለመግባት ፈርተው የሠለጠኑ አገልጋይ ከመቅጠር ይቆጠባሉ። የተሰጣቸውን አመራር ለማስተናገድ የሚያስችል ባሕርይ ያላጎለበቱ አንዳንድ ወጣት አገልጋዮች ለአመራር መንፈሳዊነት የጎደለው ባሕርይ ያሳያሉ።

4) ብዙ አገልጋዮችን ለማስመረቅ እንጣደፋለን። ለአብያተ ክርስቲያኖቻችን በመቶዎች የሚቆጠሩ ምሩቃን ያስፈልጉ የለም? ብለን እናስባለን። ጥቂት ሰዎችን ማሠልጠን ራስ ውድ ዋጋ

የሚጠይቅ ተግባር ነው። የተቻለንን ያህል ትልቅ ትምህርት ቤት በመገንባት ብዙ ሰዎችን (አብያተ ክርስቲያናትን የመምራት ብቃት ባይኖራቸውም እንኳን) እናስመርቃለን።

5) ለሁሉም ሰው እንደ ዓይነት ሥልጠና እንሰጣለን። በክፍላችን ውስጥ ለሁሉም ሰው እኩል መረጃ እንሰጣለን። አንዳንዶች ያንን መረጃ ሊፈልጉ ቢችሉም፣ አንዳንዶቹ መረጃውን አይጠቀሙም። መምህሩ የበለጠ እምቅ ችሎታ ወይም መንፈሳዊ ግንዛቤ ያላቸውን ሰዎች በመምረጥ የግል የሆነ ትኩረትና ሥልጠና ሊሰጣቸው አይችልም። «ሁሉንም በእኩል ዓይን መመልከት አለብን» እንላለን። ይህ ግን ልዩ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ለማሳደግ አያስችለንም።

ሰዎችን እንደ ዓለም ዘዴ ማሠልጠኑ ምንኛ ቀላል ነው? ጳውሎስ «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ኛ ቆሮ. 11:1) ቢላቸውም፣ እኛ ግን ክሥራችን ያሉት ሰዎች ወደ እኛ እንዲቀርቡና ምን እንደምንመስል እንዲያውቁ አንፈልግም። ስጦታ ያላቸው ሰዎች ከአጠገባችን እንዲደርሱ እንፈልግም። ምክንያቱም እነርሱ ማገልገል ከጀመሩ፣ ምእመናን እኛን አይሰሙንም ብለን እናስባለን። ነገር ግን ፍላጎታችን ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ እንደምትፈልገው እንድታድግ ቢሆን፣ እግዚአብሔር ብዙ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች በሚያመጣበት ጊዜ የበለጠ ደስተኞች እንሆን ነበር። የዓለምን የትምህርት ዘዴ ስለ ለመድን፣ ሰው ሊማር የሚችለው በትምህርት ቤት ብቻ ነው ብለን እናስባለን። መደበኛውን የትምህርት መመዘኛ ያሟሉትን ሰዎች ነው የምንፈልገው። ወጣትና ያልተሞከሩ መሪዎችን በመቅጠር ወዲያውኑ በመሪነት አገልግሎት ላይ እናስቀምጣለን። በመንፈሳዊ ባሕርይ ወይም በብስለት ላይ እምብዛም እናተኩርም። ቀስ በቀስ አነስተኛ ኃላፊነት እየሰጠንና በታማኝነታቸው መጠን እያሳደግን እንሄድም።

14ኛ ጥያቄ፡- ከኢየሱስ ሕይወትና ትምህርቶች ስለ አመራር የምንመለከታቸውን ዐበይት ነገሮች ከልስ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የኢየሱስን የአመራር ምሳሌነት ቢከተሉ አመራር (መሪዎችም ሆኑ መዋቅሮች) እንዴት እንደሚቀየሩ ከልስ።



ኢየሱስ ምሳሌያችን ከሆነ፣ አብያተ ክርስቲያኖቻችን በአመራር ረገድ እርሱን ለመምሰል አልቻሉም ማለት ነው። ስለ መሪነት ባለን ግንዛቤ ላይ የዓለምና የባህላችን አመለካከት ከፍተኛ ጫና ይፈጥርብናል። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጓት እንደ ዓለም ዓይነት ብዙ መሪዎች አይደሉም። የሚያስፈልጉን ታላቅነታችን በትሕትና ከምናበረክተው አገልግሎት ይመነጫል የሚል እምነት ያላቸው መሪዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ከሞተ በኋላ በሐዋርያቱ አማካኝነት እንዳደረገችው፣ በዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ልታመጣ የምትችለው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው።

## ሁለተኛ ቀን

15ኛ ጥያቄ፡- መንፈስ ቅዱስ በሁሉም አማኞች ላይ ከመጣ በኋላ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከነበሩት አይሁዶች በተለየ የአዲስ ኪዳን አማኞች ያገኟቸውን የተለዩ ነገሮች ዘርዝር።

ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ካረገና በአማኞች ውስጥ ይኖር ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ከላከ እነሆ 2000 ዓመታት ሊሆኑ ተቃርበዋል። ይህ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ የማደሩ ጉዳይ ካመንንበት ጊዜ ጀምሮ ስንሰማው የኖርነው በመሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ከአማኞች ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የሚያመጣቸውን ታላላቅ ነገሮች ሳናስብ እንቀራለን። አሁን የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ የሚኖሩ «አካላዊ ሰዎች» ሳይሆኑ፣ የኢየሱስ ተከታዮች የሆኑትን ወገኖች ሁሉ የሚያካትቱ «መንፈሳዊ ሰዎች» ናቸው። እግዚአብሔር ከእንግዲህ በአንድ የአይሁድ ጎሳ ላይ ማተኮሩ ቀርቶ፣ ሰዎችን ሁሉ ወደ ራሱ ይስባል። መንፈስ ቅዱሱንም ቢሆን የሚሰጠው ሕዝቡን እንዲመሩ ለሚፈልጋቸው የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ ለሁሉም እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ነው። ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ የማደሩ እውነታ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሚመራበትና በሚተዳደርበት ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ልዩነት ይፈጥራል።